# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የድህረ-ምረቃ መርሐ-ግብር

# በ 12ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ፤ ከስነ ትምህርታዊ ሰዋስው አንጻር

በ

እስሌማን አባይ መኮንን

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ · ADDIS ABABA U

IES LIBRARY

ግንቦት 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# በ 12ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ፤ ከስነ ትምህርታዊ ሰዋስው አንጻር


በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የቋንቋዎች ጥናት ፋክልቲ

የአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ትምህርት


በ ተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛን ማስተማር (ALTA) ኤም. ኤ. ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት


በ

እስሌማን አባይ መኮንን


ግንቦት 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የድህረ-ምረቃ መርሐ-ግብር

በ 12ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ፤ ከስነ ትምህርታዊ ሰዋስው አንጻር

በ

እስሌማን አባይ መኮንን

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ስም ፊርማ

ጌታሁን [illegible]

አማካሪ

[illegible]

ፈታኝ

# ምስጋና

ከጥናቱ መነሻ እስከ መድረሻ የጥናትና ምርምሩን ትክክለኛ አቅጣጫ በመጠቆም፣ ረቂቁን በማንበብና ተገቢውን እርማት በመስጠት ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝ አማካሪየና መምህሬ ለዶ/ር ጌታሁን አማረ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ልባዊ ምስጋናየን አቀርባለሁ።

ለጥናቱ የሚያስፈልገኝን ወጪ በመሸፈን ትብብር ላደረገልኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ።

ለጥናትና ምርምር ስራየ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን አገኝ ዘንድ የተለያዩ ሰነዶችንና መጻሕፍትን ላዋሱኝና በቃለ መጠይቅና የጽሑፍ መጠይቅ መረጃዎችን እንድሰበስብ ለተባበሩኝ መስሪያ ቤቶች፣ ድርጅቶችና ግለሰቦች ምስጋናየ ላቅ ያለ ነው።

በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለዚህ ጥናት መሳካት አስተዋጽኦ ላደረጉልኝ መምህሬ አቶ ጌታቸው እንዳላማው(ረዳት ፕሮፌሰር) እና ለሌሎችም የቋንቋዎች ጥናት ተቋም መምህራን ከፍ ያለ ምስጋናየ ይድረሳቸው።

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዓላማ በ 1998 ዓ.ም ተሻሽሎ ስራ ላይ በዋለው የ 12ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አደረጃጀት አቀራረብ ከስነ ትምህርታዊ ሰዋስው አንጻር መገምገም ነው። ጥናቱ መነሻ ያደረገውም የሰዋስዋዊ ይዘቶቹ አደረጃጀትና አቀራረብ ምን ይመስላል? ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ ለቋንቋው ቅርጽ፣ ፍቺና አጠቃቀም ምን ያህል ትኩረት ሰጥተዋል? የሚሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ ነው። እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስም ከተተኳሪ መጽሀፉ በሰነድ ፍተሻ፣ ከመማሪያ መጽሐፉ አሻሻይ ባለሙያና ከናሙና መምህራን በቃለ መጠይቅ እንዲሁም በናሙናነት ከተመረጡ ተማሪዎች በጽሑፍ መጠይቅ አስፈላጊው መረጃ ተሰብስቦና ተደራጅቶ አይነታዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በገላጭ የምርምር ስልት የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ ተሰጥቷል። ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ ከግልጽነት፣ ከትክክለኛነት፣ ከተገቢነት፣ ከተከታታይነት፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት እንዲሁም የተማሪዎችን ትምህርታዊ ዳራ ከማገናዘብ አንጻር ጥሩ ገጽታ ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል። ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ የታላሚውን ቋንቋ ቅርጽ የሚተነትኑ እንጂ ለመዋቅሩ ፍቺና አጠቃቀም ትኩረት ያላደረጉ ናቸው። በዚህም የታላሚውን ቋንቋ ትክክለኛ ሰዋስው ማሳወቅና ይህንን ተጠቅሞ ተግባቦት መፈጸም ከሚሉት የሰዋስው መማር ማስተማር ዓላማዎች ውስጥ መጀመሪያ ከተጠቀሰው ዓላማ አንጻር ጥሩ ቢሆኑም በሁለተኛው ግን ደካማ ሆነው ተገኝተዋል። በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተካተው የሚገኙት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከደረጃው መርሃ ትምህርት ጋር ያልተዛመዱ ሆነው ተገኝተዋል። ይህም የመማሪያ መጽሐፉ የማሻሻል ስራ ከሰዋስው ትምህርት ማቅረቢያ ንድፈ ሐሳባዊ መርሆች አንጻር ጥሰት የታየበት ሆኖ ተገኝቷል።

## የሰንጠረዦች ማውጫ

ገጽ

ሠንጠረዥ 1፣ የመማሪያ መጽሀፉ አጠቃላይ ቅኝት ....................................34

ሠንጠረዥ 2፣ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ስለተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ገለጻዎች/ማስታዎሻዎች/ግልጽነት ለቀረበው ጥያቄ ተማሪዎች የሰጡት መልስ ....................................36

ሠንጠረዥ 3፣ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ስለተካተቱት የሰዋስው መልመጃ ትዕዛዛት ግልጽነት ለረበው ጥያቄ ተማሪዎች የሰጡት መልስ ...............38

ሠንተረዥ 4፣በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችና የስርጭት ሁኔታ ....................................40

ሠንተረዥ 5፣ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከደረጃው ተማሪዎች የመስራት አቅም ወይም የክፍል ደረጃ ጋር ካላቸው ተገቢነት አንጻር ለቀረበው ጥያቄ ተማሪዎች የሰጡት መልስ.....47

ሠንተረዥ 6፣ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የደረጃውን ተማሪዎች ትምህርታዊ ዳራ ከማገናዘብ አንጻር ለቀረበው ጥያቄ ተማሪዎች የሰጡት መልስ ....................................48

ሠንተረዥ 7፣ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የድግሞሽ መጠን....................................51

ሠንጠረዥ 8፣ ስለመማሪያ መጽሐፉ ሰዋስዋዊ መልመጃዎች ተከታታይነት ለቀረበ ጥያቄዎች ተማሪዎች የሰጡት መልስ ....................................54

ሠንተረዥ 9፣ ተደጋግመው የሚቀርቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ስፋትና ጥልቀት እየቸመሩ ከመሄድ አንጻር ለቀረበ ጥያቄ ተማሪዎች የሰጡት መልስ ......59

# ማውጫ

ርዕስ ገፅ

ምዕራፍ አንድ

1.መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................ 1

1.2 የጥናቱ አላማ ........................................ 3

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................ 4

1.4 የጥናቱ ወሰን ........................................ 4

ምዕራፍ ሁለት

2. ክለሳ ድርሳን ........................................ 6

2.1 የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ........................................ 6

2.1.1 የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ምንነት ........................................ 6

2.1.2 የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት አይነቶች ........................................ 6

2.1.3 የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት አስፈላጊነት ........................................ 8

2.2 ሰዋስው ........................................ 9

2.2.1 ሰዋስው ምንድን ነው? ........................................ 9

2.2.2 የሰዋስው ትምህርት አጭር ታሪክ ........................................ 11

2.2.3 ሰዋስውን ለምን እናስተምራለን? ........................................ 12

2.3 ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ........................................ 12

2.4 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ

የሚኖራቸው አደረጃጀትና አቀራረብ ........................................ 16

2.4.1 አቀራረብ ........................................ 16

2.4.1.1 ግልጽነት ........................................ 16

2.4.1.2 ትክለኛነት ........................................ 17

2.4.1.3 ተመጣጣኝነት ........................................ 18

2.4.1.4 ተገቢነት ........................................ 19

2.4.2 አደረጃጀት ........................................ 20

2.4.2.1 ተከታታይነት ........................................ 21

2.4.2.2 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ........................................ 22

2.4.2.3 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት ....................................22
2.4.2.4 ሂደት ተኮርና ውጤት ተኮር የሰዋስው ትምህርት ............24
2.5 የስነ ትምህርታዊ ሰዋስው መገለጫዎች ....................................24
2.6 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ....................................................26
ምዕራፍ ሶስት
3. የጥናቱ ዘዴ.......................................................................29
3.1 የጥናቱ መረጃ ምንጭ ........................................................29
3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ.................................................29
3.2.1 የሰነድ ግምገማ...............................................................29
3.2.2 ቃለ-መጠይቅ .................................................................29
3.2.3 የፅሑፍ መጠይቅ..............................................................30
3.3 የናሙና አወሳሰድ..............................................................30
3.3.1 የክልል፣የዞንና ወረዳ ናሙና አወሳሰድ.....................................30
3.3.2 የትምህርት ቤቶች ናሙና አወሳሰድ .......................................30
3.3.3 የመምህራን ናሙና አወሳሰድ...............................................31
3.3.4 የአሻሻዮች ናሙና አወሳሰድ ................................................31
3.3.5 የተማሪዎች ናሙና አወሳሰድ ...............................................31
3.4 የመረጃ አተናተን...............................................................31
ምዕራፍ አራት
4. የመረጃዎች ትንታኔ ...........................................................33
4.1 የመማሪያ መጽሐፉ አጠቃላይ ቅኝት ........................................33
4.2 በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ.34
4.2.1 ከግልጽነት አንጻር ........................................................ 34
4.2.2 ከትክክለኝነት አንጻር ......................................................38
4.2.3 ከተመጣጣኝነት አንጻር ....................................................39
4.2.4 ከተገቢነት አንጻር .........................................................45
4.3 በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት.50
4.3.1 ከተከታታይነት አንጻር ....................................................59
4.3.2 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት አንጻር ..............................61

4.3.3 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት አንጻር .................................. 61
4.3.4 ከሂደት-ተኮርና ውጤት-ተኮር የሰዋስው ማስተማር አንጻር...............63
ምዕራፍ አምስት፡- ማጠቃለያና አስተያየት
5.1 ማጠቃለያ .........................................................................65
5.2 አስተያየት.........................................................................68
ዋቢ ፅሑፎች.........................................................................70
አባሪ አንድ .........................................................................76
አባሪ ሁለት .........................................................................73
አባሪ ሶስት .........................................................................85

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ አይነተኛዉን ሚና ከሚጫወቱ የትምህርት መሳሪያዎች ዉስጥ መማሪያ መጻሕፍት ግንባር-ቀደም ተጠቃሽ ናቸው። የቋንቋ ትምህርቱ የእውቀት፣የተግባቦት፣የክህሎትና የስብእና እሴቶችን ማበርከት ይችል ዘንድም ትምህርቱ ስነ ትምህርታዊ የሆነ አቀራረብ ሊኖረዉ ይገባል (Nunan፣1991 እና Bygate and et.al፣ 1994)። የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ የስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ቃና ይኑረው የሚሰውን ወቅታዊ አቅጣጫ መሠረትና ምንነቱን ቀጥሎ እንመለከታለን።

የስነ ትምህርታዊ ሰዋስውን መሰረት አስመልክተዉ Nunan (1991፣152) እንደለገፁት፣ የቋንቋ ትምህርት በተግባቦታዊ አቀራረብ መሰጠት አለበት በማለት የዛሬ ሁለት አስርተ-አመታት ገደማ በተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ መተግበር ጀመረ። ይህ ዘዴ፣በታላሚው ቋንቋ ሐሳብን ማስተላለፍ ላይ እንጅ ሰዋስዋዊ ትምህርትን ገሸሽ ያደረገ ነበር። በዚህም ተማሪዎች በቋንቋው ሐሳባቸውን መግለፅ ቢችሉም የቋንቋውን ትክክለኛ ሰዋስው በማወቅ የተስተካከለ የተግባቦት እዉቀትን ለማግኘት አልቻሉም ነበር።

ከቅርብ አመታት ወዲህ ተቀባይነት እያገኘ ያለው የስነ ትምህርታዊ ሰዋስው አቀራረብ መሰረትም ጥንታዊው የቋንቋ ማስተማር ዘዴና ተግባቦታዊ የሰዋስው ትምህርት አቀራረቦች የነበሩባቸውን ግድፈቶች ባሟላ ሁኔታ ትምህርቱ የቋንቋውን የቅርፅና የተግባቦት እዉቀት አጣምሮ ማበርከት በሚያስችል መልኩ ተቃኝቶ መቅረብ አለበት የሚል ነዉ (Nunan 1991፡ 152)።

Little (1994፣99) እንደገለጹት፣ ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ሶስት ጉዳዮችን ያጠቃልላል። አንደኛ ስነ ትምህርታዊ ሂደትን ማለትም የታላሚውን ቋንቋ ስርኣት መሠረታዊ የሆነ የቋንቋ ትምህርት ስነ-ዘዴን፣ ሁለተኛ ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ማለትም ስለታላሚው ቋንቋ ስርዓት በአንድ ወይም በሌላ መልኩ መረጃ የሚሰጡ ምንጮችንና ሶስተኛ የሂደትና የይዘት ቅንጅትን ያካትታል።

Baygate and et.al. (1994፣34) እንደገለፁት፣ ስነ ትምህርታዊ ሰዋስዉ ተማሪ ተኮር ወይም መምህር ተኮር ለሆነ ማንኛውም ሰዋስዋዊ ገለፃና ስነ ትምህርታዊ አቀራረቡን በመወከል የሚያገለግል አጠቃላይ ብያኔ ነው። ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ገላጭ ወይም አዛዥ ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ የማስተማሪያ ሰዋስው ወይም ማጣቀሻ ሰዋስው ሊሆን ይችላል። አላማዉም የአፍመፍቻ ቋንቋ እውቀትን ለማሻሻል ወይም የዉጭ ቋንቋን ለማስተማር ሊሆን ይችላል።

የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ለመማር ማስተማር አላማ ተነድፈው ከሚቀርቡባቸዉ ማስተማሪያ መሳሪያዎች ዉስጥ የተማሪዎች መማሪያ መፃሕፍት ይገኙበታል። በመማሪያ መፃሕፍቱ ዉስጥ የሚካተቱ ይዘቶች ትምህርታዊ ግባቸዉን ይመቱ ዘንድ ልዩልዩ ንድፈ-ሐሳባዊ ጉዳዮችን ያገናዘቡ መሆን አለባቸዉ። ይህንኑ አስመልክተዉ Dubin እና Olshtain (1986)፣ Stern (1992)፣ እና Cunningsworth (1995) እንደሚገልፁት፣ የቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት በጥንቃቄ የተመረጡና የተደራጁ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ለተማሪዎች ማቅረብ ይችሉ ዘንድ በዝግጅት ወቅት የተለያዩ ስነ ልሳናዊ፣ ስነ ትምህርታዊና ስነ ልቦናዊ ንድፈ ሐሳቦችን መሰረት ሊያደርጉ ይገባል። ከዚህ በተጨማሪ በዝግጅት ወቅትም ይሁን በስራ ላይ ከዋሉ በኋላ ተከታታይ ግምገማ ወይም ፍተሻ ሊደረግባቸዉና ከዚህም በሚገኙ ምላሾች ሊሻሻሉ ይገባል።

በመሆኑም በመማሪያ መፃሕፍት ዉስጥ ሰዋስዉን ለማስተማር የሚዘጋጁ ይዘቶች የተሻሻለና ወቅታዊ የሆነ የስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው አደረጃጀትና አዘገጃጀትን ንድፈ-ሐሳባዊ ጥቆማዎች መሰረት ማድረግ ይኖርባቸዋል። በአማርኛ መማሪያ መፃሕፍት ዉስጥ የሚዘጋጁ ሰዋስዋዊ ይዘቶችም በቋንቋ ትምህርቱ አላማና ግብ ላይ ተመስርተዉ ከላይ የቀረቡትን የስነ ትምህርታዊ ሰዋስዉን ገፅታዎች ማሟላታቸው በእጅጉ ጠቃሚ እንደሚሆን ይታመንበታል።

ከሁለት አስርት አመታት ወዲህ በሀገራችን ኢትዮጵያ አዲስ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ በመተግበር ላይ ይገኛል። ይኸዉ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት በብሔራዊ ደረጃ እንዲዘጋጁ በማድረግ ላይ ይገኛል። ከነዚህም ዉስጥ የ12ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ይገኝበታል። መማሪያ መፃሕፍትም ተከታታይ ግምገማዎች ሊደረጉባቸዉና በግምገማዎቹ ግኝቶች

ላይ በመመስረትም የማሻሻያ ስራዎች ሊከናወኑ ይገባል፡፡ ስለዚህም ይኸው የ 12ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ምን ያህል ስነ ትምህርታዊ የአዘገጃጀት ንድፈ ሐሳባዊ መሰረቶችን ያገናዘበ ነዉ? የመማሪያ መጽሐፉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከስነ ትምህርታዊ ሰዋስዉ ንድፈ ሐሳባዊ መርሆች አንጻር ምን ጠንካራ ጎንና ምንስ መሻሻልና መስተካከል ይኖርበታል? ከመርሃ ትምህርቱ ጋርስ ምን ያህል ዝምድና አላቸው? የሚሉት ጥያቄዎች ወሳኝና በጥናት ላይ የተመሰረተ ምላሽ የሚያስፈልጋቸዉ ናቸዉ፡፡ ይህን ጥናት በተጠቀሰው መማሪያ መጽሐፍ ላይ ለማድረግ አነሳሽ የሆነው ምክንያትም አጥኚው በመማሪያ መጽሀፉ ያስተማረ መሆኑና ለድህረ ምረቃ ማሟያነት በወሰዳቸው የስነ ልሳን ኮርሶች ውስጥ ስነ ትምህርታዊ ሰዋስውን በሚመለከት ባገኘው ግንዛቤ መሰረት በመማሪያ መጽሐፉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ላይ መሻሻል የሚኖርባቸው ገጽታዎች ይኖራሉ ብሎ በማሰቡና በጥናቱ የሚገኙ ውጤቶችም ጠቃሚ የመፍትሄ ሐሳቦችን ሊጠቁሙ ይችላሉ ብሎ በማመኑ ነው፡፡

አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር በብሔራዊ ደረጃ ከተዘጋጁ የተማሪዎች መማሪያ መፃሕፍት ዉስጥ በ 1998 ዓ.ም ተሻሽሎ ስራ ላይ የዋለው የ12ኛ ክፍሉ መማሪያ መጽሐፍ ይገኝበታል፡፡ በዚህ ጥናት ዉስጥም ቀደም ሲል የተጠቀሱትን መሪ ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ በዚህ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ዉስጥ የሰዋስዉ ይዘቶችን ከስነ-ትምህርታዊ ሰዋስዉ የይዘት አደረጃጀትና አቀራረብ መርሆች አንፃር ለመመርመር ጥረት ያደርጋል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋነኛ አላማ በ 1998 ዓ.ም ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ተሻሽሎ በተዘጋጀዉ የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶችን አደረጃጀትና አቀራረብ ከስነ ትምህርታዊ ሰዋስው መርሆች አንፃር መፈተሽ ነው፡፡ ይህን አጠቃላይ አላማ መሰረት በማድረግም ለሚከተሉት ቁልፍ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ይሞክራል፡፡

1. ተተኳሪ በሆነው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ምን ያህል ስነ ትምህርታዊ ነው?

2. የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ለቋንቋው ቅርጽ፣ ፍቺና አጠቃቀም የሰጡት ትኩረት ምን ያህል ስነ ትምህርታዊ ነው?
3. ከስነ ትምህርታዊ የሰዋስው ትምህርት የይዘቶች ማደራጃና ማቅረቢያ መርሆች አንጻር የመማሪያ መጽሀፉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ምን ጠንካራና ምንስ መሻሻል የሚኖርበት ገጽታ አለ?

## 1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

መማሪያ መፃሕፍትን በዝግጅት ወቅትና በስራም ላይ ከዋሉ በኋላ መገምገሙ መፃሕፍቱን በቀጣይ ለማሻሻል በእጅጉ ይጠቅማል። ይህ ጥናትም በአገልግሎት ላይ በሚገኘዉ በ12ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ዉስ ጥ የሚገኙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ስነ-ትምህርታዊነት ለመመርመር የሚሞክር በመሆኑ ቀጣዮቹ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፤

1. በጥናቱ ተተኳሪ በሆነዉ መማሪያ መፅሐፍ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች ምን ያህል ስነ ትምህርታዊ እንደሆኑ በመፈተሽ የታዩ ጠንካራ ጎኖች ቀጣይነት እንዲኖራቸዉ፤ደካማ ጎኖቻቸዉ ደግሞ እርምት እንዲደረግባቸዉ ለመጠቆም የበኩሉን አስተዋፅኦ ሊያበረክት ይችላል።
2. የደረጃውን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ የሚያዘጋጁና የሚያሻሽሉ አካላት በዝግጅታቸውም ሆነ በማሻሻል ሂደታቸው ሊገለገሉባቸው የሚችሉ ግብዓቶችን በአቅሙ ይጠቁማል።
3. የቋንቋ መምህራን የሰዋስው መማሪያ መማሪያዎችን ለማዘጋጀትም ሆነ በእጃቸው ያለውን ለማሻሻል ሲነሱ መነሻ ሐሳብ ያገኙበታል።
4. ከዚህ በኋላ፣ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ለሚደረጉ ጥናቶች እንደ መነሻ ሊያገለግል ይችላል።

## 1.4 የጥናቱ ወሰን

የአማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለማስተማር መማሪያ መፃሕፍት በሐገር-አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅተዉ ስራ ላይ እያዋሉ ይገኛሉ። ከነዚህ መፅሐፍት ዉስጥ በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሚሆነዉ በ 1998 ዓ.ም ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ተሻሽሎ

የተዘጋጀዉ ይሆናል። ጥናቱ በመማሪያ መፅሐፉ ዉስጥ የተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶችን አመራረጥ፣አቀራረብና አደረጃጀት ከስነ ትምህርታዊ ሰዋስዉ ንድፈ ሐሳቦች አንጻር ይፈትሻል። መማሪያ መጽሐፉ በተመሰረተበት መርሃ ትምህርት ውስጥ የተካተቱት ሰዋስዋዊ ይዘቶች የዚህ ጥናት ተተኳሪ ይሆናሉ። ለ 12ኛ ክፍል ተማሪዎች እያገለገለ ካለው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውጪ ያሉት ከዚህ ጥናት ትኩረት ውጪ ሲሆኑ፣ ተተኳሪ በሆነው መማሪያ መጽሀፍ የሚገኙ ከሰዋስው ውጪ ያሉ ይዘቶችም በዚህ ጥናት አይተኮርባቸውም። በመሆኑም የዚህ ጥናት ወሰን፡ ተተኳሪ በሆነው መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ሰዋስዋዊ ይዘቶች እንዴት ተደራጅተው ቀረቡ በሚለውና እነዚህ ይዘቶች መርሃ-ትምህርቱን ምን ያህል ተከትለዋል፣ ምን ያህልስ አፈንግጠው ወጥተዋል? የሚሉትን ጥያቄዎች በመመለስ ላይ የተቀነበበ ነው።

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳን

### 2.1 የቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት

#### 2.1.1 የቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ምንነት

ስለ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ምንነት ከማውሳታችን በፊት በጥቅሉ ስለመማሪያ መፃሕፍት ምንነት የሚከተሉትን እናንሳና ወደ ጉዳያችን እንገባለን።

የመማሪያ መፃሕፍት ለአንድ የተወሰነ የትምህርት ዓይነትና የክፍል ደረጃ የሚዘጋጁ፣ ስርዓታዊ የሆነ አደረጃጀት ያላቸውና በትምህርትነት ስለቀረበው የትምህርት ዓይነት በምንጭነት የሚያገለግሉ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ናቸው (Good፣ 1973)። በተጨማሪም መማሪያ መፃሕፍት የአንድን የትምህርት ዓይነት አንኳር ፅንሰ-ሐሳብና ይዘቶችን አካተው የያዙ፣ የተለያዩ ተሞክሮዎችን፣ ምሳሌዎችንና መልመጃዎችን አካተው የሚገኙ የማስተማሪያ መሳሪያዎች መሆናቸውን Rowntree (1981) ያስረዳሉ።

ስለ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት Allwright ( 1981) እንደሚያስረዱት፣ ተ ማሪዎች ቃላሚውን ቋንቋ በራሳቸው እንዲማሩ የሚያስችሉ መመሪያዎች ናቸው። መፃሕፍቱ ተማሪዎች መማር ያለባቸውን የትምህርት ይዘቶች፣ መልመጃዎችንና ምሳሌዎችን አካትተው ይይዛሉ። በተጨማሪም የቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማቃናት ወይም ለማገዝ የሚዘጋጁ ሲሆን፣ በክፍል ውስጥ የሚተገበረውን የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ የመወሰን አቅም ያላቸው የማስተማሪያ መሳሪያዎች ናቸው።

#### 2.1.2 የቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት አይነቶች

የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት በሚከተሉት ስነ ዘዴ፣ ትኩረት ከሚሰጡት የቋንቋ ትምህርት ይዘት፣ ከተተኪሪ ተማሪዎቻቸው አንጻር ልዩነት ይኖራቸዋል።

Grant (1987፤12) ፤ የቋንቋ መማሪያ መፃሀፍትን ሰፋ ባለ መልኩ ስርዓት-ተኮርና ተግባቦታዊ በማለት መፃሕፍቱን በሁለት ከፍለዋቸዋል።

ሀ/ ስርዓት-ተኮር የቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት

እነዚህ የቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ቀደም ሲል መዋቅራዊ የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ተብለው ከተጠቀሱት ጋር በይዘትና በትኩረት ተመሳሳይ ናቸው። ዋነኛ ትኩረታቸው ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ስርዓት እንዲማሩት ማስቻል ነው። ስለዚህ ለቋንቋው ቅርፅ ወይም ሰዋስው ከፍተኛ ሽፋን ወይም ትኩረት ሲሰጡ ይስተዋላል። ተማሪዎችም የቋንቋውን ስርዓት ከተማሩት በኋላ ተገቢ ነው ብለው እንዳመኑበት አገላለፅ ይጠቀሙበታል ተብሎ ይታመናል።

ለ/ ተግባቦታዊ የቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት

እንደ Grant (1987፤13) አገላለፅ፤ ተግባቦታዊ መማሪያ መፃሕፍት ትኩረት የሚያደርጉት፡-

1. ቋንቋዉን በዉይይትና በእርስ-በርስ ግንኙነት መጠቀም ላይ፤
2. ተማሪዎች ስሜትና ፍላጎታቸውን እንዲያንፀባርቁ ማበረታታት ላይ፤
3. ከቋንቋው ቅርፅ ይልቅ በቋንቋዉ የመጠቀም ብቃት ማመቻቸት ላይ፤
4. ለማዳመጥና መናገር የበለጠ ትኩረት በመስጠት ሁሉንም ክሂሎች አጣጥመዉ ለማቅረብ መሞከር ላይ ነው።

ከዚህም በመነሳት መፃህፍቱ ከታላሚው ቋንቋ ቅርፅ ይልቅ ለቋንቋው ተግባቦታዊ አገልግሎት ትኩረት ይሰጣሉ። ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታዩ ተማሪዎች በዕውናዊ ሕይወታቸው ውስጥ ሊገለገሉበት የሚችሉትን የቋንቋ አጠቃቀም በክፍል ውስጥ የሚያለማምዱ ተግባር ተኮር የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ናቸው ማለት ይቻላል። በይዘታቸውና በትኩረታቸው ቀደም ሲል ሁኔታዊና አገልግሎታዊ ተብለው ከተጠቀሱት የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ጋር ተመሳሳይነት እንዳላቸውም መረዳት ይቻላል።

### 2.1.3 የቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት አስፈላጊነት

የቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት በቋንቋ ትምህርት ዉስጥ የሚኖሩ ክንውኖችን፣ ይዘቶችንና የማስተማር ዘዴዎችን ለመምረጥና ለመተግበር የመነሻ መሰረቶች ናቸዉ። Behar (1994፣13) እንደገለፁት፣ የቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት አንድን ትምህርታዊ ይዘት በተቀናጀ፣ ቅደም ተከተሉን በጠበቀና በተጠየቀው መንገድ በማቅረብ፤ መምህራን ይህን የአካሄድ ቅጽ ተከትለው እንዲያስተምሩ ያግዛሉ። ለመምህራንና ተማሪዎችም የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ሊያበረክቱ ይችላሉ።

- በተመሳሳይ የክፍል ደረጃ ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ተመሳሳይ ይዘት እንዲቀርብላቸው ያግዛሉ፤
- አንድን የተነደፈ አላማ ለማስፈፀም ስልታዊ በሆነ መንገድና በተደራጀ ቅፅ ለማዘጋጀት ያስችላሉ፤
- ለመምህራን፣ ምዕራፎችን ወይም አጠቃላይ ትምህርቱን የማስተማር እቅድ ለመንደፍ እንደ ቢጋር ሆነዉ ያገለግላሉ፤
- ለመምህራን፣ እንደተዘጋጀ ቅፅ በማገልገል ለትምህርቱ የሚሆኑ ቁሳቁሶችን እንዲያዘጋጁ ይረዷቸዋል።

የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ለቋንቋ ትምህርት ዓላማ ግብ መምታት ጠንካራ የኃይል ምንጭ ናቸው። በተለይም በተጠቃሚዎች፣ በአዘጋጆች፣ በተማሪዎች፣ በመምህራንና በማኅበረሰቡ ዘንድ ከፖለቲካዊ፣ ከኢኮኖሚያዊና ከማሕበራዊ ጠቀሜታ አንፃር ያላቸው ተፈላጊነት ከፍተኛ ነው (Hutchison and Torres፣1994፣ 318-19)።

ተስፋዬ (1981፣93)፣ የቋንቋ መማሪያ መፃሕፍትን አስፈላጊነት እንደሚከተለው ያስገነዝባሉ፤

1. የቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ለመምህሩ የትምህርቱን ቅደም ተከተል በመወሰንና በማቅረብ፣ መነሻውንና መድረሻውን በመጠቆምና ምን ማድረግ እንዳለበት በማመላከት ትምህርቱን ይበልጥ ተጠናክሮ እንዲያስተምር እገዛ ያደርጋሉ፤
2. የተለያዩ ጉዳዮችን በማቅረብ፣ የሚያስደስቱ መልመጃዎችን፣ የሚፈፀሙ ስራዎችን በመወሰን፣ ተማሪው የተማረውን በተግባር እንዲገልፅ ዕድል በመስጠት፣ አስተማሪውም ሆነ ተማሪው ሊገነዘቡት የሚችሉትን ይዘት

በማቅረብና ለንባብ የሚቀርቡትን ምንባቦች በቃላት ብቻ ሳይሆን በልዩ ልዩ ስዕሎች፣ ቻርቶች፣ ግራፎች፣ ፎቶ-ግራፎች፣ ወዘተ...አጅቦ በማቅረብ ትምህርቱ አስደሳች እንዲሆን ያደርጋሉ።

3. የቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ትክክለኛና ተገቢ የቋንቋ አጠቃቀም ስልትን የሚይዙ በመሆናቸው በቋንቋ ትምህርት ሂደት ከስህተት የራቀ የቋንቋ ትምህርት ይዘትን በማቅረብ የመማር-ማስተማር ሂደቱን ያግዛሉ፤
4. የቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት በቋንቋ ትምህርት ዘርፎች መካከል ያለውን ቅንጅት አጥጋቢ በሆነ ስልት ለማጣመር ያግዛሉ፤ ይህም የቋንቋውን ክሂሎች በተመጣጠነ ደረጃ ለማስተማር ከማገዛቸውም በላይ የቃላት አመራረጥን፣ የአገባብ ስርዓትን፣ የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀምን፣ የአፃፃፍ ውበትን፣ ወዘተ... የሚያጠቃልሉ በመሆናቸው ጉልህ እገዛ ያደርጋሉ፤
5. ተማሪውንም ሆነ መምህሩን የሚያነቃቁ መሆናቸው፣ በየደረጃው የተፈፀመ ተግባር መኖሩን ማመልከታቸው፣ የመምህሩን የማስተማር ዘዴ ማገዛቸው፣ ወዘተ... ዋና ዋናዎቹ የአገልግሎታቸው መገለጫዎች ናቸው።

ከላይ የተመለከትናቸው የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ጠቀሜታዎች ይገኙ ዘንድ የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ከመርሃ-ትምህርት ጋር የሚኖራቸው ዝምድና በእጅጉ ጠቃሚ ነው። ይህን አስመልክቶ Hutchison and Torres (1994፣ 320) ሲገልጹ፣ <<የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ሲዘጋጁ፣ ሲሻሻሉ፣ ሲጻፉ ፣ወዘተ. የሚችሉት የተነደፈውን መርሃ-ትምህርት መሰረት አድርገው ነው>> ብለዋል።

## 2.2 ሰዋስው

### 2.2.1 ሰዋስው ምንድን ነው?

ሰዋስው የቋንቋ ስርዓት ነው። ይሁን እንጂ ይህ ስርዓት መሠረት በሚያደረጋቸው ተዋቃሪዎች ረገድ የግንዛቤ ልዩነቶች ይታያሉ። በዚህም መሠረት ብዙዎቹ ብያኔዎች ዓረፍተነገርን መሠረት ያደረጉና ሰዋስው የቃላትን የቅንጅት ስርዓት የሚመለከት፣ በዓረፍተነገር ደረጃ የሚታይና የቋንቋውን ተናጋሪዎች ስምምነት መሠረት ያደረገ ቅደም ተከተላዊ የቃላት አገባብ መሆኑን Brown (1994፣45) ይገልፃሉ።

Ur (1996፡32) እንደገለጹት ደግሞ፣ ሰዋስው በዓረፍተነገር ደረጃ ብቻ የማይገደብና በቃልና በሃረግ ደረጃም የሚታይ የአገባብ ስርዓት ነው። የአገባብ ስርዓት ደግሞ ድምጾች ምዕላድን ወይም ቃላትን ለመመስረት ከሚፈጥሩት ቅንጅት የሚጀምርና እስከ ዓረፍተነገር ምስረታ የሚዘልቅ ነው።

ከላይ ከቀረቡት ሶስት ብያኔዎች ውስጥ ሶስት የተለያዩ ጉዳዮችን መገንዘብ እንችላለን። ከ Brown (1994) የተመለከትነው ሰዋስው በአረፍተ-ነገር ደረጃ ብቻ የሚታይ ነው፤ የሚለውን ሲሆን፤ በመቀጠል ከ Ur (1996)፣ ብያኔ እንደተረዳነው ደግሞ፤ ሰዋስው ከድምፅ በመጀመር እስከ አረፍተ-ነገር አገባብ ድረስ ያለውን ስርዓት ሁሉ አካትቶ የሚይዝ ነው። የመጀመሪያው ብያኔ ሰዋስውን በጠባቡ የሚበይን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በመጠኑ ሰፋ ያለ ነው። ከነዚህ ብያኔዎች ሰፋ ያለውን የ Larsen Freeman (2003) ብያኔ ስንመለከት ደግሞ፣ ሰዋስው ከስነ ድምፅ እስከ አረፍተ ነገር ያለውን ቅርፅ ብቻ ሳይሆን በሰዋስው ዉስጥ ያለውን አእምሮአዊ ስርዓትም ጨምሮ እንደሚይዝ ያስገነዝበናል።

ከዚህ ጥናት ዓላማ አንፃር ሰዋስውን በጠባቡ ብያኔው መመልከቱ የተሻለ ይሆናል። የሰዋስውን ሰፊና ጠባብ ብያኔ ጌታሁን (1997) ሲገልጹ፣

> «በአሁኑ ወቅት ሰዋስው የሚለው ቃል ሁለት አሻሚ ፍቺዎችን ይዞ ይገኛል። አንደኛው ፍቺ የሰው ልጅ የሚጠቀምበትን ቋንቋ እውቀት የሚጠቁመውና በሰው ልጅ አእምሮ ውስጥ ያለውን ችሎታ ነው። የሰው ልጅ ቋንቋውን ሲያውቅና ሲጠቀምበት የሚችለው ይህ ችሎታ ስላለው ነው። ከዚህ አንጻር ሲታይ ሰዋስው አእምሯዊ እሳቤ ነው ለማለት ይቻላል። ሁለተኛው ደግሞ የቋንቋ ተመራማሪዎች ስለቋንቋ ስርዓትና መዋቅር የሚያደርጉትን ገለጻ የሚጠቁመው ነው። ይህ ፍቺ የአንድን ቋንቋ የስርዓት ጥናት የሚመለከት ስለሆነ ከመጀመሪያው ፍቺ ጠባብ ነው" ጌታሁን (1997:ll) ።

በዚህ ጥናት ውስጥም የሰዋስውን ጠባብ ብያኔ በመያዝ በአማርኛ ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓት መሰረትነት ሰዋስውን ለማስተማር በተተኳሪው መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱትን ሰዋስዋዊ ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ የሚፈትሽ ነው።

2.2.2 የሰዋስው ትምህርት አጭር ታሪክ

በዚህ ክፍል የሰዋስውን ትምህርት ታሪክ በአጭሩ የምንቃኝ ሲሆን በዚህም ሰዋስውን እንዴት ማስተማር እንዳለብን ሐሳብ ማግኘት እንችላለን። ይህን አስመልክቶ Nagyne (2006፣12) እንዳስቀመጡት፣ ታሪክን መመርመር ያሁኑን ለመገንዘብና የወደፊቱን ለመገመት ሐሳብ ይሰጠናል። ያለፉት ተሞክሮዎች በአሁኑ ጊዜ ያለው የቋንቋ ማስተማር ስነ ዘዴ ምን መልክ እንዳለው ጥሩ ግንዛቤ ያስጨብጠናል። ለዚህም ሲባል በሰዋስው ትምህርት ላይ ባለፉት ዘመናት በሂደት የታዩትን ጉልህ ገፅታዎችና መሻሻሎችን መዳሰሱ አስፈላጊ ይሆናል።

ለበርካታ ክፍለ ዘመናት የቋንቋ መማር ልማዳዊ በሆነ መንገድ የላቲንና ግሪክ ቋንቋዎችን መሰረት በማድረግ ሲሰጥ ቆይቷል። በዚያ ወቅትም የቋንቋ ትምህርት ዋነኛ ግብ የነበረው የቋንቋውን ሰዋስው ለማወቅ ሲባል ነበር። ይህ የቋንቋ መማር ማስተማር አካሄድም ሰዋሰው ወትርጉም የተባለው ዘዴ እንዲፈጠር ያደረገ ነበር (Bygate and et.al.1994፣2)።

በሰዋስው ወትርጉም ዘዴ የትምህርቱ ዋነኛ አላማ የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ህግጋት በዝርዝር መተንተን መቻል ነው። ቀጥሎም ይህ እውቀት ወደ አረፍተ ነገሮችና ፅሑፎች የሚተረጎም ይሆናል። በዚህ አካሄድም ሰዋስዋዊ ህጎችን ማስታወስ ስነ ድምፅንና ስነ-አረፍተ-ነገርን ለመረዳት ይጠቅማል በማለት የዘዴው አራማጆች ያምኑ ነበር (Richard and Rodjers፣1986፣3)።

የተወሰኑ ምሁራን ሰዋስው ወትርጉም ዘዴን ተቃውመውት የነበረ ቢሆንም እስከ 20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ በስፋት ሲሰራበት ነበር። በሁለተኛው የአለም ጦርነት ወቅት የአሜሪካ ወታደሮች ቃላዊ የቋንቋ ክሂላቸውን ያዳብሩ ዘንድ በማሰብ አዝናዊ ወልሳናዊ ዘዴ በአሜሪካ የስነባህርይና የመዋቅራዊ ስነ-ልሳን ሲፈጠር ቆሰ። በዚህ ዘዴም ተማሪዎች አረፍተ ነገሮችንና ምልልሶችን እንዲደጋግሙና እንዲያስታውሱ ማድረግ

ለሰዋስዋዊ እውቀት ይረዳል የሚል እምነት ነበር። ተማሪዎቹ ሰዋስዋዊ ህግን ማስታወስ አይጠበቅባቸውም ነበር። በአጠቃላይም 20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተለያዩ ልምዶች ለቋንቋ ትምህርት መሻሻል ጠቃሚ ንድፈ-ሐሳቦች እንዲፈጠሩ የሆኑበት ወቅት ነበር። በዚሁ ክፍለ-ዘመንም የKrashen የቋንቋ መማር ንድፈ-ሐሳብና የተግባቦታዊ አቀራረብ ንቅናቄዎች ለሰዋስው ትምህርት ትኩረት ለሌላቸውና ፍቺ-ተኮር ለሆኑ የቋንቋ ማስተማር ዘዴዎች መፈጠር አነሳሾች ነበሩ (Nagyne and.et. al. 2006፣14)።

ከቋንቋ መማር-ማስተማር ጋር በተያያዘ የተግባቦታዊ አብዮት ዘመን ተብሎ የሚታወቀው ከ 1970ዎቹ ወዲህ ያለው ጊዜ፣ ሰዋስው በትምህርትነት መሰጠት አለበት ወይም የለበትም የሚሉ ዉዝግቦችን በማስተናገድም የሚታወስ ነው። ፅንፈኛ አቋም ያላቸው ምሁራን ሰዋስው በትምህርትነት መሰጠት የለበትም በማለት ይከራከሩ ነበር። ይሁን እንጂ የሰዋስው መማር-ማስተማር ተግባቦታዊ ብቃትን ለማሻሻል ጠቀሜታ እንዳለው ታመነበት። የቋንቋ ትምህርት ዓላማም ሰዋስዋዊ ዕውቀትን ያካተተ የተግባቦት ብቃትን ለማሻሻል የሚል አንድምታ ተሰጥቶት ይገኛል (Nagyne 2006፣15)።

### 2.2.3 ሰዋስውን ለምን እናስተምራለን?

የቋንቋ ትምህርት ክህሎትን ከማዳበር ባሻገር የቋንቋው ተማሪ ሊገነዘበው የሚገባውን ሰዋስዋዊ ዕውቀት ማካተት ይኖርበታል። በዚህም መሠረት አፍ መፍቻም ሆነ ሁለተኛ ቋንቋን ከተግባቦታዊ አገልግሎት በተጨማሪ የአጠቃቀም ስርዓቱን ማስተማር-መማር አስፈላጊ ይሆናል። የቋንቋ ዕውቀትና ችሎታ የሚለካው ተግበቦታዊ አገልግሎቱን ከስርዓቱ ጋር አቀናጅቶ በመገንዘብ በመሆኑ ሰዋስውን የመማር-ማስተማርን አስፈላጊነት የግድ ያደርገዋል (Brown 1994፣49)።

## 2.3 ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው

ስነ ትምህርታዊ ሰዋስዉ ማለት የተሻሻሉ የሰዋስው ማስተማር ገፅታዎችን የሚመለከት ንድፈ ሐሳብ ሲሆን ብዙውን ጊዜም በመፅሐፍ መልክ ተተርጉሞ የሚቀርብ ነው። የስነ ትምህርታዊ ሰዋስዉ አላማ ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ ተጠቅመው በምን መልክ

Bygate and et. al. (1994፣32) የCorder (1975)ን ብያኔ ጠቅሰው እንዳስቀመጡትም፣ አንዳንድ ሰዎች የስነ ትምህርታዊ ሰዋስውን አገልግሎት ለመምህሩ ብቻ እንደሆነ አድርገው የመገደብ አዝማሚያ አላቸዉ። ይሁን እንጅ የስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ፋይዳ መምህሩ የቋንቋ ትምህርቱን ይዘት ለተማሪዎቹ የሚያቀርብበትን መንገድ መምራት ነዉ።

Nunan (1991፣153) እንደሚገልፁት፣ ስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው በቋንቋ ትምህርት ሂደት ዉስጥ ያሉ መምህራንና ተማሪዎች ለመማር ማስተማር አላማ ሲባል ሲቀርቡላቸው የሚያስፈልጉ አቅጣጫዎችን የሚመለከት ንድፈ-ሐሳብ ነው።

Baygate and et.al (1994፣34) እንደገለፁት፣ ስነ ትምህርታዊ ሰዋስዉ ተማሪ ተኮር ወይም መምህር ተኮር ለሆነ ማንኛውም ሰዋስዋዊ ገለፃና ስነ ትምህርታዊ አቀራረቡን በመወከል የሚያገለግል አጠቃላይ ብያኔ ነው። ስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው ገላጭ ወይም አዛዥ ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ የማስተማሪያ ሰዋስው ወይም ማጣቀሻ ሰዋስው ሊሆን ይችላል። አላማዉም የአፍ መፍቻ ቋንቋ እውቀትን ለማሻሻል ወይም የዉጭ ቋንቋን ለማስተማር ሊሆን ይችላል።

እንደ Little (1994፣99) ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ሶስት ጉዳዮችን ያጠቃልላል። አንደኛ ስነ ትምህርታዊ ሂደትን ማለትም የታላሚውን ቋንቋ ስርአት መሠረታዊ የሆኑ የቋንቋ ትምህርት ስነ-ዘዴን፣ ሁለተኛ ስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው ማለትም ስለታላሚው ቋንቋ ስርዓት በአንድ ወይም በሌላ መልኩ መረጃ የሚሰጡ ምንጮችንና ሶስተኛ የሂደትና የይዘት ቅንጅትን ያካትታል። እንዲሁም ስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው በተመሳሳይ መልኩ የቋንቋው ትምህርት ሂደትና ይዘት አካል እንደመሆኑ ለተማሪዎች የሚቀርበውን ቋንቋ ስርዓት በማስያዝ በኩል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው።

በተመሳሳይ መንገድ Westney (1994፣72) «ከስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ማዕከላዊ ተግባራት ውስጥ አንዱ ሕጉ-ገብ (rule-governed) በሆኑ ቋንቋዊ መዋቅሮች ላይ

ህግጋትን መደንገግ ነው» በማለት ያብራራሉ፡፡ ይህ ማለት ህገኛ የሆኑ ቋንቋዊ ውቅሮችን ደረጃ በደረጃ ማቅረብ የስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው ሚና መሆኑን ያሳያል፡፡

ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ለሰዋስው መማር-ማስተማር ውስጥ የትምህርት ልምዶች ግባቸውን መምታት ይችሉ ዘንድ ሊከተሏቸው የሚገቧቸውን መርሆች ሊጠቁም የሚችል ፈርጀ ብዙ ንድፈ ሐሳባዊ አቅጣጫ ነው፡፡ አንድ የሰዋስው መፅሐፍ ስነ ትምህርታዊ የሆነ ሰዋስዋዊ ይዘት አካቷል ይባል ዘንድ ሊያሟላቸው የሚገቡ ባህርያትን Bygate and et.al. (1994) Greenbaum (1987)ን በመጥቀስ እንደሚከተለው አስቀምጠዋቸል፡፡

የስነ ትምህርታዊ ሰዋስዉ አምስት ተፈላጊ ባህርያት፣

1. በክፍሎቹ የትምህርት ርዝመት መወሰን አለባቸው፤
2. በስነ-ልቦናዊ ስነ ልሳን መሰረቶች የተቃኙ መሆን አለባቸው፤ (ለምሳሌ፡-የቋንቋ ማስተማሪያ ምርጥ ስነ ዘዴዎችን ማገናዘብ)
3. የሰዋስዉ ርዕሶችና መሳሪያዎች እንደየደረጃዉ የተመጠኑ መሆን አለባቸዉ፤
4. ተማሪዎች በአጠቃላይ ህጎች ላይ ጥላቻ እንዳይኖራቸዉ የነሱን ትኩረት የሚሰበስቡ ሆነው መዘጋጀት አለባቸው፤
5. በተግባር ሊተረጎሙ የሚችሉ መሆን አለባቸው፤ (ቢቻል ራሱን የቻለ የመልመጃ መፅሐፍ ያላቸዉ) (Bygate and et.al.1994፣33)፡፡

Bygate and et.al., (1994፣45-53) ጨምረው እንደገለፁትም፣ የቋንቋ ህግጋት (ሰዋስዋዊ ክፍሎች) ለመማር ማስተማር አላማ በመማሪያ መፃሕፍት ዉስጥ ሲቀርቡ 'ጥሩ ህግጋት' መሆን አለባቸዉ፡ 'ጥሩ ህግጋት' ሊያስብላቸዉ የሚችለዉም ከስነ ትምህርታዊ ንድፈ ሐሳቦች ጋር ተገናዝበዉ ሲቀርቡ ነዉ፡፡ የህግጋቱን ስነ ትምህርታዊነት በሚከተሉት ስድስት መስፈርቶች ልንመዝናቸዉ የምንችል ሲሆን እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ትክክለኛነት- ህግጋት እዉነተኛ መሆን አለባቸዉ- የቋንቋ ህግጋት አላማኝ በሆነ መልኩ ከስነ ልሳናዊ ሐቆች ጋር ሲጎዳኙ እጅግ ጥሩ

ይሆናል። ትክክለኛውን የሰዋስው ስርዓት ለመንገር (ለማቅረብ)

ስነ ትምህርታዊ ሰዋስዋዊያን ግላዊ ጉዳዮቻቸዉን፣ አሉታዊ

አመለካከታቸዉንና ለቋንቋ ለዉጥ ያላቸዉን ያለመቀበል አቋም

ወደ ጎን በማለት እውነተኛውን ቅርፅ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

2. ገደብ- ስነ ትምህርታዊ ህግ የተሰጠዉን ቅርፅ እስከምን ድረስ

ብቻ እንደሚሰሩ በግልፅ ማሳየት አለበት፤ ስነ ትምህርታዊ ህግ

ምንም እንኳን ትክክለኛና በጥሩ ሁኔታ የተገለፀ ቢሆንም

ተማሪዎቹ ቅርፁን መቼ መጠቀም እንዳለባቸዉና እንደሌለባቸዉ

ሊያዉቁ የሚችሉት የቀረበዉን ቅርፅ የት ላይ ቢጠቀሙበት

ትክክል እንደሚሆን በግልፅ የተቀመጠ ገደብ ሲቀርብላቸዉ ብቻ ነው።

4. ግልፅነት- ህጎች ግልፅ መሆን አለባቸዉ። የቋንቋ ህግ ግልፅ በሆነ

ስነ ትምህርታዊ ማብራሪያ ሲዘጋጅ ተማሪው በቀላሉ ይረዳዋል። ይህ

ይሆን ዘንድም አንድኛዉ የተረዳዉን መልእክት ሌሎችም በተመሳሳይ

ይረዱታል? የሚለው ጥያቄ ትልቅ ትኩረት የሚያሻዉ ነዉ።

4. ቀላልነት- ቀላልነት ገለፃን በተቃለለና ለመረዳት ይበልጥ በሚያመች

ሁኔታ ማቅረብ ማለት ነዉ። ለምሳሌ፡- የክፍፍሎችን ቁጥር መብዛት

ማስወገድና አላስፈላጊ ዝርዝሮችን ማስወገድ ወዘተ። አንድ ሰዋስዋዊ

ቅርፅ ትክክለኛ ቢሆንም እንኳን ለመረዳት በሚያስቸግር ሁኔታ ከቀረበ

ብቻውን ዋጋ አይኖረዉም።

5. ስያሜ (ፅንሰ ሐሳባዊ ጥንቃቄ)- የሰዋስዋዊ መዋቅሮች አቀራረብ

የተማሪዉን የእዉቀት ደረጃ ከግምት ባስገባና የተሻለ ይማርበታል በተባለ

ስያሜ፣ ገለፃና የአቀራረብ አማራጮች መቅረብ አለባቸዉ።

6.ጠቃሚነት፡- ስነ ትምህርታዊ ህጎች ለቋንቋ ትምህርቱ ጠቀሜታ

ያላቸዉ መሆንአለባቸዉ፤ ስነ ትምህርታዊ ሰዋስዉ ቀጥታ ለሰቋንቋ

ሳይሆን ቋንቋ ከቋንቋዉ ተማሪዎች ጋር ለሚኖረዉ መስተጋብር ታስቦ የሚዘጋጅ ነዉ። ጥሩ ስነ ትምህርታዊ ህግ ጥሬ ስነ ልሳናዊ ትንታኔን አያቀርብም። ይዘቶች ለትምህርትነት የሚቀርቡት ተማሪዎቹ በታላሚዉ ቋንቋ ለሚኖራቸዉ እዉቀት አንዳች ፋይዳ ያላቸዉ ሲሆኑ ብቻ ነው (Bygate and et.al.1994፣45-53)።

የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን በመማሪያ መፃሕፍትም ሆነ በክፍል ውስጥ ለማቅረብ የተሻሻሉ ስነ ትምህርታዊ ዘዴዎችን በማገናዘብ እንደሚያስፈልግ ተረድተናል። በዚህም መሰረት ውጤታማና ወቅታዊ የሆነው ተግባቦታዊ የሰዋስው ትምህርት እንዴት እንደሚቀርብ ተመልክተናል። ከዚህ በተጨማሪም ይዘቶቹ በመማሪያ መፃሕፍት ውስጥ ሲካተቱ የተማሪውን ልዩ ልዩ ዳራዎች ማገናዘብ እንዳለባቸውና ተዛማጅ ጉዳዮችንም መሰረት ያደረገ አቀራረብና አደረጃጀት ሊኖራቸው ይገባል። የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መፃሕፍት ውስጥ እንዴት መቅረብና መደራጀት እንዳለባቸው ደግሞ ቀጥሎ የምንመለከት ይሆናል።

## 2.4 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መፃሕፍት ውስጥ የሚኖራቸው ስነ ትምህርታዊ አደረጃጀትና አቀራረብ፤

የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ ሲቀርቡ ሊከተሏቸው የሚገቡ የአቀራረብና አደረጃጀት መርሆች አሉ።እነዚህ መርሆች ለሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ብቻ ተብለው የተነደፉ አይደሉም።መርሆቹ ለሌሎች ቋንቋ ትምህርት ይዘቶችም ሆነ ለሌላ የትምህርት አይነት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት በጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ።በዚህ ጥናት ውስጥም ከሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አኳያ ለማየት ተሞክሯል።

### 2.4.1 የይዘቶች አቀራረብ

#### 2.4.1.1 ግልጽነት

አንድ የትምህርት ይዘት ጥሩ አቀራረብ አለው የሚባለው ግልፅ ሆኖ ሲቀርብ ነው።ከሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አንፃርም ተማሪዎች የቀረበውን ትምህርት በመረዳት ረገድ ምንም እክል ወይም አጠራጣሪ ሁኔታ ሊያጋጥማቸው አይገባም። ወይም የቀረበው

የሰዋስው ትምህርት ይዘት ከአቀራረብ አንፃር ለመረዳት አስቸጋሪ መሆን የለበትም (Harmer፣1987)። ይህንንም ማድረግ ይቻል ዘንድ የቀረቡ ገለፃዎች፣ ምሳሌዎች፣ ትዕዛዞችና መልመጃዎች ግልፅና የማያጠራጥሩ እንዲሆኑ ይመከራል (Writing Language Teaching Materials፣2003)። ይህም ተማሪዎች በመማሪያ መፃሕፍታቸው ውስጥ ተካትተው የቀረቡላቸውን መልመጃዎች ለመስራት በሚሞክሩበት ወቅት መምህራቸው ወይም ሚረዳቸው ሰው ካጠገባቸው ባይኖር እንኳን ቢያንስ ከግልፅነት አንጻር የሚያጋጥማቸውን ችግር ሊያቃልልላቸው ይችላል።

Swan (1994፣48) በበኩላቸው፣ ለተማሪዎች የሚቀርቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ግልፅ መሆን እንዳለባቸው አስቀድመው ይገልፃሉ። በመቀጠልም የምናቀርበው ይዘት ግልጽነት ይኖረው ዘንድ አቀራረባችን ተገቢውን ቅደም ተከተል የጠበቀ፣ ምሳሌዎችን ያካተተ፣ ለዋና ዋና ነጥቦች አፅንኦት የሰጠ፣ አጠራጣሪ የሆኑ ነገሮችን ያስወገደ መሆን አለበት። የመማሪያ መፃሕፍት አዘጋጆች ስለሚያቀርቧቸው ሰዋስዋዊ ይዘቶች በቂ ግንዛቤ ካለመኖር አቀራረባቸው ግልፅነት እንዳኖረው ሊያደርግ ይችላል። ስለዚህ አዘጋጆች ስለሚቀርቧቸው ይዘቶች በቂ ግንዛቤ ወይም እውቀት እንዲኖራቸውና ተማሪዎች ሊረዱት በሚችሉ መልኩ በገለፃ ወይም በምሳሌዎች በመታገዝ ሊያቀርቡ ይገባል።

Sheldon (1988) እና Edge (1993) እንደሚስረዱት፣ በክፍል ስራነትም ይሁን በቤት ስራነት የሚሰጡ መልመጃዎች ግልፅ የሆነ ትዕዛዝ ሊኖራቸው ይገባል። በመልመጃዎች ስር ተካትተው የሚቀርቡ ጥያቄዎች ሊሰሩ የሚችሉበትን መንገድ የሚያሳይ ግልፅ ምሳሌ ለተማሪዎች መቅረብ አለበት። ይህም በተማሪዎች ላይ ግርታ እንዳይፈጠር ይረዳል።

### 2.4.1.2 ትክክለኛነት

Swan (1994) እንደሚያስረዱት፣ ትክክለኛነት ዕውነተኛ የቋንቋውን ስነ-ልሳናዊ ባህሪ ወይም የቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ የሚጠቀምበትን ይዘት ይመለከታል። ለተማሪዎች የሚቀርቡ ሰዋስዋዊ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ትክክልና እውነተኛ ሊሆኑ ይገባል። በርግጥ የታላሚውን ቋንቋ አንዳንድ ሰዋስዋዊ ክፍሎች ትክክለኛ ቅርፅ ማሳየቱ ከተማሪዎች ዕድሜና የትምህርት ደረጃ አንፃር ከባድና ውስብስብ ሊሆን ይችላል። ይህ

ሆኖም ግን በተቻለ መጠን ተማሪዎች የቋንቋውን ትክክለኛው ስነ ልሳናዊ ባህሪ እንዲያውቁ ያስፈልጋል።
Edge (1993) በበኩላቸው፣ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ብቻ ሳይሆኑ በአጠቃላይ በቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ ተካተው የሚገኙ የትምህርት ይዘቶች ከሚሰጡት መረጃ አንፃር ትክክለኛ መሆን እንዳለባቸው ይገልፃሉ። ይህም ይዘቶቹ ለተማሪዎች ስህተት እንዳያስተምሩ ወይም የቋንቋውን ትክክለኛ ስነ-ልሳናዊ ባህሪ የማያሳይ መረጃ እንዳያስተላልፉ ያስችላቸዋል።

ከገለጻዎቹ እንደምንገነዘበው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ለመቅረብ ስንሞክር በተለይ ትክክለኛና ከስህተት የፀዱ ግብአቶችን ለተማሪዎች ለማቅረብ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልጋል። ትክክለኛ ሰዋስዋዊ ይዘትም የቋንቋውን እውነተኛ ወይም ትክክለኛ ስነ-ልሳናዊ ባህሪ የሚያሳይና የቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ የሚጠቀምበት ወይም የሚቀበለው ነው። ይህም በክፍል ውስጥ በሚቀርብ ሰዋስዋዊ ይዘትና ከክፍል ውጪ የቋንቋው ተናጋሪዎች በሚገለገሉበት መካከል ልነት እንዳይፈጠር ያግዛል።

### 2.4.1.3 ተመጣጣኝነት

የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ሲቀርቡ ከቋንቋው ክሂል ዘርፎች፣ሰዋስው፣ቃላትና ስነ-ፅሑፍ ተመጣጥነው መሆን አለበት። የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚኖራቸው ስርጭት ከታላሚው ቋንቋ ልዩ ልዩ የሰዋስው ክፍሎች ሚዛናዊ በሆነ መልኩ እንዲቀርቡ ጥረት መደረግ አለበት። በዚህም መሰረት ይዘቶቹ ከቋንቋው የድምፅ ስርዓት፣ የምዕላድና የቃል ክፍል፣የአገባብና የፍቺ ስርዓት የተውጣጡ እንዲሆኑ ይጠበቃል። (Harmer፣ 1987፣18)።

በዚህ መሰረት የሚቀርበው የሰዋስው ትምህርት ተማሪዎች የቋንቋውን ስርዓት ትርጉም ባለው መንገድ ጠንቅቀው አውቀው በትክክለኛው መንገድ እንዲገለገሉበት ማስቻል አለበት። ይህንን አላማ ከግብ ማድረስ ይቻል ዘንድ ትምህርቱ የቋንቋውን ቅርጽ፣ ፍቺና አገባብ ማካተት ይኖርበታል (Larsen Freeman 1991፤ 280 Wilkins፣ 1972፡218 Ur 1996 ፡76 ፣Cunningsworth 1984፣16)።

ከገለፃው በመነሳት የይዘት ብቻ ሳይሆን የአቀራረብ መመጣጠንም መኖርም አለበት። ይህም ሊፈጠር የሚችለውን መሰላቸትና ፍትሃዊ ያልሆነ (ለተወሰኑ ይዘቶች ብቻ ትኩረት የሚሰጥ) የአቀራረብ ሁኔታ እንዳይኖር አስተዋፅኦ ይኖረዋል።

2.4.1.4 ተገቢነት

በቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ ተካተው የሚቀርቡ ይዘቶች ከተማሪዎች እድሜ፣ ብስለት፣ የቋንቋ ችሎታ፣ ቀደምት እውቀት፣ የትምህርት ደረጃ፣ ፍላጎትና ዝንባሌ አንፃር የሚጣጣሙ መሆን አለባቸው። ይዘቶቹ ከተማሪዎች የመገንዘብና የመስራት አቅም በላይ አስቸጋሪ ወይም ከባድ ሆነው መዘጋጀት የለባቸውም (Sheldon፣ 1988፡243)። ተገቢነት ያላቸው ይዘቶች ከተማሪዎች ደረጃ፣ ችሎታ፣ ፍላጎትና ዝንባሌ ጋር የተጣጣሙ በመሆናቸው ተማሪዎች በቀላሉ ሊረዷቸው ይችላሉ።

Harmer (1987፣19) ተገቢነትን አስመልክቶ የሚሰጡት ገለፃ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ ለቋንቋው ትምህርት ከሚያበረክቱት አስተዋፅኦ አንፃር ነው። በዚህ መሰረት የአንድ ቋንቋ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች በቋንቋው ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የቋንቋ ቅርፆች ፍቺና አጠቃቀም ለማስተማር የሚያስችሉ ወይም ተገቢ መሆን እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው። Swan (1994፣51) በበኩላቸው፣ ተገቢነትን የሚገልፁት የሚቀርቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ሰዋስው ዙሪያ ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ መስጠት ከመቻላቸው፣ ተማሪዎች ያለባቸውን ሰዋስዋዊ ችግር ከመፍታትና በአጠቃላይ ተማሪዎቹ ይዘቶቹን በዛ ደረጃ ሊማሯቸው አስፈላጊ ከመሆኑ አንፃር ነው።

በአጠቃላይ ተገቢነትን አስመልክተው የተሰጡ ገለፃዎችን ስንመለከት ሶስት አንድምታ እንዳላቸው ማስተዋል ይቻላል። የመጀመሪያው ገለፃ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከተማሪዎች ደረጃ፣ ፍላጎት፣ ወዘተ...ጋር መጣጣም እንዳለባቸው ያሳያል። በሁለተኛ ደረጃ ቀረበው ገለፃ ደግሞ ይዘቶቹ የቋንቋውን ትምህርት ዓላማ ከግብ የሚያደርሱ መሆን እንዳለባቸው ይጠቁማል። ሶስተኛው ተማሪዎች ሊማሯቸው ወይም ሊያውቋቸው የሚገቡ መሆን እንዳለባቸው ያሳያል። Harmer (1987፣18) በበኩላቸው፣ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተገቢነት ለቋንቋው ትምህርት እድገት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ፣ የተማሪዎችን እድሜ፣

የቀደመ እውቀት መሰረት የሚያደርጉ፣ በቋንቋው ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ቅርጾች፣ ፍቺና አጠቃቀምን ለማስተማር የሚያስችሉ መሆን እንዳለባቸው አበክረው ይገልጻሉ።

### 2.4.2 የይዘቶች አደረጃጀት

አደረጃጀት በመማሪያ መፃሕፍት ውስጥ የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች እንዴት ባለ ቅደም ተከተል መቅረብ እንዳለባቸው፣ የትኛው ከየትኛው መቅደም እንዳለበት፣የትኛው መከተል እንዳለበት የሚያመለክት ነው።በተጨማሪም ይዘቶቹ እንዴት ባለ መንገድ ተደጋግመውና ጥልቀት እየጨመሩ መቅረብ እንዳለባቸው ያሳያል። ከዚህም በመነሳት አደረጃጀት ከቀላል ወደ ከባድ፣ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ተጨባጭ ከሆነው ወደ ረቂቁ ወይም ተገላቢጦሻቸውን እንዲሁም ድግግሞሽን ይመለከታል ማለት ይቻላል (Nunan 1988 እና Cunningsworth 1995)።

Tyler (1949) እና Taba (1962) እንደሚያስረዱት የትምህርት ልምዶች ወይም ይዘቶች ቅንጅታዊ ውጤት ማስገኘት ይችሉ ዘንድ እርስ በርሳቸው ተደጋግፈው ሊደረጁ ይገባል። አደረጃጀታቸውም ተዋረዳዊና ጎናዊ ግንኙነትን የጠበቀ እንዲሆን ያስፈልጋል። ተዋረዳዊ ግንኙነት በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ውስጥ የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች ወይም ልምዶች የሚኖራቸውን ግንኙነት ያሳያል። ለምሳሌ በአስራ አንደኛ ክፍል የቀረቡ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በአስራ ሁለተኛ ክፍል ከቀረቡ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ጋር ላቸው ግንኙነት የይዘቶቹን ተዋረዳዊ ግንኙነት ያሳያል። ይህም አስራ ሁለተኛ ክፍል የቀረቡ ይዘቶች በአስራ አንደኛ ክፍል የቀረቡትን መሰረት አድርገው የሚገነቡ እንደሆነ ያሳያል። በሌላ በኩል የአስራ አንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ወይም ልምዶች ከአስራ አንደኛ ክፍል የታሪክ፣ የስነ-ዜጋ ወይም ከሌላ የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያላቸው ግንኙነት የይዘቶቹን ወይም የትምህርት ልምዶቹን ጎናዊ ግንኙነት ያሳያል።

በዚህ ጥናት ውስጥ ተተኳሪ የሚሆነው የአደረጃጀት ስልት የይዘቶቹን ተዋረዳዊ ግንኙነት የሚያሳየው ይሆናል። ጎናዊ ግንኙነት ከጥናቱ ትኩረት ውጪ ይሆናል ማለት ነው።በጥናቱ ውስጥ ተተኳሪ ወደሚሆነው ተዋረዳዊ አደረጃጀት ስንመለስ በስሩ

ተከታታይነት፣ ቀጣይነት፣ ከአጠቃሳይ ወደ ዝርዝር፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሚሉ የአደረጃጀት ስልቶችን እናገኛለን።

### 2.4.2.1 ተከታታይነት

ተከታታይነት በአንድ የክፍል ደረጃ የቀረቡ የትምህርት ይዘቶች ወይም ልምዶች በዛው የክፍል ደረጃ ተደጋግመው መቅረባቸውን ይመለከታል። ለምሳሌ በሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ምዕራፍ አንድ ላይ የቀረበ ይዘት በዛው የክፍል ደረጃ የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ሌሎች ምዕራፎች ውስጥ ተደጋግሞ መቅረብ እንዳለበት የሚጠቁም ነው።ይዘቱ ተደጋግሞ ሲቀርብ ግን ስፋትና ጥልቀት እየጨመረ መሆን አለበት።በሌላ አገላለፅ በምዕራፍ አንድ የቀረበው በቀጣይ ምዕራፍ ከቀረበው ጋር ተመሳሳይ የቅለት ደረጃ ሊኖረው አይገባም (Tyler 1949 እና Taba 1962)።

ተከታታይነት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በምን አይነት ቅደም ተከተል ሊደራጁና ከተማሪዎች እድገት አንፃር ስፋትና ጥልቀት እየጨመሩ ሊቀርቡ እንደሚገባ የሚያሳይ ነው።በተከታታይነት ውስጥ ድግግሞሽ ጠቀሜታ አለው። አንድ አዲስ የቋንቋ ትምህርት ይዘት አንድ ጊዜ ብቻ መቅረቡ በቂ አይደለም። ይልቁንም ተማሪዎች በተለያዩ ምዕራፎችና በተለያዩ አውዶች ውስጥ ሊያገኙት ይገባል። ይህም ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ይዘቱን በሚገባ እንዲረዱት፣ እንዲካኑትና በተገቢ ሁኔታ ለተግባቦት እንዲያውሉት ያስችላቸዋል። ድግግሞሹ በተለይም ለሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ጠቀሜታ አለው። ምክንያቱም ሰዋስዋዊ ቅርፆች በአንድ ጊዜ ትምህርት ላይያዙ ይችላሉና (Larson Freeman፣1991 እና Cunningsworth፣ 1995)።

ከገለፃዎች መረዳት እንደሚቻለው በአንድ የክፍል ደረጃ የሚገኙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በዛው የክፍል ደረጃ ተደጋግመው ሊቀርቡ ይገባል። ድግግሞሹ መሆን ያለበት ግን ኋላ የቀረቡት ቀድመው ከቀረቡት ሰፋና ጠንከራ ብለው መሆን አለበት። ይህም ሰዋስዋዊ ይዘቶቹን በስፋትና በጥልቀት ለማስተማር ይረዳል። ተማሪዎችም የሰዋስዋዊ ይዘቶቹን ቅርፅ፣ ፍቺና አጠቃቀማቸውን በደምብ እንዲያውቁና በአገልግሎት ላይ እንዲያውሏቸው ያስችላል። በተጨማሪም ተማሪዎች ተመሳሳይ የሆነ ስራን በመስራት እንዳይሰላቹና ለትምህርቱ አሉታዊ አመለካከት እንዳይኖራቸው ያደርጋል።

### 2.4.2.2 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት

በዚህ የአደረጃጀት ስልት የታላሚውን ቋንቋ ህግጋት የሚያሳይ ገለፃ አይቀርብም፡፡ በቅድሚያ ህግጋቱን ሊጠቀሙ የሚችሉ ምሳሌዎች ለተማሪዎች ይቀርባሉ፡፡ተማሪዎችም የቀረቡላቸውን ምሳሌዎች በደምብ በማጤን የቋንቋው ህግጋት ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገምታሉ፡፡ ከዛም ግምታቸውን ሊያረጋግጡ የሚችሉ ምላሾችን ከመምህራቸው ያገኛሉ፡፡ ይህ የአደረጃጀት ስልት የህፃናትን የአፍ መፍቻ ቋንቋ አለማመድ የተከተለና ተፈጥሯዊ እንደሆነ መምህራን ይናገራሉ (Cunningsworth፣ 1995)፡፡

Harmer (1987) እና Larsen Freeman (1991)፣ በበኩላቸው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአደረጃጀት ስልት ተማሪዎች ከቀረቡላቸው ዝርዝር ምሳሌዎች በመነሳት የቋንቋውን አጠቃላይ ህግጋት እንዲያወጡ የሚያነሳሳ ነው፡፡ በዚህ ስልት አንድ አዲስ ሰዋስው ትምህርት ይዘት ሲቀርብ ምንም አይነት ገለፃ አይደረግም፡፡ ዋነኛ ትኩረቱም ተማሪዎች ከቀረቡላቸው ምሳሌዎች በመነሳት ቋንቋውን ለመጠቀም የሚያስችሏቸውን ሰዋስዋዊ መረጃዎች እንዲለዩ ማስቻል ነው፡፡

### 2.4.2.3 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት

በዚህ የአደረጃጀት ስልት ተማሪዎች ስለሚማሩት ቋንቋ ህግጋት የሚያሳይ ገለፃ ይቀርብላቸዋል፡፡ ከገለፃው በመነሳትም ህግጋቱን በተግባር ላይ ወይም ለተግባቦት ለማዋል ይሞክራሉ፡፡ ይህም መሆኑ ተማሪዎች የቋንቋውን ህግጋት በፍጥነትና በቀላሉ እንዲረዷቸው ያስችላቸዋል፡፡ ሆኖም ይህ ብቻውን በቂ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በገለፃ ብቻ በመታገዝ ህግጋቱን በጥቅም ላይ ወይም ለተግባቦት ማዋሉ አዳጋች ሊሆንባቸው ይችላል፡፡ ስለዚህም ገለፃው በበቂ ምሳሌዎች ተደግፎ ሊቀርብ ይገባል (Cunningsworth፣ 1995)፡፡

Harmer (1987) እና Larsen Freeman (1991) ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአደረጃጀት ስልትን አስመልክቶ ከላይ ከቀረበው ገለፃ ጋር ተመሳሳይ ገለፃ ሰጥተዋል፡፡ በዚህ የአደረጃጀት ስልት ለተማሪዎች ስለታላሚው ቋንቋ ህግጋት የሚያሳይ ገለጻ ይቀርብላቸዋል፡፡ ገለፃውንም መሰረት በማድረግ ህግጋቱን በዝርዝር ወደመለማመድ ይቀጥላሉ፡፡ Stevick (1986) እንደሚስረዱት፣ ገለፃ ተማሪዎች ለሚያነሷቸው ሰዋስዋዊ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠትና ተማሪዎችን ለማገዝ አንዱ መንገድ ነው፡፡ አለማችውም

### 2.4.2.2 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት

በዚህ የአደረጃጀት ስልት የታላሚውን ቋንቋ ህግጋት የሚያሳይ ገለፃ አይቀርብም። በቅድሚያ ህግጋቱን ሊጠቀሙ የሚችሉ ምሳሌዎች ለተማሪዎች ይቀርባሉ።ተማሪዎችም የቀረቡላቸውን ምሳሌዎች በደምብ በማጤን የቋንቋው ህግጋት ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገምታሉ። ከዛም ግምታቸውን ሊያረጋግጡ የሚችሉ ምላሾችን ከመምህራቸው ያገኛሉ። ይህ የአደረጃጀት ስልት የህፃናትን የአፍ መፍቻ ቋንቋ አለማመድ የተከተለና ተፈጥሯዊ እንደሆነ መምህራን ይናገራሉ (Cunningsworth፣ 1995)።

Harmer (1987) እና Larsen Freeman (1991)፣ በበኩላቸው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአደረጃጀት ስልት ተማሪዎች ከቀረቡላቸው ዝርዝር ምሳሌዎች በመነሳት የቋንቋውን አጠቃላይ ህግጋት እንዲያወጡ የሚያነሳሳ ነው። በዚህ ስልት አንድ አዲስ ሰዋስው ትምህርት ይዘት ሲቀርብ ምንም አይነት ገለፃ አይደረግም። ዋነኛ ትኩረቱም ተማሪዎች ከቀረቡላቸው ምሳሌዎች በመነሳት ቋንቋውን ለመጠቀም የሚያስችሏቸውን ሰዋስዋዊ መረጃዎች እንዲለዩ ማስቻል ነው።

### 2.4.2.3 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት

በዚህ የአደረጃጀት ስልት ተማሪዎች ስለሚማሩት ቋንቋ ህግጋት የሚያሳይ ገለፃ ይቀርብላቸዋል። ከገለፃው በመነሳትም ህግጋቱን በተግባር ላይ ወይም ለተግባቦት ለማዋል ይሞክራሉ። ይህም መሆኑ ተማሪዎች የቋንቋውን ህግጋት በፍጥነትና በቀላሉ እንዲረዷቸው ያስችላቸዋል። ሆኖም ይህ ብቻውን በቂ አይሆንም። ምክንያቱም ተማሪዎች በገለፃ ብቻ በመታገዝ ህግጋቱን በጥቅም ላይ ወይም ለተግባቦት ማዋሉ አዳጋች ሊሆንባቸው ይችላል። ስለዚህም ገለፃው በበቂ ምሳሌዎች ተደግፎ ሊቀርብ ይገባል (Cunningsworth፣ 1995)።

Harmer (1987) እና Larsen Freeman (1991) ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአደረጃጀት ስልትን አስመልክቶ ከላይ ከቀረበው ገለፃ ጋር ተመሳሳይ ገለፃ ሰጥተዋል። በዚህ የአደረጃጀት ስልት ለተማሪዎች ስለታላሚው ቋንቋ ህግጋት የሚያሳይ ገለጻ ይቀርብላቸዋል። ገለፃውንም መሰረት በማድረግ ህግጋቱን በዝርዝር ወደመለማመድ ይቀጥላሉ። Stevick (1986) እንደሚስረዱት፣ ገለፃ ተማሪዎች ለሚያነሷቸው ሰዋስዋዊ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠትና ተማሪዎችን ለማገዝ አንዱ መንገድ ነው። ለሳማውም

ተማሪዎች ቋንቋውን ለተግባቦት በሚጠቀሙበት ወቅት ተገቢና ትክክለኛ ቅርፆችን በፍጥነትና በትክክል መምረጥ እንዲችሉ ለመርዳት ነው፡፡ ሆኖም ብቻውን በቂ ባለመሆኑ በበቂ ምሳሌዎች ሊታገዝ ይገባል፡፡

የሰዋስዉ መልመጃዎች ምን አይነት ስነ ትምህርታዊ አደረጃጀት ሊኖራቸው ይገባል? ከአጠቃላይ-ወደ-ዝርዝር ወይስ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ? ይህንን ጉዳይ አስመልክተዉ James እና Grett (1991፣129) እንደገለፁት፣ ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ለተማሪዎች የታላሚዉን ቋንቋ ስርዓት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በመሄድ እንዲያዉቁት የሚያግዙ መሆን አለባቸዉ፡፡ ብዙዎቹ ልማዳዊ የሰዋስዉ አቀራረቦች ቃላት ባላቸዉ መዋቅራዊ ግንኙነቶች ላይ ማጠቃለያዎች መስጠትን ያስቀድማሉ:: በመሆኑም ተማሪዎቹ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር መሄድ ይጠበቅባቸዋል ማለት ነዉ፡፡ ይሁን እንጅ ተማሪዎች የዉጭ ቋንቋ ትምህርት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ሲቀርብላቸዉ እርግጠኛ ካለመሆን የመነጩ ሁለት ችግሮች ወዲያዉኑ ይገጥሟቸዋል:: ከነዚህም ውስጥ ቃላት በህጎች እንዴት በእርግጠኝነት ይገዛሉ? እና ህጎች እርስ በርሳቸዉ መስተጋብር የሚፈጥሩት እንዴት ነዉ? የሚሉት ናቸዉ፡፡ በተቃራኒዉ ሌሎች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሚቀጥሉ ሲሆኑ ቃላትን በተገቢዉና በትክክለኛዉ ስነ-አገባባዊና ስነ-ፍቻዊ መንገድ የማደራጀት ችግሮች ያሉባቸዉ ሆነዉ ይገኛሉ፡፡ በዚህም ምክንያት ሁለቱም ከአጠቃላይ-ወደ-ዝርዝር እና ከዝርዝር-ወደ-አጠቃላይ አቀራረቦች የተማሪዉን የተንታኝነትና የስልጠት ብቃቱን ለማዳበር ሚና ይኖራቸዋል ማለት ይቻላል፡፡ ተማሪዎች ስለታላሚዉ ቋንቋ ልዩልዩ መረጃ ያስፈልጋቸዋል፡፡

ከገለፃዎቹ መረዳት እንደሚቻለው ከሁለቱ አደረጃጀቶች ማለትም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አንደኛው የተሻለ ነው:: ሌላኛው አይደለም ብሎን ማበላለጥ የሚቻል አይደለም፡፡ ምክንያቱም ሁለቱም አደረጃጀቶች ጠቀሜታዎች ያሏቸውና አንደኛውን የአደረጃጀት ስልት ብቻ መጠቀሙ በቂ ባለመሆኑ ነው፡፡በመሆኑም በቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ ሰዋሰዋዊ ይዘቶች ሲደራጁ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ስልቶችን መጠቀም ተገቢ ይሆናል ማለት ነው፡፡

### 2.4.2.4 ውጤት ተኮርና ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ

እንደ Batstone (1994፣51) እንደገለጹት፣ ውጤት ተኮር አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው በታላሚው ቋንቋ መዋቅር ዙሪያ ባለው የቋንቋው ቅርጽ ላይ ነው። በመማር ማስተማሩ ሂደት ሁለት ቁልፍ ደረጃዎችን ማለፍ ያስፈልጋል። የመጀመሪያው አዲሱን የቋንቋ ግብዓት መገንዘብ ሲሆን ዋና አላማውም

### 2.5 የስነ ትምህርታዊ ሰዋስው መገለጫዎች

የስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው አጠቃላይ መገለጫዎችን Nagyne (2006፣93) እንደሚከተለው አስቀምጠዋቸዋል፤

- ❖ ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ገላጭ ሰዋስውን መሰረት አድርጎ በተደጋጋሚ አገልግሎት ላይ የሚውሉ የቋንቋ መዋቅሮችንና ቅንጣቶችን ማካተት ይኖርበታል፤
- ❖ የስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ትኩረት ለተማሪዎቹ አዲስ ወይም ከባድ ሲሆኑ በሚችሉ መዋቅሮችና ፍቺዎቻቸው ላይ መሆን ይኖርበታል፤
- ❖ ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ለኢ አፍ ፈት ተማሪዎች ሲዘጋጅ ስለ ቋንቋው ሰዋስው በለመዱ እውቀት ካካበቱት (አፍ ፈት ተማሪዎች) ከሚዘጋጀው በላይ የሆነ ገለፃን መስጠት ይኖርበታል። በዚህም ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ሲዘጋጅ አፈ ፈትና ኢ አፈ ፈት ተማሪዎችን ታሳቢ በማድረግ ይሆናል ማለት ነው፤
- ❖ ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ከአገባብ ደረጃ በላይ በመሄድና ተግባቦታዊ አላማዎችን ለማሳካት ፍቺንና አጠቃቀምንም ማካተት አለበት፤
- ❖ በጣልቃ ገብነት ሊፈጠሩ የሚችሉ እክሎችን ለማስወገድ ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ተነፃፃሪ ምልአቶችንም (elements) ሊያካትት ይችላል።በዚህም ምክንያት ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ልሳነ ክልኤ ሊሆን ይችላል፤
- ❖ በስነ ትምህርታዊ ሰዋስው የሚካተቱ ሰዋስዋዊ ህጎች (rules) አደረጃጀት ተግባራዊ (empirical) ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በመሆን አለበት እንጂ ጎድፉ ሐሳባዊ (theoretical) መሆን የለበትም። መነሻው በጽሑፍ ወይም በዲስኩር ደረጃ ይሆናል፤

* በስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ውስጥ የሚገኙ ስያሜዎች የተማሪውን ደረጃና ዳራ ያገናዘቡ መሆን ይኖርባቸዋል (Nagyne,2006,93)።
* ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ወቅታዊና የተሻሻሉ የቋንቋ ማስተማር፣የይዘት አቀራረብ፣የይዘት አደረጃጀትና የመሳሰሉ ጉዳዮችን ከግምት በማስገባት ይዘጋጃል (Bygate and et.al.,1994፣33)።

የስነ ትምህርታዊ ሰዋስውን ምንነት፣ጠቀሜታ፣መገለጫዎችና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን እስካሁን ከቀረቡ ገለፃዎች ተመልክተናል። ከነዚህ ገለፃዎች በመነሳትም ከዚህ ጥናት ትኩረት ጋር በሚዛመድ ሁኔታ የስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ስነ ልቦናዊ፣ስነ ትምህርታዊና ስነ ልሳናዊ ንድፈ ሐሳቦች በመማሪያ መፃሕፍት ውስጥ ሰዋስውን ለማስተማር በሚቀርቡ ይዘቶች ላይ እንዴት ሊተረጎሙ እንደሚችሉ ቀጣዩን ጠቅለል ያለ ገለፃ መስጠት ይቻላል።

ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው በመማሪያ መፃሕፍት ውስጥ በሚገኙ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ላይ ከሚተረጎምባቸው ሁኔታዎች ውስጥ የታላሚው ቋንቋ መዋቅሮች ይገኙበታል።ይኸውም ሰዋስዋዊ ህጎች የተማሪውን ትምህርታዊ ዳራ ያገናዘቡ፣ ትክክለኛ፣ ግልፅና ጠቃሚ፣ የቋንቋውን ልዩ ልዩ ክፍሎች አመጣጥነው የሚያቀርቡ፣ አንድን ሰዋስዋዊ ይዘት በተለያዩ ክፍሎች ስፋትና ጥልቀት እየጨመረ በሚሄድ ሁኔታ በመደጋገም የሚያቀርቡ መሆን ይኖርባቸዋል።

ቀደም ሲል የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትን ስርዓት ተኮርና ተግባቦታዊ ተብለው ተከፍለዋል። ከስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ንድፈ ሐሳባዊ ጥቆማዎች አንጻር የትኞቹ የተሻሉ ናቸው? መልሱ የሚሆነው የስነ ትምህርታዊ ሰዋስው መገለጫ የሰዋስው ትምህርት የታላሚውን ቋንቋ ትክክለኛ ሰዋስዋዊ ስርዓት በመጠቀም ተግባቦት ላይ መድረስ በመሆኑ የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ለቋንቋው ቅርጽና በቅርጹ ለሚኖረው ተግባቦት ለሁለቱም ትኩረት የሚሰጡ መሆን ይኖርባቸዋል። ከዚህም በተጨማሪ በመርሃ ትምህርቱ ላይ የተመሰረቱ መሆን ይኖርባቸዋል። እነዚህ ጉዳዮችም የዚህን ጥናት ተተኳሪ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት ሰዋስዋዊ ይዘቶች የሚገመገሙባቸው ነጥቦች መካከል ዋነኞቹ ናቸው።

## 2.6 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚሁ ንዑስ ርዕስ ስር ከዚህ ጥናት ጋር ዝምድና ያላቸውን ቀደምት ጥናታዊ ጽሁፎችን ለመዳሰስ ይሞከራል፡፡ ተስፋዬ በቀለ (1993) "በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ለስምንተኛ ክፍል አማርኛ ኢ. አፈ.ፊት ተማሪዎች በተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ግምገማ" በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ ጥናቱ በመጽሀፉ ላይ ግምገማ ያካሄደው ከሁለት አብይ ጥያቄዎች አንጻር ነው፡፡ አንደኛው በመጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች ለቋንቋው ቅርጻዊ ስርዐትና ፍቺ ትኩረት መስጠት አለመስጠታቸውን ይጠይቃል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የመልመጃዎቹን አደረጃጀት የሚመለከት ነው፡፡ በዚህም መሰረት የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎቹ ለቋንቋው ቅርጻዊ ስርዓት እንጂ ለፍቺ ትኩረት አለመስጠታቸውን፣ ከጥቅል ሰዋስዋዊ ባህሪያቸው ወደ ዝርዝር አለመደራጀታቸውን፣ ለገለጻዊ የግብዓት ማቅረቢያ ስልት ትኩረት አለመስጠቱንና ግብዓቱን በግልጽ የማያሳዩ ጥያቄዎች መቅረባቸውን ለማየት ችሏል፡፡ ተስፋዬ ግኝቶቹን መሰረት በማድረግ ችግሮች የሚስተካከሉባቸውን የመፍትሄ ሃሳቦች አስፍሯል፡፡

በማስከተል ሁሉባንተ አደመ (1994) ‹‹በአማራ ክልል የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛው እርከን ለሚገኙ ተማሪዎች በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ›› ያቀረበውን ጥናት እናገኛለን፡፡ጥናቱ ዓላማ ያደረገውም በመማሪያ መፃሕፍቱ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ቁዘቶችን አቀራረብና አደረጃጀት መገምገም ነው፡፡ ግምገማውን መሰረት በማድረግም በመማሪያ መፃህፍቱ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ግልፅነት እንደሌላቸው፣ ከተማሪዎች ልምድና ችሎታ ጋር እንዳልተጣጣሙ፣ ከየሰዋስው ክፍሉ ተመጣጥነው እንዳልቀረቡ እንዲሁም አደረጃጀታቸው ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት/ቀጣይነት/ እንደሌላቸው ገልጿል፡፡ በመጨረሻም ድክመቶቹ ሊስተካከሉ የሚችሉበትን የበኩሉን የመፍትሔ ሐሳቦች አስፍሯል፡፡

ነብዩ ሰለሞን (1996) ‹‹በኦሮሚያ ክልል በአማርኛ አፍ ፈት ለሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ተማሪዎች በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ወስጥ የሰዋስዉ አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ››፣ የነብዩ ጥናት አላማ አድርጎ የተነሳው በመማሪያ መፃሕፍቱ ውስጥ

ተካተው የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶችን አደረጃጀት ከተከታታይነት፣ ቀጣይነት፣ ከዝርዝር ወደአጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት አንጻር ለመመርመር እንዲሁም የይዘቶቹን አቀራረብ ከግልጽነት፣ ከትክክለኝነት፣ ከተመጣጣኝነት/ሚዛናዊነት ለመፈተሽ ነው። በግምገማውና ፍተሻው መሰረትም በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱ ለዋሰው ትምህርት ይዘቶች በብዛኛው ግልፅነት እንደሚስተዋልባቸው፤ መማሪያ መፃሕፍቱ ከስነ ድምፅ፣ ከስነ ምዕላድ፣ከስነ አገባብና ከስነ ፍቺ የሰዋሰው ክፍሎች የተውጣጡ ይዘቶችን ቢያቀርቡም ሚዛናዊነት እንደሚጎድላቸው፤ በተጨማሪም ከዘመናዊ የአማርኛ ሰዋሰው አንፃር ስህተት የሆኑ ሰዋሰዋዊ ይዘቶችን መቅረባቸውን ገልጿል። በመጨረሻም የተገለፁ ችግሮች ሊስተካከሉ የሚችሉባቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች አስቀምጧል።

ሌላው ጌታቸው ተፈራ (1995) ለሁለተኛው እርከንና ለመሰናዶው እርከን በተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መፃሕፍት የስነ-ልሳን ትምህርት አቀራረብና ድረጃ ግምገማ›› ሲሆን፤ ጥናቱ አላማ አድርጎ የተነሳው በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ለስነ-ልሳን ማስተማሪያነት የዋሉ ይዘቶችና አቀራረባቸው ተማሪዎች ስነ-ልሳናዊ እውቀታቸውን ሊያዳብሩ በሚያስችል ስልታዊ ምጣኔ መቅረባቸውን መመርመር ነው።በጥናቱ ግኝት መሰረትም የ 9ኛ፣ የ 10ኛና የ 11ኛ ክፍሎች መፃህፍት ውስጥ የቀረቡ የስነ-ልሳን ይዘቶች ተጠየቃዊ ግንኙነት ባለው ሁኔታ አለመዋቀራቸውን፣ ፍሰታቸውን አለመጠበቃቸውንና ተማሪው ምን ዓይነት ስነ-ልሳናዊ ትምህርት በመማር ላይ እንዳለና እጎለበተ እንደሄደ ለማወቅ በሚያስችል መልኩ አለመደራጀታቸውን ጠቁሟል። በአንፃሩ የ 12ኛ ክፍሉ መፅሐፍ በስነ ልሳን ይዘት አቀራረቡ በብዙ መልኩ አወንታዊ ገፅታው የጎላ መሆኑንም ጠቅሷል።በመጨረሻም ድክመቶች ሊስተካከሉ የሚችሉባቸውን የበኩሉን የመፍትሔ ሐሳቦች አስፍሯል።

የተሰሩ ጥናት የሰዋሰው መልመጃዎችን ፍቺ ተኮርነትና አደረጃጀታቸውን ለመፈተሽ ያለመ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ይመሳሰላል። ሆኖም ጥናቱ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የተዘጋጀውን የስምንተኛ ክፍል መፅሐፍ የሚመለከት ሲሆን ይህ ጥናት ግን በአገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀውንና የ 12ኛ ክፍል መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙትን የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች ይመለከታል። ስለዚህ ተተኪሪ ካደረጓቸው ክፍል ደረጃዎች አንፃር ልዩነት አላቸው።

የሁሉባንተ ጥናት ተተኳሪ ካደረገው ርዕሰ ጉዳይ አንፃር ከዚህ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ የሁለቱም ጥናቶች ርእስ ጉዳይ የሰዋስው ትምህርት ነው፡፡ ሆኖም የሁሉባንተ ጥናት በአማራ ክልል የተዘጋጁትንና ከ 5 እስከ 8 ኛ ክፍሎች ያሉትን መፃሕፍት የሚመለከት ሲሆን ይህ ጥናት ግን ለ 12ኛ ክፍል የተዘጋጀውን ይመለከታል፡፡

የነብዩ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ላይ ማተኮሩ ነው፡፡ ሆኖም የነብዩ ጥናት ከ 5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች በተዘጋጀው መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ከመገምገም በተጨማሪ ለየክፍሉ ደረጃ የተዘጋጁትን መርሃ-ትምህርቶች ከመፃሕፍቱ ጋር በማዛመድ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ተተኳሪ ካደረጓቸው የክፍል ደረጃዎች ከመፈተሻ ነጥቦች አንፃር ልዩነት አላቸው፡፡

የጌታቸው ጥናት በ 1992 ዓ.ም ከዘጠነኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል የተዘጋጁትን መፃህፍት የስነ-ልሳን ይዘቶች ይመለከታል፡፡ ይህ ጥናት ደግሞ በ 1997 ዓ.ም ለአስራ አንደኛ ክፍል የተዘጋጀውን የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ይመለከታል፡፡ በመሆኑም ተተኳሪ ርእሰ ጉዳያቸው የሰዋስው ትምህርት መሆኑ ሁለቱም ጥናቶች ተዛማጅ ይሆናሉ፡፡ ሆኖም ጌታቸው ተተኳሪ ያደረጋቸው ከዘጠኝ እስከ አስራሁለተኛ ክፍል ድረስ ያሉትን አራት መማሪያ መፃሕፍት ሲሆን ይህ ጥናት ግን ለአስራ ሁለተኛ ክፍል ደረጃ የተዘጋጀውን ብቻ ይመለከታል፡፡ ስለዚህም ከተተኳሪ መማሪያ መፃህፍት ብዛት አንፃር ልዩነት አላቸው፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት ከምርምር ዘርፎች መካከል አይነታዊ የምርምር ዘዴን (Qualitative Research Method) ሲሆን አቀራረቡ ደግሞ በገላጭ (Discriptive) ስልት ነው። በዚህ ዘዴም ጥናቱ በ 12ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ከስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው አንጻር ፈትሾ የሚገኘውን ውጤት ይዘረዝራል።

### 3.1 የጥናቱ መረጃ ምንጭ

የዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ ምንጮች ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች በ 1998 ዓ.ም ተዘጋጅቶ እያገለገለ ያለዉ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ነው። በሁለተኛ ደረጃ በመማሪያ መፅሐፉ ከሚያስተምሩ የጥናቱ ናሙና መምህራንና መማሪያ መጽሐፉን ካዘጋጁ ባለሙያዎች በቃለ-መጠይቅ አማካኝነት የሚገኙ ምላሾች እንዲሁም የደረጃው ተማሪዎች ለቀረበላቸው የጽሁፍ-መጠይቅ የሚሰጧቸው ምላሾች ናቸው።

### 3.2 የመረጃ መሰብሰቢ መሳሪያ

#### 3.2.1 የሰነድ ግምገማ

በዚህ ጥናት ዉስጥ ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ የሚያገለግለዉ የሰነድ ግምገማ ነዉ። በሰነድነት የሚገመገመዉም ከላይ የተጠቀሰዉ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ናቸው። ግምገማዉ የሚካሄደዉም ስነ-ትምህርታዊ ሰዋስዉን አስመልክቶ በክሰሳ-ድርሳን ላይ በቀረቡ ንድፈ-ሐሳቦች አማካኝነት ነው። በእነዚህ ንድፈ-ሐሳቦች መሰረትም በመማሪያ መፅሀፉ ዉስጥ በተካተቱ የሰዋስዉ ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣ አቀራረብና አደረጃጀት ላይ ፍተሻ ተደርጓል።

#### 3.2.2 ቃለ-መጠይቅ

በቃለ-መጠይቅ መረጃ የሚሰበሰበው ከመማሪያ መጽሐፉ አሻሻዮችና የጥናቱ ናሙና ከሆኑት መምህራን ነው። ለደረጃው መምህራን የቀረበው መጠይቅ 13 መነሻ ጥያቄዎችን ይዟል። ጥያቄዎችም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ ሰዋሰዋዊ

ይዘቶች እንዴት እንደተደራጁና እንደቀረቡ ከመምህራን መረጃ ለማግኘት ያለሙ ናቸው:: ለመማሪያ መጽሀፉ አሻሻዮች የቀረቡ ጥያቄዎች ደግሞ 4 መነሻ ጥያቄዎችን የያዘ ነው:: እነዚህ ጥያቄዎችም የመማሪያ መጽሐፉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከደረጃው መርሃ ትምህርት ጋር ያላቸውን ዝምድና በተመለከተ መረጃ ለማግኘት ሲባል የተዘጋጁ ናቸው:: አዘገጃጀታቸውም ምዕራፍ ሁለት ስር የተካተቱ ንድፈ-ሐሳባዊ ጥቆማዎችን መሰረት በማድረግ ነው::

### 3.2.3 የፅሑፍ መጠይቅ

የጽሁፍ መጠይቅ የቀረበው በአማራ ብሄራዊ ክልል በምዕራብ ጎጃም ዞን በጃቢ ጠህናን ወረዳ በሚገኙት በዳሞት ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ትምህርት ቤት፣ በጅጋ ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ትምህርት ቤት እና በቡሬ ወረዳ በሚገኘው የሽኩዳድ መሰናዶ ትምህርት ቤት ውስጥ ለሚማሩ የ 12ኛ ክፍል ተማሪዎች ነው:: የመጠይቁ ዋነኛ አላማ ከመማሪያ መጽሐፉ በሰነድ ግምገማና ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ የተገኙትን ውጤቶችና የተማሪዎችን ምላሽ በማቀናጀት ገለፃውን አሳማኝ ለማድረግ ነው:: ጥያቄዎቹ የተዘጋጁት ምዕራፍ ሁለት ስር የተካተቱ ንድፈ-ሐሳቦችንና ተዛማጅ ጥናቶችን መሰረት በማድረግ የመማሪያ መፅሐፉን ሰዋስዋዊ ይዘቶች በሚመለከት ተማሪዎች መረጃ ሊሰጡባቸው ይችላሉ ተብለው ነጥቦች ላይ በማተኮር ነው::

## 3.3 የናሙና አወሳሰድ

### 3.3.1 የክልል፣ ዞንና ወረዳ ናሙና አወሳሰድ

የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆነው መማሪያ መፅሐፍ በአገር አቀፍ ደረጃ የሚያገለግል ቢሆንም በጥናቱ ሂደት ውስጥ በነበረው የጊዜና የበጀት እጥረት ምክንያት በአማራ ክልል ብቻ ሲወሰን ተገዷል:: በአማራ ክልል ከሚገኙት ዞኖች ውስጥ የምዕራብ ጎጃም ዞን ተመርጧል:: በዚሁ ዞን ከሚገኙ ወረዳዎች ውስጥ በአመቺ-ነሞና ዘዴ የጃቢ-ጠህናን እና የቡሬ ወረዳዎች ተመራጭ ሆነዋል:: ወረዳዎቹ የተመረጡትም የዚህ ጥናት አቅራቢ በቅርበት ስለሚያውቃቸውና ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃዎችን ለመስጠትና ለመተባበር ዝግጁ የሆኑ መምህራንና የፅሕፈት-ቤት ሰራተኞች ስለተገኙባቸው ነው::

### 3.3.2 የትምህርት ቤቶች ናሙና አወሳሰድ

በናሙናነት በተመረጡት ሁለት ወረዳዎች ውስጥ ሦስት የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ሲሆን በጠቅላይ ንሞና-ዘዴ ሁሉም ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል፡፡

### 3.3.3 የመምህራን ናሙና አወሳሰድ

በዚህ ጥናት ዉስጥ በናሙናነት የተመረጡት መምህራን በናሙናነት በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የአማርኛ ቋንቋን ለአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች በማስተማር ላይ የሚገኙት መምህራን በቁጥር አራት ሲሆኑ በጠቅላይ-ንሞና ዘዴ ሁሉም እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ ይህም የተደረገበት ምክንያት ቁጥራቸው አነስተኛ በመሆኑና ሁሉንም በማሳተፍ በቂ መረጃ ማግኘት ይቻላል በሚል እሳቤ ነው፡፡

### 3.3.4 የአሻሻዮች ናሙና አወሳሰድ

የመማሪያ መጽሐፉን የማሻሻል ሂደት ውስጥ የተሳተፉት ባለሙያዎች በቁጥር አምስት ሲሆኑ (ሁለት አሻሻዮች፣ ሁለት ገምጋሚ እና አንድ አርታኢ) በጠቅላይ የንሞና ዘዴ ሁሉንም ባለሙያዎች የጥናቱ ተሳታፊ ለማድረግ ተሞክሮ ነበር፡፡ ነገር ግን ሁለቱ አሻሻዮች ከአገር እንደወጡ የሚጠቁም መረጃ በመገኘቱ፣ አንድ ገምጋሚ ጡረታ ስለወጡና አሁን ያሉበት አድራሻ ባለመታወቁ እንዲሁም አርታኢዎችም አድራሻቸው ባለመታወቁ ምክንያት በጥናቱ ተሳታፊ አልሆኑም፡፡ በመሆኑም በመፅሃፉ የማሻሻል ስራ ላይ በገምጋሚነት የተሳተፉት አንድ ባለሙያ ብቻ በጥናቱ ውስጥ ተካተዋል፡፡

### 3.3.5 የተማሪዎች ናሙና አወሳሰድ

በናሙናነት በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚማሩ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች በቁጥር 1138 ሲሆኑ ከነዚህም መካከል 114 ተማሪዎች ማለትም (10%) የሚሆኑት የፅሁፍ መጠይቁን እንዲሞሉ ተመርጠዋል፡፡ ከናሙና ተማሪዎች መጠይቁን ሞልተው የመለሱት 110 ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ አራት ተማሪዎች መጠይቁን ሞልተው ስላልመለሱ ከጥናቱ ውጪ ሆነዋል፡፡

## 3.4 የመረጃ አተናተን

ከመፅሃፉ በሰነድ ፍተሻ፣ ከተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ እንዲሁም ከመምህራንና ከመፅሃፉ አሻሻይ ባለሙያ በቃለመጠይቅ አማካይነት ስለመማሪያ መፅሃፉ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ለመፈተሽ የተሰበሰቡት መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡ አተናተኑም ለአካሄድ እንዲያመች በአብዛኛው በመማሪያ መፅሃፉ ውስጥ ከተገኙ መረጃዎች በመጀመር፣ ከመምራንና ከተማሪዎች ከተገኙ መረጃዎች ጋር በማገናኘት፣ ከመፅሃፉ አሻሻይ ባለሙያ ከተገኘው መረጃ ጋርም እንደአስፈላጊነቱ በማጣቀስ ተተንትነዋል፡፡ ባጽሁፍ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች በመቶኛ ስሌት ተጠቃለው፤ በሰነድ ምርመራ የተገኙት ደግሞ በአስረጅነት በመውሰድና በምሳሌነት ከተወሰዱት ጋር የሚመሳሰሉትንም የሚገኙበትን ገጽ በዝርዝር በመጠቆም ቀርበዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃዎች ትንታኔ

በዚህ ክፍል የጥናቱ ተተኳሪ የሆነው የ12ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በክለሳ ድርሳን ከሰፈሩ ንድፈ ሐሳቦች አንፃር ይተነተናሉ። በተጨማሪም ትንተናውን ከመምህራን በቃለ መጠይቅ እና ከተማሪዎች በፅሑፍ መጠይቅ በተገኙ ምላሾች ለማጠናከር ጥረት ይደረጋል። በቅድሚያ ግን ስለመማሪያ መፅሐፉ ውስጣዊና ውጫዊ ገፅታ አጠር ያለ ቅኝት እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 4.1 የመማሪያ መፅሀፉ አጠቃላይ ቅኝት

የመማሪያ መፅሐፉ በሀገር አቀፍ ደረጃ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ምኒስቴር ባለመብትነት በመጀመሪያ በ 1994 ዓ.ም በመቀጠልም በ1998 ዓ.ም እንደገና ተሻሽሎ የተዘጋጀና በንግድ ማተሚያ ድርጅት የታተመ ነው። የሽፋን ቀለሙ ቡኒ ሲሆን በሽፋኑ መሀል ላይም አራቱን የቋንቋ ክሂሎች የሚያሳዩ ስዕሎች ይገኛሉ። የመፅሐፉ ሽፋን በቀላሉ ሊበላሽና ሊቀደድ የሚችል ዓይነት ነው። ምክንያቱም ሽፋኑ ከተራ ካሳስር ወረቀት የተዘጋጀ በመሆኑ ነው። አጥኚው ለጥናቱ በተንቀሳቀሰበት ወቅትም ይህንኑ አስተውሏል። ከመጠን አንፃር ስንመለከት መፅሐፉ 24 ሴንቲ-ሜትር ቁመትና 16 ሴንቲ-ሜትር ወርድ ያለው ሲሆን ክብደቱም ቀላል ነው።

ወደ መፅሐፉ ውስጣዊ ገፅታ ስንዘልቅ የመማሪያ መፅሐፉ የተዘጋጀበት አላማ የደረጃው ተማሪዎች በአራቱ ክሂሎችና በስነ ልሳን እንዲሁም በስነ ፅሑፍ ረገድ ያላቸውን ችሎታ ማሳደግ እንደሆነ የሚገልፅ መረጃ በመግቢያው ላይ ይገኛል። መፅሀፉ ስለተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች የሚያወሱ በዝርውና በግጥም የቀረቡ ምንባቦችን በየምዕራፎቹና ንዑስ ምዕራፎቹ ስር አካቷል። በየምዕራፉ በአብዛኛው በአምስት ክፍሎች የተደለደሉ መልመጃዎች ይገኛሉ። ይኸውም ስባት ምዕራፎች አምስት ክፍሎችን የያዙ ሲሆኑ በመጀመሪያው ክፍላቸው የአንብቦ መረዳት መልመጃዎችን፣ በሁለተኛው ደግሞ የመግባ

መልመጃዎችን፣ በሶስተኛው ክፍል የመናገር፣ በአራተኛው የስነ ፅሑፍና በአምስተኛው የሰዋስው መልመጃዎች ይገኛሉ። ሌሎች አምስት ምዕራፎች አራት ክፍሎች ያሏቸው ሲሆኑ የአንብቦ መረዳት፣ የመፃፍ፣ የመናገርና የሰዋስው መልመጃዎችን በቅደም ተከተል አስቀምጠዋል። ቀሪዎቹ ሁለት ምዕራፎች ባለሶስትና ባለ ስድስት ክፍሎች ናቸው። አተያየባቸው ስንመለከት ለማንበብ በቂ በሆነ መጠን ጎላ ጎላ ብለው የተፃፉ ናቸው። የፊደላት ግድፈት አልፎ አልፎ ይታያል። ከላይ የቀረቡትን ገለፃዎች ጠቅለል አድርጎ ማሳየት ይቻል ዘንድ የሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 1፣ የመማሪያ መፅሐፉ አጠቃላይ ቅኝት

| | |
|---|---|
| የህትመት ዘመን | 1998 |
| የገጾች ብዛት | 166 |
| የምዕራፎች ብዛት | 14 |
| የምንባባት ብዛት | 18 |
| የሰዋስው ትምህርት የቀረበባቸው ምንባባት ብዛት | 14 |
| ዋጋ /በብር/ | 5.20 |

## 4.2 በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ

### 4.2.1 ከግልፅነት አንፃር

በክለሳ ድርሳን ላይ እንደተገለፀው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ጥሩ አቀራረብ አላቸው ከሚያስብሉ ገፅታዎች ውስጥ ግልፅ ሆነው መቅረባቸው ይገኝበታል። ይህ እንዲሆንም የቀረቡ ገለፃዎች፣ ምሳሌዎች፣ ትዕዛዞችና መልመጃዎች ለመረዳት የማያስቸግሩ፣ ግርታን የማይፈጥሩና የማያጠራጥሩ መሆን ይኖርባቸዋል። ከዚህ አንፃር በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆነው መማሪያ መፅሐፍ ምን አይነት ገፅታ እንዳለው ቀጥሎ እንመለከታለን።

በአስራሁለተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ አስር ሰዋስዋዊ ገለፃዎች ቀርበዋል። እነዚህ ሰዋስዋዊ ገለፃዎች ደግሞ የግልፅነት ችግር የሌለባቸው ናቸው ማለት ይቻላል። ሆኖም ግን አልፎ አልፎ ችግሮች ተስተውለዋል።

በመማሪያ መፅሐፉ ገፅ 15 እና 27 ላይ በሚገኙ መልመጃዎች ውስጥ የሚታየው የግልፅነት ችግር ሲሆን እሱንም ቀጥሎ የምንመለከተው ይሆናል።

> የሚከተሉት ቃላት በመደበኛ አፃፃፍ የተፃፉ ናቸው። በስነ ልሳናዊ አፃፃፍ ፅፋችሁ በእያንዳንዱ ቃል ውስጥ የሚገኙትን ድምፀ ልሳናት ብዛት ግለፁ።
>
> | ምሳሌ፦ ቃል | ስነ ልሳናዊ አፃፃፍ | የድምፀ ልሳናት ብዛት |
> |---|---|---|
> | መሬት | ምሀርኤት | 5 |
> | ክበሮ | ክበብዐርአ | 6 |
>
> /ገፅ፡ 15/

> በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን አናባቢ ድምፆች ለይታችሁ አውጡ።
>
> ምሳሌ፦ ከተማ [ክኧትኧምአ]
>
> መረረ [ምኧርኧርኧ]
>
> /ገፅ፡ 27/

ከላይ እንደምንመለከተው የመጀመሪያው አስረጂ መልመጃ ውስጥ ቃላት በስነ ልሳናዊ አፃፃፍ እንዴት እንደሚፃፉ ለማሳየት በቀረቡት ምሳሌዎች ውስጥ ግልፅ ያለመሆን ችግር በጉልህ ይታያል። ይኸውም 'መሬት' የሚለው ቃል በስነ ልሳናዊ አፃፃፍ ሲፃፍ [ምኧርኤት] መሆን ሲገባው [ም_ኧርኤት] ተብሏል፤ 'ከበሮ' የሚለው ቃል ደግሞ [ክኧብኧርኦ] መሆን ሲገባበት [ክ ብ ርኦ] ተብሎ ተፅፏል። በመጀመሪያው አስረጂ ምሳሌ 1. ላይ በመጀመሪያው አናባቢ [ኧ] ቦታ ላይና በሁለተኛው ምሳሌ በመጀመሪያና በሁለተኛ አናባቢዎች ቦታ ማስቀመጥ በ [ኧ] መሞላት በሚገባቸው ቦታዎች ላይ የሚገኙት ትክክለኛ አናባቢዎች ሲሆኑ ይህ ‹‹ ›› ምልክት ነው። ስለተቀየሩ አስረጂ [illegible] ደግሞ መልመጃው [illegible] ውስጥ ያሉትን አናባቢ ድምፆች መለየትን

ይጠይቃል፡፡ የመልመጃውን አሰራር ለማሳየት ከቀረቡት ሁለት ምሳሌዎች ውስጥ ሁለተኛው ምሳሌ በትክክለኛ ስነ-ልሳናዊ ስርዓት የቀረበ ሲሆን የመጀመሪያው ግን ችግር ያለበት ነው፡፡ ይኸውም ‹ከተማ› የሚለው ቃል በስነ-ልሳናዊ አፃፃፍ ሲፃፍ [ክኧትኧምኣ] መሆን ሲገባው [ክኧትኧምአ] ተብሎ ይገኛል፡፡ ይህም በቃሉ መጨረሻ ላይ መኖር የነበረበት አናባቢ [ኣ] መሆን ሲኖርበት [አ] ሆኖ ይገኛል፡፡ ይህም የወጥነት ችግር ያለበት ምሳሌ ለተማሪዎቹ ግልጽ ያልሆነ ነው፡፡

በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የሚገኙ ሰዋስዋዊ ገለፃዎች (ማስታዎሻዎች) ምን ያህል ግልፅ ናቸው? በሚል ቃለ-መጠይቅ ከተደረገላቸው አራት መምህራን ውስጥ ሶስቱ፣ ማስታዎሻዎቹ በግልፅ የተቀመጡና ተማሪዎቹ ሊረዷቸው የሚችሏቸው መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡ አራተኛዋ መምህርትም በተመሳሳይ የማስታዎሻዎቹን (ገለፃዎቹን) ግልፅ መሆን ካስረዱ በኋላ፣ በማስታዎሻዎቹ ውስጥ የጎላ የሚባል የግልፅነት ችግር እንዳላስተዋሉና አንዳንድ ችግሮች ቢኖሩም በትምህርቱ ሂደት ውስጥ ችግር ሳይፈጥሩ የሚስተካከሉ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

ከመምህራኑ በተጨማሪ በዚህ ጥናት ተተኳሪ በሆነው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ የሚማሩ የ 12ኛ ክፍል ተማሪዎች ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ለቀረበላቸው የፅሑፍ መጠይቅ እንደሚከተለው መልስ ሰጥተዋል፡፡

ሰንጠረዥ 2፣ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ስለተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ገለፃዎች/ማስታዎሻዎች/ ግልጽነት ለቀረበው ጥያቄ ተማሪዎች የሰጡት መልስ፡፡

| ተቁ. | ጥያቄ | ብዛት | አማራጭ መልሶች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ገለጻዎች /ማስታዎሻዎች/ ግልጽ ናቸው፡፡ | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| | | በቁጥር | 7 | 92 | -- | 11 | -- |
| | | በመቶኛ | 6.4% | 83.6 % | -- | 10 % | -- |

ከስንጠረገዩ መረዳት እንደሚቻለው መጠይቁን ሞልተው ከመለሱ 110 ተማሪዎች ውስጥ 99ኞቹ (90%) አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 92 ተማሪዎች በሰዋስዋዊ ማስታዎሻዎቹ ግልፅነት እስማማለሁ በማለት ሲመልሱ፣ 7ቶቹ(6.4%) ደግሞ በጣም እስማማለሁ በማለት መልሰዋል። ቀሪዎቹ 11 (10%)ተማሪዎች አልስማማም በማለት የመለሱ ናቸው።

የሰነድ ፍተሻው ውጤት፣ የመምህራን ቃለ-መጠይቅ ምላሽና የተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ ምላሽ የሚያሳየውም የመማሪያ መፅሐፉ ሰዋስዋዊ ገለፃዎች በግልፅ የቀረቡ መሆናቸውን ነው።

የሰዋስዋዊ ይዘቶችን ግልፅነት በማስመልከት ፍተሻ ከሚደረግባቸው ይዘቶች ውስጥ የመልመጃዎች ትዕዛዛት ይገኙበታል። በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የሚገኙ ሰዋስዋዊ መልመጃዎች የየራሳቸው ትዕዛዛት ቀርበውላቸዋል። እነዚህ ትዕዛዛትም ተማሪዎቹ ምን መስራት እንዳለባቸው የሚያሳዩ ናቸው። ከግልፅነት አንፃርም ተማሪዎቹ ምን መስራት እንዳለባቸው ግልፅ መልዕክትን የሚያስተላልፉ ናቸው ማለት ይቻላል። ይሁንና በገፅ፣18 ላይ ለሚገኝ መልመጃ የቀረበው ትዕዛዝ ግልፅ ያለመሆን ችግር የሚታይበት ነው። ይኸውም ‹‹በመካነ ፍጥረታቸው አንድ አይነት የሆኑ ግን የተለያዩ ከአምስት ያላነሱ ድምፆችን በመሰብሰብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።›› የሚል ነው። መልመጃው የቀረበው የተናባቢ ድምፆችን ባህርየ-ፍጥረትና መካነ-ፍጥረት ለማስረዳት የቀረቡ ማስታዎሻዎችን ተከትሎ በመሆኑና ብዙ ጊዜ በመካነ ፍጥረታቸው የሚገለጹ ድምጾች ተናባቢዎች በመሆናቸው እንዲሰበስቡ የተፈለጉት ድምፆች ተናባቢዎች ሊሆኑ ይችላሉ ብሎ መገመት ይቻላል። ይሁን እንጅ የመልመጃው ትዕዛዝ የሚሰበሰቡት ድምጾች አናባቢ ወይም ተናባቢ በማለት ለይቶ አለመቀመጡ ለደረጃው ተማሪዎች ግልፅ ላይሆን ይችላል።

የሰዋስዋዊ መልመጃዎች ትዕዛዞችን ግልፅነት አስመልክቶ መምህራን ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ የሰዋስዋዊ መልመጃ ትዕዛዞች በሁሉም የሰዋሰው መልመጃዎች ውስጥ የቀረቡና በግልፅ የተቀመጡ መሆናቸውን ያስገነዝባል። ከዚህ ጋር በተያያዘ

የፅሑፍ መጠይቅ የቀረበላቸው የደረጃው ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 3፣ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ስለተካተቱት የሰዋስው መልመጃ ትዕዛዞች ግልጽነት ለቀረበው ጥያቄ ተማሪዎች የሰጡት መልስ።

| ተቁ. | ጥያቄ | ብዛት | አማራጭ መልሶች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው መልመጃ ትዕዛዞች ግልጽ ናቸው። | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| | | በቁጥር | 15 | 95 | -- | -- | -- |
| | | በመቶኛ | 13.6 % | 86.4 % | -- | -- | -- |

ከሠንጠረዡ እንደተመለከትነው መጠይቁን ሞልተው የመለሱ 110 ተማሪዎች በሙሉ (100%) አዎንታዊ ምላሽ በመስጠት ትዕዛዛቱ ግልፅ ናቸው የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። 95 (86.4%) ተማሪዎች እስማማለሁ በማለት የመለሱ ሲሆን 15ቱ (13.6%) ደግሞ በጣም እስማማለሁ በማለት የመለሱ ናቸው። ይህም የመማሪያ መፅሐፉ ሰዋሰዋዊ መልመጃዎች የያዟቸው ትዕዛዞች ግልፅ መሆናቸውን ያሳያል።

### 4.2.2 ከትክክለኛነት አንፃር

በክለሳ ድርሳን ላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ትክክለኛነት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የታላሚውን ቋንቋ ትክክለኛ ስነ-ልሳናዊ ባህርይ የሚያሳዩ እንዲሆኑ የሚጠቁም ንድፈ-ሐሳብ ነው። ይዘቶቹ ለተማሪዎቹ ስህተት የሚያስተምሩ እንዳይሆኑ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። በማስከተል በዚህ ጥናት ውስጥ ተተኳሪ የሆነው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ከዚህ ንድፈ-ሐሳብ አንፃር ምን አይነት ገፅታ እንዳለው እንመልከት።

በዚህ ጥናት ተተኳሪ በሆነው የአስራ ሁለተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የታላሚውን ቋንቋ ትክክለኛ ስነ-ልሳናዊ

ባህርይ ከማሳየት አንፃር ጥሩ መሆናቸው በሰነድ ፍተሻው ተስተውሏል። ስህተት በሆነ ሰዋሰዋዊ መዋቅር የቀረበ ይዘትም አልተገኘም።

ከሰነድ ፍተሻው በተጨማሪ መምህራን በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ተካትቱት ሰዋስዋዊ መዋቅሮች ምን ያህል ትክክለኛ ናቸው? በሚል ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የሰጡት ምላሽም መማሪያ መፅሐፉ ትክክለኛውን የአማርኛ ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ቅርፅ ከማቅረብ አንፃር ጠንካራ ገፅታ እንዳለው የሚያሳይ ነው። ይኸውም ሁለቱ መምህራን በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የተካተቱት ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች ከአማርኛ ሰዋስው አንፃር ትክክለኛ የሆነ ሰዋሰዋዊ ቅርፅን ይዘው መቅረባቸውን ሲገልፁ አንዱ መምህርም በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ አልፎ አልፎ ግድፈት እንጅ ሰዋሰዋዊ ስህተት እንዳላስተዋሉ ገልፀዋል።

በአጠቃላይም የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆነው የ 12ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ሰዋሰዋዊ ይዘቶች ትክክለኛ የሆነውን የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስዋዊ ቅርፅ ከማሳየት አንፃር ጥሩ ገፅታ ይዘው ተገኝተዋል።

### 4.2.3 ከተመጣጣኝነት አንፃር

በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ተካተው የሚቀርቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከታላሚው ቋንቋ ልዩ ልዩ ክፍሎች የተውጣጡና ሚዛናዊ መሆን አለባቸው። ለተለየ ትምህርታዊ ግብ ሲባል አንዳንድ ሰዋሰዋዊ ክፍሎች በለጥ ያለ ትኩረት ሊሰጣቸው ይችላል። ሆኖም ግን ሁሉም ሰዋሰዋዊ ክፍሎች በተቻለ መጠን ተመጣጣኝ ስርጭት ሲኖራቸው ይዘቶቹ ሚዛናዊ እንዲሆኑ እገዛ ያደርጋል። ከዚህ ንድፈ ሐሳብ አንፃር የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆነው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ምን አይነት ገፅታ እንዳለው በማስከተል ለመፈተሽ ይሞከራል። በቅድሚያ ግን ስለመፅሐፉ የሰዋስው ይዘቶች ስርጭት ሁኔታ የሚገልፅ አንድ አጠቃላይ ሰንጠረዥ ቀጥሎ ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 4፣ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችና የስርጭት ሁኔታ

| የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ክፍሎች | የሰዋስዋዊ ክፍሎቹ የድግግሞሽ መጠን በቁጥር |
| --- | --- |
| ስነ ድምፅ | 15 |
| ስነ ምዕላድ | 15 |
| ስነ አገባብ | 7 |
| ስነ ፍቺ | 14 |
| ጠቅላላ ድምር | 51 |

በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆነው የአስራ ሁለተኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ አራቱንም የሰዋስው ትምህርት ክፍሎች አካቶ ይዟል። መፅሐፉ ከስነ ድምፅ፣ ከስነ ምዕላድ፣ ከስነ አገባብና ከስነ ፍቺ የተውጣጡ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን አካቷል። አራቱ የሰዋስው ትምህርት ክፍሎች በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ያላቸውን የስርጭት መጠን ስንመለከት ተመጣጣኝነት የሚታይባቸው ናቸው። የስነ ድምፅና ስነ ምዕላድ መልመጃዎች እያንዳንዳቸው አስራአምስት ጊዜ ተደጋግመው የቀረቡ ሲሆን ስነ ፍቺ ደግሞ አስራአራት ጊዜ ተደጋግሟል። ስነ-አገባብ ሰባት ጊዜ የተደጋገመ ሲሆን ይህም ዝቅተኛው ድርሻ ነው።

ስነ ድምፅን ለማስተማር ከቀረቡት መልመጃዎች ውስጥ አናባቢና ተነባቢ ድምጾችን ከቀረበላቸው ማስተዎሽ በመነሳት ስነ-ልሳናዊ ባህርያቸውን እንዲገልጹ የሚጠይቁ መልመጃዎች ይገኛሉ። የአናባቢ ድምጾችን ባህርያት እንዲገልጹ የሚጠይቁ ሁለት መልመጃዎች በገፅ፣29 እና 41 ላይ የቀረቡ ሲሆን ተናባቢዎቹን እንዲገልጹ የሚጠይቁት ደግሞ አራት ናቸው። እነሱም በገፅ፣ 17፣ 19 እና 41 ላይ የሚገኙ ናቸው። አናባቢና ተናባቢ ድምጾች አንድ ላይ ቀርበው እያንዳንዳቸው እንዲገለጹ የሚጠይቁ ስድስት መልመጃዎች የሚገኙ ሲሆን በገፅ፣15፣ 16፣ 27፣ 28 እና 40 ላይ ይገኛሉ።በአጠቃላይ ስናየውም የአናባቢ ድምጾችን ባህርያት መግለፅ የሚጠይቁ መልመጃዎች ስምንት ሲሆኑ ተናባቢዎች ደግሞ አስር ናቸው። እዚህ ላይ ምንም እንኳን ለተናባቢዎቹ የተሰጠው ትኩረት ከአናባቢዎቹ የሚበልጥ ቢሆንም ተናባቢ ድምጾች ከአናባቢዎቹ ቁጥር የሚበልጡ በመሆናቸው ሚዛናዊ ሆኖ የቀረበ

| የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ክፍሎች | የሰዋስዋዊ ክፍሎቹ የድግግሞሽ መጠን በቁጥር |
|---|---|
| ስነ ድምፅ | 15 |
| ስነ ምዕላድ | 15 |
| ስነ አገባብ | 7 |
| ስነ ፍቺ | 14 |
| ጠቅላላ ድምር | 51 |

በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆነው የአስራ ሁለተኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ አራቱንም የሰዋስው ትምህርት ክፍሎች አካቶ ይዟል፡፡ መፅሐፉ ከስነ ድምፅ፣ ከስነ ምዕላድ፣ ከስነ አገባብና ከስነ ፍቺ የተውጣጡ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን አካቷል፡፡ አራቱ የሰዋስው ትምህርት ክፍሎች በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ያላቸውን የስርጭት መጠን ስንመለከት ተመጣጣኝነት የሚታይባቸው ናቸው፡፡ የስነ ድምፅና ስነ ምዕላድ መልመጃዎች እያንዳንዳቸው አስራአምስት ጊዜ ተደጋግመው የቀረቡ ሲሆን ስነ ፍቺ ደግሞ አስራአራት ጊዜ ተደጋግሟል፡፡ ስነ-አገባብ ሰባት ጊዜ የተደጋገመ ሲሆን ይህም ዝቅተኛው ድርሻ ነው፡፡

ስነ ድምፅን ለማስተማር ከቀረቡት መልመጃዎች ውስጥ አናባቢና ተነባቢ ድምጾችን ከቀረቡላቸው ማስተዎሻ በመነሳት ስነ-ልሳናዊ ባህርያቸውን እንዲገልጹ የሚጠይቁ መልመጃዎች ይገኛሉ፡፡ የአናባቢ ድምጾችን ባህርያት እንዲገልጹ የሚጠይቁ ሁለት መልመጃዎች በገፅ፣29 እና 41 ላይ የቀረቡ ሲሆን ተናባቢዎቹን እንዲገልጹ የሚጠይቁት ደግሞ አራት ናቸው፡፡ እነሱም በገፅ፣ 17፣ 19 እና 41 ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ አናባቢና ተናባቢ ድምጾች አንድ ላይ ቀርበው እያንዳንዳቸው እንዲገልጹ የሚጠይቁ ስድስት መልመጃዎች የሚገኙ ሲሆን በገፅ፣15፣ 16፣ 27፣ 28 እና 40 ላይ ይገኛሉ፡፡በአጠቃላይ ስናየውም የአናባቢ ድምጾችን ባህርያት መግለፅ የሚጠይቁ መልመጃዎች ስምንት ሲሆኑ ተናባቢዎች ደግሞ አስር ናቸው፡፡ እዚህ ላይ ምንም እንኳን ለተናባቢዎቹ የተሰጠው ትኩረት ከአናባቢዎቹ የሚበልጥ ቢሆንም ተናባቢ ድምጾች ከአናባቢዎቹ በቁጥር የሚበልጡ በመሆናቸው ሚዛናዊ ሆኖ የቀረበ

ያስብለዋል። ሲሳው በድምጾች ላይ ከሚከሰቱ ስነ-ልሳናዊ ክስተቶች ውስጥ የሆነውን ድምጸ-ልሳናዊ ሂደትን ለማስተማር የቀረቡ መልመጃዎች የተካተቱ ሲሆን፣ በመማሪያ መፅሐፉ ገፅ፣ 51 ላይ ‹‹በቃላት ቅንጅት ወቅት ወይም በአንድ ቃል ውስጥ ድምጾች በሚፈጥሩት ከትትሎሽ ምክንያት የድምፅ ወይም የንበት ለውጥ የሚታይባቸውን አምስት ቃላት ፅፉችሁ ለጓደኞቻችሁ አቅርቡ›› የሚልና በተመሳሳይ ገፅ ላይ ‹‹የሚከተሉት ቃላት ሲነበቡ ወይም ባሉበት ቅርፅ የሚታይባቸውን የንበት ወይም የድምፅ ለውጦች አስረዱ›› በሚል ትዕዛዝ ስር አስር ቃላት በጥያቄነት ቀርበዋል። በዚህ መልመጃ ውስጥ በጥያቄነት በቀረቡት ቃላት ውስጥ የሚታየው ስነ-ልሳናዊ ሂደት ምስለት ሲሆን ከልዩ ልዩ የምስለት አይነቶች ውስጥ ደግሞ ከናፍራዊነትና ላንቃዊነት ናቸው። ከአስሩ ቃላት ውስጥም ስምንቱ ላንቃዊነት የሚታይባቸው ሲሆኑ ሁለቱ ደግሞ ከናፍራዊነት የሚታይባቸው ናቸው። ስለዚህም መልመጃው ከስነ ድምጸ ልሳናዊ ሂደቶች ውስጥ ከናፍራዊነትና ላኜቃዊነት የተተኮረባቸው ሲሆኑ ከነዚህም ውስጥ ላናዊነት ከፍ ያለ ሽፋን ተሰጥቶታል።

ስነ ምዕላድን ለማስተማር ከቀረቡት መልመጃዎች ውስጥ ነባርና ምስርት ስሞችን እንዲሁም ነባርና ምስርት ቅፅሎችን ለማስተማር የቀረቡት ይገኙበታል። የቅፅሎችንና ስሞችን ነባርነትና ምስርትነት የሚጠይቁ መልመጃዎች ለእያንዳንዳቸው አስር ጥያቄዎችንና ሁለት ምሳሌዎችን ይዘው በገፅ፣ 79 እና 80 ላይ በቅደም ተከተል ይገኛሉ። በዚህም ተመጣጣኝ ሆነው ተገኝተዋል። ከነዚህ መልመጃዎች በማስከተል የሁለቱንም የቃል ክፍሎች አመሰራረት የሚያሳዩ ማስታዎሻዎች ቀርበዋል። ማስታዎሻዎቹን ተከትሎም በገፅ፣ 81 ላይ አስር ስም መስራች ቅጥያዎች የቀረቡ ሲሆን በእያንዳንዱ ስም መስራች ቅጥያ ሶስት ስሞችን እንዲመሰርቱ ይጠይቃል። በተመሳሳይ ገፅ ላይ አምስት ቅፅል መስራች ቅጥያዎች ቀርበው በእያንዳንዱ ሶስት ቅፅሎችን እንዲመሰርቱ ያዝዛል። ይህም ከቅፅሎችና ስሞች ቁጥር አንፃር የተሰጠው ምጣኔ መልካም መሆኑን ያሳያል።

ስነ-አገባብን ለማስተማር በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶችን ስንዳስስም በገፅ፣111 ላይ የቀረበውን መልመጃ እናገኛለን። ይህም መልመጃ ‹‹ብቀረቡ አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ሀረጎችን የሀረግ አይነት ግለፁ›› የሚል ሲሆን አስር

ጥያቄዎችን ያቀፈ ነው። የመልመጃውን አሰራር ለማሳየት አራት ምሳሌዎች የቀረቡ ሲሆን እነዚህም ስማዊ፣ ቅፅላዊ፣ መስተዋድዳዊና ግሳዊ ሀረጎችን በቅደም ተከተል የሚያሳዩ ናቸው። ተውሳከ-ግሳዊ ሀረግ በምሳሌነት አልቀረበም። ጥያቄዎቹም አንድ መስተዋድዳዊ ሀረግ፣ አራት ስማዊ ሀረግ፣ ሁለት ቅፅላዊ ሀረግ፣ አንድ ግሳዊ ሀረግና ሁለት ተውሳከ-ግሳዊ ሀረጎች የቀረቡባቸው ናቸው። እዚህ ላይ የምናስተውለው የሚዛናዊነት ችግር በምሳሌነት ያልቀረበው ተውሳከ-ግሳዊ ሀረግ ሁለት ጊዜ በጥያቄነት ሲቀርብ በምሳሌነት የቀረቡት ግሳዊ ሀረግና መስተዋድዳዊ ሀረግ አንድ ጊዜ ብቻ መቅረባቸው ነው።

በመማሪያ መፅሐፉ ገፅ፣144 ላይ ‹‹የተሰጡ ቃላትን መሪ በማድረግ ውስብስብ ሀረግ መስርቱ።›› በሚል መልመጃ ስር አስር ቃላት ቀርበዋል። ከነዚህ አስር የሀረግ መሪ ቃላት ውስጥ ስድስቱ ስሞች ሲሆኑ አራቱ ደግሞ ግሶች ናቸው። በዚህ መልመጃም ቀሪዎቹ ሶስት የሀረግ አይነቶች ትኩረት እንዳልተደረገባቸው መረዳት ይቻላል።

የሰዋስዋዊ ማስታዎሻዎችን (ገለፃዎችን) የስርጭት ሚዛናዊነትስንመለከት በመማሪያ መፅሐፉ የስነ-ድምፅ ክፍል ስር አራት ሰዋስዋዊ ማስታዎሻዎች የቀረቡ ሲሆን እነዚህም በገፅ፣ 17 ላይ የተናባቢዎች መካነ-ፍጥረት፣ በገፅ፣ 18 የተናባቢዎች ባህርየ-ፍጥረት፣ አናባቢ ድምጾች ገፅ፣ 28 እና ድምጾችና የንበት ለውጥ በገፅ፣ 50 ላይ የሚገኙ ናቸው።

በስነ-ምዕላድ ክፍሎች ውስጥም የርባታ ቅጥያ ገፅ፣ 61፣ ስም ምስረታ ገፅ፣ 79፣ ቅፅል ምስረታ ገፅ፣ 80 እና የምስረታ ቅጥያ በገፅ፣ 82 ላይ የሚገኙ ሲሆን በድምሩም አራት ናቸው።

ስነ-አገባብን ለማስተማር በተካተቱት ይዘቶች ስር የሀረግ አወቃቀር በሚል የቀረበ ማስታዎሻ በገፅ፣ 110፣ አረፍተ-ነገር በገፅ፣ 142 እና የአረፍተ-ነገር አይነቶች በገፅ፣ 154 የሚገኙ ሲሆን ቁጥራቸውም ሶስት ነው። በአጠቃላይ ሲታይም ሰዋስዋዊ ገለፃ ለማቅረብ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የተካተቱት ማስታዎሻዎች ሲተለያዩ የቋንቋው ክፍሎች ከሞላ ጎደል በተመጣጣኝ ቁጥር ተሰራጭተው የሚገኙ ናቸው ለማለት የሚያስደፍሩ ናቸው። ይህን እስመልክቶ የመማሪያ መፅሐፉ የሰዋስው ትምህርት

ይዘቶች የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ክፍሎች በተመጣጠነ መልኩ ከማቅረብ አንፃር ያላቸውን ገፅታ እንዴት እንደሚገልፁት መምህራን ቃለ-መጠይቅ ቀርቦላቸዋል፡፡ በቃለ-መጠይቁ የተገኘው ምላሽ እንደሚያሳየውም አንደኛው መምህር በመማሪያ መፅሐፋ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ውስጥ የተወሰነ የሚዛናዊነት ችግር እንደሚስተዋል አስረድተዋል፡፡ ሁለተኛዋ መምህርት ደግሞ ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ ከሚዛናዊነት/ተመጣጣኝነት አንፃር ጥሩ ገፅታ እንዳላቸው ተናግረዋል፡፡ ሶስተኛው መምህር ደግሞ ‹‹የመማሪያ መፅሐፋ ሰዋስዋዊ ይዘቶች የቋንቋውን ልዩ ልዩ ሰዋስዋዊ ክፍሎች ለማካተት የሞከሩና ከስርጭት አንፃርም ሚዛናዊ የሚባሉ ናቸው፡፡›› ካሉ በኋላ የይዘቶቹ ስርጭት ሙሉ በሙሉ ሚዛናዊ ነው ባይባልም አበረታች እንደሆነም ጨምረው ገልጸዋል፡፡ አራተኛው መምህርም ‹‹ይዘቶቹ ከተመጣጣኝነት አንፃር ደህና ናቸው ማለት ይቻላል›› በማለት መልሰዋል፡፡

ከሰነድ ፍተሻው ውጤትና ከመምህራኑ ምላሽ እንደምንገነዘበውም የመማሪያ መፅሐፉ ሰዋስዋዊ መልመጃዎች ልዩ ልዩ ክፍሎችን ተመጣጣኝ በሆነ ስርጭት ከማካተት አንፃር ያላቸው ገፅታ አልፎ አልፎ ከሚስተዋሉ ክፍተቶች በስተቀር በአብዛኛው ጠንካራ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የተካተቱት የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች ለቋንቋው ቅርፅ፣ ፍቺና አጠቃቀም ተመጣጣኝ ትኩረት ከመስጠት አንፃር ያላቸውን ገፅታ ስንመለከት ጉልህ ድክመት ተስተውሎባቸዋል፡፡ ይኸውም በመማሪያ መፅሐፋ ውስጥ ሃምሳ የሚደርሱ ሰዋስዋዊ መልመጃዎች የሚገኙ ሲሆን ቅርፅና ፍቺን አቀናጅተው ያቀረቡት ከአምስት ያልበለጡ መልመጃዎች ብቻ ሆነው በመገኘታቸው ነው፡፡ ሌሎቹ መልመጃዎች በቋንቋው ቅርፅ ላይ ብቻ ያነጣጠሩ ናቸው፡፡ ቅርፅና ፍቺን አቀናጅተው ካቀረቡ መልመጃዎች መካከል በገፅ፣ 70 እና 166 ላይ የቀረቡትን ቀጥሎ እንመልከት፡፡

> በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን ቅጥያ ምዕላዳች ለያታችሁ ፍቻቸውን ግለፁ፡፡
>
> ምሳሌ፡- 1. ፍየሎች     ቅጥያ = /-ኦች/
>
> ፍቺ = አብዢ (ብዙ ቁጥር አመልካች)
>
> 2. ልጅሽ     ቅጥያ = ባለንብረትነትን አመልካች

(የሁለተኛ መደብ አንስታይ ጾታ ነጠላ ቁጥር)

1. አልጋዎች
2. ጫማዋ
3. ነገረችህ

ገፅ፣ 70

... በሚከተሉት ግሶች ውስጥ ያሉትን የባለቤትና የተሳቢ ተውላጠ ስም ወኪል ቅጥያዎችን ለይታችሁ አውጡ።

1. ነገረችህ
2. ገዛሻቸው
3. አስቡት ...

ገፅ፣ 166

ከላይ የቀረቡ አስረጃዎችን እንደምንመለከተው፣ የመጀመሪያው መልመጃ በተሰጡ ቃላት ውስጥ የሚገኙትን ቅጥያ ምዕላዶች መለየትንና ቅጥያ ምዕላዶቹ የያዙትን ፍቺ መግለፅን ይጠይቃል። በዚህም ከቅርፅ በተጨማሪ ፍቺ ላይም ያተኮረ መልመጃ ነው። ሁለተኛው መልመጃ ደግሞ በተሰጡት ቃላት ውስጥ ያሉ የባለቤትና ተሳቢ ወኪል ቅጥያዎችን እንዲለዩ ይጠይቃል። ተማሪዎቹ ወኪል ቅጥያዎቹን ከለዩ በኋላ የባለቤት ወይም የተሳቢ ተውላጠ-ስም ወኪል ቅጥያዎች እያሉ ስለመፈረጅ የቅጥያዎቹን ፍቺ መረዳት የሚጠይቃቸው በመሆኑ፣ ይህ መልመጃ ሰዋስዋዊ ቅርፅን ከፍቺ ጋር አጣምሮ ያቀረበ ነው። ከነዚህ በተጨማሪ ሰዋስዋዊ ቅርፅን ከፍቺ ጋር አቀናጅተው የሚያስማምዱ ሌሎች ሶስት ያህል መልመጃዎችም ይገኛሉ። ይሁንና በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ሃምሳ ሰዋስዋዊ መልመጃዎች የመካተታቸውን ያህል ለጉዳዩ የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑን መረዳት እንችላለን። ከዚህ ጋር በተያያዘ ቃለ-መጠይቅ የቀረበላቸው መምህራን የሰጡት ምላሽ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የተካተቱት ሰዋስዋዊ መልመጃዎች ለታለሚው ቋንቋ ቅርፅ፣ ፍቺና አጠቃቀም ከሰጡት ምጣኔ አንፃር ደካማ እንደሆኑና መልመጃዎቹ በቋንቋው መዋቅራዊ ቅርፅ ላይ ብቻ ያነጣጠሩ መሆናቸውን የሚገልፅ ሲሆን፣ ይኸውም አንደኛው

መምህር ‹‹ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ የቋንቋውን ቅርፅ ብቻ የሚያስተምሩ ናቸው›› ሲሉ፣ ሁለተኛው መምህር ደግሞ ይዘቶቹ ከዚህ አንፃር ትልቅ ችግር ያለባቸው መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ ሶስተኛዋ መምህርት ይዘቶቹ ሰዋስውን በደረቁ የሚያቀርቡ እንጂ ለፍቺና አጠቃቀም ቦታ የሌላቸው መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡ አራተኛው መምህር ደግሞ ‹‹ሰዋስዋዊ መልመጃዎቹ ሰዋስውን የሚተነትኑ እንጅ ከፍቺና አጠቃቀም ጋር አቀናጅተው የሚያቀርቡ አይደሉም›› ብለዋል፡፡ የሰነድ ፍተሻው ውጤትና የመምህራኑ የቃለ-መጠይቅ ምላሽ የሚያስገነዝበንም ይዘቶቹ ለታላሚው ቋንቋ ቅርፅ፣ ፍቺና አጠቃቀም ከሰጡት ትኩረት አንፃር ያላቸውን ደካማ ገፅታ መሆናቸውን ነው፡፡

### 4.2.4 ከተገቢነት አንፃር

በክለሳ ድርሳን ላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተገቢነት አላቸው የሚባለው ከተማሪዎች የክፍል ደረጃና የመስራት አቅም ጋር ሲጣጣሙ፣ በአንድ መልመጃ አንድን ሰዋስዋዊ ቅርጽ ብቻ የሚያስተምሩ፣ የተማሪዎችን ትምህርታዊ ዳራ ያገናዘቡና ለታላሚው ቋንቋ ቅርጽ፣ ፍቺና አጠቃቀም ትኩረት የሚሰጡ ሲሆኑ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆነው የአስራ ሁለተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ምን አይነት ገፅታ እንዳለው ለመመልከት እንሞክር፡፡

በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ለክፍል ደረጃው ተማሪዎች ውስብስብና ለመስራት የሚያስቸግሩ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተካተው አይገኙም፡፡ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የተካተቱ ሰዋስዋዊ ገለፃዎች፣ ምሳሌዎችና መልመጃዎች ተማሪዎች ሊሰሯቸው የሚችሏቸው ናቸው፡፡

በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከአንድ በላይ የሆነ ሰዋስዋዊ ቅርፅን የሚያስኩ አለመሆናቸው ለይዘቶቹ ተገቢነት አንዱ መገለጫ ነው፡፡ ለአስረጂነት ያህልም በመማሪ መፅሀፉ ገፅ፣ 15 ላይ የሚገኘውንና ‹‹የሚከተሉትን ቃላት በስነ-ልሳናዊ አፃፃፍ ፅፉችሁ በአንዳንዱ ቃል ውስጥ የሚገኙትን ድምጸ-ልሳናት ብዛት

ግለፁ፡፡›› ፤ ‹‹የሚከተሉትን ድምፆች ባህርየ-ፍጥረትና መካነ-ፍጥረት ግለፁ፡፡›› ገፅ፣19 ፤ ‹‹ከሚከተሉት ቃላት የርባታ ቅጥያዎችን ብቻ ለይታችሁ አውጡ፡፡›› ገፅ፣ 61 ፤ ‹‹በሚከተሉት አረፍተ-ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ሀረጎች ምን አይነት ሀረጎች እንደሆኑ ግለፁ፡፡›› ገፅ፣ 111 እና ማስታዎሻውን መሰረት በማድረግ ለእያንዳንዳቸው የአረፍተ-ነገር አይነቶች ሶስት ሶስት አረፍተ-ነገሮችን ስሩ፡፡›› ገፅ፣ 154 ወዘተ... መልመጃዎችን ስንመለከት ከአንድ በላይ ሰዋስዋዊ ቅርፅን የሚያሰሩ አይደሉም፡፡ ይህ ገፅታም ከተገቢነት አንፃር የመማሪያ መፅሀፉን ጥሩ ጎን የሚያንፀባርቅ ነው፡፡

የመማሪያ መፅሀፉ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከተገቢነት አንጻር ያላቸውን ገፅታ አስመልክቶ ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸው መምህራን ምላሻቸውን የሰጡ ሲሆን፣ በዚህም የመጀመሪያዋ መምህርት ይዘቶቹ ለደረጃው ተማሪዎች እውቀት ሊያስጨብጡ የሚችሉ፣ የሚመጥኑና በአንድ መልመጃ አንድን ሰዋስዋዊ ቅርጽ ብቻ ለማሰራት የሚያቀርቡ መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡ ሁለተኛው መምህርም ከደረጃው ተማሪዎች ውስጥ የመረዳት አቅም ሊኖር እንደሚችል ጠቁመው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ ከብዙሃኑ ተማሪዎች አንፃር ሲታዩ ተገቢነት ያላቸው ናቸው ብለዋል፡፡ ሶስተኛው መምህርም ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ ከተገቢነት አንፃር ጥሩ ገፅታ እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡ አራተኛው መምህር ደግሞ ‹‹በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የሚገኙትን የሰዋስው ይዘቶች ከደረጃው ተማሪዎች አንፃር ሳያቸው ተገቢ ናቸው፤ አመራረጣቸው ላይም እስማማለሁ›› ብለዋል፡፡

ከተገቢነት ጋር በተያያዘ ከመምህራኑ በተጨማሪ ተማሪዎችም የፅሑፍ-መጠይቅ የቀረበላቸው ሲሆን ምላሻቸውም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ሠንጠረዥ 5፣ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከደረጃው ተማሪዎች የመስራት አቅም ወይም የክፍል ደረጃ ጋር ካላቸው ተመጣጣኝነት አንጻር ለቀረበው ጥያቄ ተማሪዎች የሰጡት መልስ፡፡

| ተ.ቁ. | ጥያቄ | ብዛት | አማራጭ መልሶች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች ከእናንተ/ከ 12ኛ ክፍል ተማሪዎች/ የክፍል ደረጃና የመስራት አቅም ጋር ተመጣጣኝ ናቸው። | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| | | በቁጥር | 4 | 96 | 6 | 4 | -- |
| | | በመቶኛ | 3.6% | 87.3 % | 5.4 % | 3.6 % | -- |

ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው መጠይቁን ሞልተው ከመለሱ 110 ተማሪዎች መካከል 100ዎቹ (90.6%) አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ ሲሆን፣ ከነዚህ ውስጥ 96ቱ (87.3%) እስማማለሁ በማለት መልስ ሲሰጡ፣ 4ቱ (3.6%) ደግሞ በጣም እስማማለሁ ብለዋል። 6 ተማሪዎች (5.4%) መወሰን ያስቸግረኛል በማለት የመለሱ ሲሆን ቀሪ 4 (3.6%) ተማሪዎች ደግሞ አልስማማም የሚል መልስ ሰጥተዋል።

ከሰነድ ፍተሻው ውጤት፣ ከመምህራኑ የቃለ-መጠይቅ ምላሽና ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ የአብዛኞቹ ተማሪዎች ምላሽ የሚያሳየንም በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከደረጃው ተማሪዎች የመስራት ችሎታ ጋር ተገቢ መሆናቸውን ነው።

ሰዋስዋዊ ይዘቶች የተማሪዎችን የትምህርት ዳራ ያገናዘቡ፣ በውስጣቸው የያዟቸው ተግባራት ተማሪዎችን ስለሚያውቁት ነገር መረጃ እንዲሰጡ ካደረጉ በኋላ አዲስ የሆነውን ትምህርት ማቅረባቸው በክለሳ የይዘቶቹን ተገቢነት የሚያሳይ ገጽታ ነው። ይህም እያንዳንዱን ተማሪ ንቁ ተሳታፊ በማድረግ ትምህርቱን ተግባቦታዊ ለማድረግ አገዛ ያደርጋል። ከዚህ አንፃር የዚህ ጥናት ተተኳሪ የመማሪያ መፅሐፍ የተካተቱትን ሰዋስዋዊ ይዘቶች ለመፈተሽ የተሞከረ ሲሆን በሚከተሉት እንመለከተዋለን።

በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የተካተቱ ልዩ ልዩ የሰዋስው ትምህርት ክፍሎች የደረጃው ተማሪዎች ከሚያውቋቸው ላይ በመነሳት አዲስ የሆነውን ትምህርት የሚያቀርቡ ናቸው ለማለት የሚያስደፍሩ ናቸው። ለዚህም ማስረጃ የሚሆኑት ከመምህራንና ከተማሪዎች የተገኘው ምላሽ ሲሆን ቀጥሎ የምንመለከተው ይሆናል።

በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የተካተቱት ሰዋስዋዊ ይዘቶች፣ ተማሪዎች በቀደሙት ክፍሎች የተዋወቋቸው ናቸውን? በሚል ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸው መምህራን ሲመልሱ፣ በመማሪያ መፅሐፉ ከተካተቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ውስጥ አብዛኞቹ በቀደሙት የክፍል ደረጃዎች ላይ የተዋወቁና አዲስ ያልሆኑ ናቸው ብለዋል፡፡ መምህራኑ አዲስ ሊሆን ይችላል ያሉት ይዘት የድምፆች መካነ-ፍጥረትና ባህርየ-ፍጥረት መሆኑንም ጨምረው ገልፀዋል፡፡ ለቃለ-መጠይቁ ምላሽ ከሰጡ አራት መምህራን መካከል አንደኛው እንደገለፁት ‹‹የተወሰኑ ይዘቶች እንግዳ ቢሆኑም የአብዛኞቹ ይዘቶች አዲስ አለመሆን ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ የመማሪያ መፅሐፉን ጠንካራ ገፅታ አያደበዝዝም፡፡ የተወሰኑ አዲስ ይዘቶችን ማካተት በራሱ አዲስ እውቀትን ከማስጨበጥ አንፃር በበጎነቱ ለጠቀስ የሚችል ነው›› ብለዋል፡፡ ከመምህራን በተጨማሪ ተማሪዎችም የፅሑፍ-መጠይቅ የቀረበላቸው ሲሆን ምላሻቸውም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 6፣ በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የደረጃውን ተማሪዎች ትምህርታዊ ዳራ ከማገናዘብ አንጻር ለቀረበው ጥያቄ ተማሪዎች የሰጡት መልስ፡፡

| ተቁ. | ጥያቄ | ብዛት | አማራጭ መልሶች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን እናንተ/የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች/ ካላችሁበት የክፍል ደረጃ በፊት የተማራችኋቸው ናቸው፡፡ | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| | | በቁጥር | 23 | 81 | 6 | -- | -- |
| | | በመቶኛ | 20.9 % | 73.6 % | 5.4 % | -- | -- |

ከሰንጠረዡ እንደምንመለከተው የፅሑፍ መጠይቁን ሞልተው ከመለሱ 110 ተማሪዎች መካከል 104ቱ (94.5%) ይዘቶቹን ቀደም ባሉት ክፍሎች የተዋወቅናቸው ናቸው በማለት አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ከነዚህ ውስጥ 81ዱ (73.6%) እስማማለሁ በማለት የመለሱ ሲሆኑ 23ቱ (20.9%) ደግሞ በጣም እስማማለሁ ያሉናቸው። ቀሪዎቹ 6 (5.4%) ተማሪዎች ደግሞ አልስማማም በማለት የመለሱ ናቸው። በአጠቃላይም መማሪያ መፅሐፉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች የደረጃውን ተማሪ የትምህርት ዳራ ከማገናዘብ አንፃር ጥሩ ገፅታ ያላቸው ናቸው።

በቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ የሚካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ሲመረጡና ሲዘጋጁ ለክፍል ደረጃው ከተዘጋጀው መርሃ-ትምህርት ጋር የሚጣጣሙና ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል። ይህም የይዘቶቹን ተገቢነት ከሚያሳዩ ገፅታዎች መካከል ዋነኛ መገለጫ በመሆኑ የዚህ ጥናት ተተኳሪ በሆነውና በ1998 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው የ 12ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ከዚህ አንፃር ለመገምገም ተሞክሯል። በዚህም በጣም ጉልህ የሆነ ችግር ለማየት ተችሏል።

መማሪያ መፅሐፉ በመግቢያው ላይ ተሻሽሎ የተዘጋጀውን መርሃ ትምህርት መሰረት እንዳደረገ የሚገልፅ መረጃ ይገኛል። በሰነድ ፍተሻው ወቅት በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ከስነ ድምፅ እስከ ስነ አገባብና ስነ ፍቺ ያለውን የታላሚው ቋንቋ ሰዋስዋዊ ክፍሎች የያዙ ሃምሳ ያህል ሰዋስዋዊ መልመጃዎችን ለማየት ተችሏል። ተሻሽሎ በተዘጋጀው(በ1997 ዓ.ም) በደረጃው መርሃ ትምህርት ላይ የተደረገው ፍተሻ የሚያሳየው ደግሞ በመርሃ ትምህርቱ ገጽ፣ 3-4 ላይ ‹‹የድምፀ ልሳናት አፈጣጠር፣ የድምፀ ልሳናት መካነ ንባብና ባህርየ ንባብ፣ አናባቢ ድምፆች እና ተናባቢ ድምፆች›› ከሚሉት በስተቀር ሌሎች ስለምስረታ፣ ስለ ርባታ፣ ስለ መፅላዶች፣ ሀረጎች፣ አረፍተ ነገሮች ወዘተ... የሚያወሱ ይዘቶች በጥቅሉም ይሁን በዝርዝሩ ያስቀመጠው ነገር የለም። የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆነው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ይህን መርሃ ትምህርት መሰረት ያደረገ ነው የተባለው እንዴት ሆኖ ነው? ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት በመማሪያ መፅሐፉ ዝግጅት ላይ ተሳታፊ የነበሩ ባለሙያዎችን ለማግኘት ቢሞከርም፣ የመማሪያ መፅሐፉ አዘጋጆችም ሆኑ አርታኢው በሀገር ውስጥ የሚገኙ

ስላልሆነ እነሱን የመጠየቁ ሙከራ ሳይሳካ ቀርቷል። ለማግኘት የተቻለው በመማሪያ መፅሐፉ የማሻሻል ስራ ላይ ገምጋሚ የነበሩትንና ተሻሽሎ በ 1997 ዓ.ም በተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ላይ አዘጋጅ ባለሙያ የነበሩትን አንድ ባለሙያ ብቻ ነው። ባለሙያው ችግሮቹን አስመልክቶ ለቀረቡለት ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽም ምክንያታዊነት የጎደለው ሆኖ ተገኝቷል።

የመማሪያ መፅሐፉን ሰዋስዋዊ ይዘቶች ትልቅ ጥያቄ ውስጥ የጨመረው ከላይ የተገለፀው ችግር ሊፈጠር የቻለው ከግዴለሽነትና በመማሪያ መፅሐፉ ዝግጅት ወቅት በነበረው ትልቅ ክፍተት ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል። አዘጋጅ ባለሙያዎቹ በስራው የካበተ ልምድ ያላቸው ናቸው። ባለሙያዎቹ በመማሪያ መፅሀፉ መግቢያ ላይ የተሻሻለውን መርሃ ትምህርት መሰረት አድርገው እንዳዘጋጁት የሚገልፅ መረጃ ማስቀመጣቸው የጉዳዩን አስፈላጊነት ጠንቅቀው በማወቃቸው ነው። መማሪያ መፅሐፉ ከመርሃ ትምህርቱ ምንም ግንኙነት ሳይኖረው ቀርቦ እያለ ‹‹…መርሃ ትምህርቱን መሰረት አድርጓል።›› ብሎ መግቢያው ላይ መፃፉ ለምን ይሆን?

## 4.3 በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት

### 4.3.1 ከተከታታይነት አንፃር

ኝ

በክለሳ ድርሳን ላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ተከታታይነት በአንድ የክፍል ደረጃ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በዛው የክፍል ደረጃ ተደጋግመው መቅረብና ድግግሞሻቸውም ስፋትና ጥልቀት እየጨመረ መሄድ እንዳለበት የሚያሳይ ነው። ከዚህ አንፃር በዚህ ጥናት ውስጥ ተተኳሪ የሆነው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ምን አይነት ገፅታ እንዳለው በማስከተል ለመመልከት እንሞክር። በቅድሚያ ግን በመማሪያ መፅሐፉ ተካተው የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችንና የድግግሞሽ መጠን የሚያሳይ ሠንጠረዥ እንመልከት።

ሠንጠረዥ 7፣ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የድግግሞሽ መጠን

| በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች | ይዘቶቹ የቀረቡበት የድግግሞሽመጠን |
|---|---|
| | በቁጥር |
| ስነ-ድምፅ | |
| ስነ-ልሳናዊ አፃፃፍ | 3 |
| ድምፀ-ልሳናዊ ሂደት | 2 |
| የድምፆች መካነ-ፍጥረትና ባህርየ-ፍጥረት | 8 |
| ንጥረ-ድምፆች | 2 |
| ስነ-ምዕላድ | |
| ቅጥያና የርባታ ምዕላዶችን መለየት | 7 |
| የቃል ክፍሎች | 2 |
| ነባርና ምሥርት ስሞችና ቅፅሎች | 6 |
| ስነ-አገባብ | |
| የሀረግ አይነቶችን መለየት | 3 |
| ሀረግ ምሥረታ | 2 |
| አረፍተ ነገር ምሥረታ | 2 |
| ስነ-ፍቺ | |
| የቅጥያ አፃፋዎች ፍቺ | 2 |
| የቃላት፣ሀረጋትና አረፍተ-ነገሮች አውዳዊ ፍቺ | 12 |

ከቀረበው ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ከተካተቱ ሃምሳ ያህል ሰዋስዋዊ መልመጃዎች ውስጥ የስነ-ድምፅና ስነ-ምዕላድ ይዘቶች እያንዳንዳቸው

አስራአምስት ጊዜ ተደጋግመው የቀረቡ ሲሆን፣ስነ-ፍቺ ደግሞ አስራአራት ጊዜ ተደጋግሟል፡፡ በዝቅተኛ ድግግሞሽ የቀረቡት ደግሞ የስነ-አገባብ መልመጃዎች ናቸው፡፡

በዝርዝር ስንመለከትም ‹‹ቃላትን በስነ-ልሳናዊ አፃፃፍ ፅፋችሁ በእያንዳንዱ ቃል ውስጥ የሚገኙትን ድምፀ-ልሳናት ብዛት ግለፁ፡፡›› የሚል መልመጃ በመማሪያ መፅሐፉ ገፅ፣ 15 ላይ ይገኛል፡፡ ይኸው መልመጃ በዛው ገፅ፣ (15) እና 27 ላይ ለሶስት ጊዜ ተደጋግሞ ቀርቧል፡፡ ሌላው ንጥረ-ድምፆችን የሚያስተምረው መልመጃ ሲሆን፣ ይኸውም ‹‹የሚከተሉት ጥንድ ጥንድ ቃላት የተለያየ ፍቺ እንዲኖራቸው ምክንያት የሆኑትን ድምፆች በቀረቡት ምሳሌዎች መሰረት ለዩ፡፡›› የሚል ሲሆን በገፅ፣ 16 ላይ ይገኛል፡፡ ይህ መልመጃ በገፅ፣ 28 ላይ ተደግሞ ቀርቧል፡፡ በድምፆች መካነ-ፍጥረትና ባህርየ-ፍጥረት ላይ ያተኮረ መልመጃ በገፅ፣ 17 ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ይዘት ለስምንት ጊዜ ተደጋግሞ የቀረበ ሲሆን በገፅ፣ 17፣ 18፣ 19፣ 29፣40 እና 41 ላይ ይገኛል፡፡

በቃላት ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ ቅጥያ ምዕላዶችን ለይቶ ማሳየት ላይ ያነጣጠሩ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ለሰባት ያህል ጊዜ ተደጋግመዋል፡፡ ከይዘቶቹ ውስጥ ‹‹በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን ምዕላዶች ለዩ፡፡›› እና ‹‹ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ የርባታ ቅጥያዎችን ብቻ ለይታችሁ አውጡ፡፡›› የሚሉ ሁለት መልመጃዎች በገፅ፣ 61 ላይ የሚገኙ ሲሆን ሌሎች አምስት መልመጃዎችም በገፅ፣ 70፣ 96 እና 166 ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡ የቃል ክፍሎችን እንዲለዩ የሚጠይቁ መልመጃዎች በገፅ፣ 78 እና 97 ውስጥ ለሁለት ጊዜ ተደግመው ቀርበዋል፡፡ ነባርና መስርት ስሞችን እንዲለዩ የሚያዙ መልመጃዎች ለስድስት ያህል ጊዜ ተደጋግመው የቀረቡ ሲሆን ‹‹ከሚከተሉት ስሞች ነባርና ምስርት ሆኑትን ለዩ፡፡›› የሚለውና ‹‹የሚከተሉትን ቅፅሎች ነባርና ምስርት በማለት ለዩ፡፡›› የሚሉት መልመጃዎች በገፅ፣79 እና 81 ላይ ተከታትለው ቀርበዋል፡፡

የሀረግ አይነቶችን መለየት ላይ ያተኮሩ መልመጃዎ ለሶስት ጊዜ የተደገሙ ሲሆን፣ ከነዚህም ውስጥ ‹‹በሚከተሉት አረፍተ-ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ሀረጎች ምን ዓይነት ሀረጎች እንደሆኑ ግለፁ፡፡›› የሚል መልመጃ በገፅ፣ 111 ላይ ይገኛል፡፡ ሌሎቹ ሁለት መልመጃዎችም በገፅ፣ 143 ላይ ይገኛሉ፡፡

ሀረግ ምስረታን ለማስተማር ሁለት መልመጃዎች የቀረቡ ሲሆን፣ እነሱም ‹‹የሚከተሉትን ቃላት መሪ በማድረግ ሀረግ መስርቱ፡፡›› በገፅ፣111 እና 144 ላይ ቀርበው ይገኛሉ፡፡ አረፍተ-ነገር መመስረትን ለማስተማር የተካተቱ መልመጃዎች ደግሞ ሁለት ጊዜ የቀረቡ ሲሆን፣ እነሱም ‹‹ማስታዎሻውን መሰረት በማድረግ ለእንዳንዳቸው የአረፍተ-ነገር አይነቶች ሶስት አረፍተ-ነገሮችን ስሩ፡፡›› የሚለው መልመጃ በገፅ፣ 154 ላይ ይገኛል፡፡ በዚሁ ገፅ ላይ ‹‹በሚከተሉት አረፍተ-ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን የአረፍተ-ነገር ተዋቃሪዎች በመጠይቃዊ ቃላት ወይም ሀረጋት በመተካት መጠይቃዊ አረፍተ-ነገር መስርቱ፡፡›› የሚል መልመጃ ይገኛል፡፡

በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የስነ-ፍቺ መልመጃዎች በተደጋጋሚ ቀርበዋል፡፡ እነሱም የቃላትን፣ ሀረጋትንና አረፍተ-ነገሮችን አውዳዊ ፍቺ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ በመማሪያ መፅሀፉ ገፅ፣26 ላይ ‹‹ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት ፍቺ ፈልጉላቸው፡፡›› የሚለው የሚገኝ ሲሆን ‹‹በሚከተሉት ሀረጋትና አረፍተ-ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ሀረጋትና ቃላት የያዙትን አውዳዊ ፍቺ ከገለፃችሁ በኋላ ተመሳሳይ ፈልጉላቸው፡፡›› የሚለው ደግሞ ገፅ፣33 ላይ ይገኛል፡፡ ከነዚህም በተጨማሪ በገፅ፣ 75፣96፣123፣138፣141፣149፣151፣152 እና 160 ላይም የስነ-ፍቺ መልመጃዎች ይገኛሉ፡፡

ከላይ ከቀረበው ዝርዝር እንደተመለከትነው መማሪያ መፅሐፉ የቋንቋውን ልዩ ልዩ ክፍሎች በተደጋጋሚ አቅርቧል፡፡ ይህም የይዘቶቹን ጥሩ ገፅታ የሚያሳይ ነው፡፡ ይሁንና አንዳንድ ይዘቶች አነስተኛ በሆነ ድግግሞሽ መቅረባቸው እንደ መጠነኛ ክፍተት የሚታይ ነው፡፡ ባጠቃላይ ሲታይ ግን ከተከታታይነት አንፃር ጥሩ ገፅታ እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡ ይህን አስመልክቶ ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸው መምህራን የሰጡት ምላሽ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ከመምህራኑ ውስጥ አንድኛው የመማሪያ መፅሐፉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች በተለያዩ ክፍሎች ተደጋግመው እንደቀረቡ ከተናገሩ በኋላ ‹‹ሁሉም ይዘቶች በእኩል መጠን ባይደጋገሙም ባጠቃላይ ግን ይዘቶቹ ከተከታታይነት አንፃር መልካም ናቸው›› የሚል ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ ሁለተኛው መምህርም ‹‹አብዛኞቹ ሰዋስዋዊ ይዘቶች በተለያዩ ክፍሎች

ተደጋግመው ቀርበዋል›› በማለት ተመሳሳይ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ሌሎች ሁለት መምህራንም አንድነት ያለው ምላሽ የሰጡ ሲሆን ይኸውም ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ በተለያዩ ክፍሎች ተደጋግመው መቅረባቸውን ነገርግን አንዳንድ ይዘቶች በብዙ ጊዜ የተደጋገሙ ሲሆን አንዳንዶቹ ግን አነስ ባለ ድግግሞሽ የቀረቡ መሆናቸውን የሚገልፅ ነው፡፡ ከመምህራን በተጨማሪ ተማሪዎችም የይዘቶቹን ተከታታይነት በሚመለከት የፅሑፍ መጠይቅ የቀረበላቸው ሲሆን፣ የሰጡት ምላሽም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 8፣ ከመማሪያ መፅሐፉ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተከታታይነት አንጻር ለቀረበ ጥያቄ ተማሪዎች የሰጡት መልስ፡፡

| ተቁ. | ጥያቄ | ብዛት | አማራጭ መልሶች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በተለያዩ ክፍሎች ተደጋግመው ቀርበዋል፡፡ | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| | | በቁጥር | 9 | 101 | -- | -- | -- |
| | | በመቶኛ | 8.2% | 91.8 % | -- | -- | -- |

ከቀረበው ሰንጠረዥ እንደተመለከትነው፣ የፅሑፍ መጠይቁን ሞልተው የመለሱ 110 ተማሪዎች በሙሉ (100%) አዎንታዊ ምላሽ በመስጠት ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ በተለያዩ ክፍሎች ተደጋግመው መቅረባቸውን ገልፀዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ 101ዶቹ (91.8%) እስማማለሁ በማለት የመለሱ ሲሆን 9 (8.2%) ተማሪዎች ደግሞ በጣም እስማማለሁ ያሉ ናቸው፡፡

ከሰነድ ፍተሻው ውጤት፣ ከመምህራን የቃለ-መጠይቅ ምላሽና ከተማሪዎች የፅሑፍ-መጠይቅ ምላሽ መረዳት የምንችለው የመማሪያ መፅሐፉ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከተከታታይነት አንፃር ያላቸውን ጥሩ ገፅታ ነው፡፡

የመማሪያ መፅሐፉን ሰዋስዋዊ ይዘቶች ተከታታይነት ከፈተሸን በኋላ በመቀጠል የምንመለከተው ተደጋግመው የቀረቡ ይዘቶች ስፋትና ጥልቀት እየጨመሩ መሄድ

አስመሄዳቸውን ይሆናል፡፡ የሰነድ ፍተሻው ውጤት እንደሚያመለክተው ተደጋግመው የቀረቡት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ስፋትና ጥልቀት እጨመሩ የሚሄዱ መሆናቸውን ነው፡፡ አስረጂዎችን ቀጥሎ እንመልከት፡፡

በመማሪያ መፅሐፉ ገፅ፣ 15 ላይ በቃላት ውስጥ የሚገኙትን ድምፀ-ልሳናት ብዛት መግለፅ ላይ ያተኮረ መልመጃ ይገኛል፡፡ አቀራረቡም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

የሚከተሉትን ቃላት በስነ-ልሳናዊ አፃፃፍ ፅፉችሁ በእያንዳንዱ ቃላት ውስጥ የሚገኙትን ድምፀ-ልሳናት ብዛት ግለፁ፡፡

| ቃል | ስነ-ልሳናዊ አፃፃፍ | የድምፀ-ልሳናት ብዛት |
|---|---|---|
| መሬት | ምእርኤት | 5 |
| ከበሮ | ክእብእርኦ | 6 |
| ሰላም | | |
| ወረቀት | | |
| ገበሬ | | |

ገጽ፣15

በዚህ መልመጃ ውስጥ ተማሪዎቹ በቀረቡላቸው ምሳሌዎች መሰረት ቃላትን በስነ-ልሳናዊ አጻጻፍ ፅፈው የድምፀ-ልሳናቱን ብዛት ይገልፃሉ፡፡ በዚህ ወቅት ስነ-ልሳናዊ አፃፃፍንም ይሁን ድምፀ-ልሳናትን አስመልክቶ የቀረበ ማብራሪያ ባይኖርም ግንዛቤ የሚጨብጡት በመልመጃው ክንውን ወቅት ነው፡፡ ከዚህ በተለየ አቀራረብ ነገር ግን ተመሳሳይ ይዘት ያለው መልመጃ በገፅ፣15 ላይ የሚገኝ ሲሆን ስነ-ልሳናዊ አፃፃፍን ከማለማመድ በተጨማሪ ስለ ድምፀ-ልሳናት ምንነት በተዘዋዋሪ ግንዛቤ የሚሰጥ ነው፡፡ አቀራረቡን ቀጥሎ እንመልከት፡፡

የሚከተሉትን ቃላት በስነ-ልሳናዊ አጻፃፍ ፅፉችሁ የተናባቢዎችንና አናባቢዎችን ድምፆች ብዛት ለይታችሁ አሳዩ፡፡

ምሳሌ፡- ልብስ = ልእብስ = የተናባቢ ብዛት = 3

የአናባቢ ብዛት = 1

ሌባ = ልኤብኣ = የተናባቢ ብዛት = 2

የአናባቢ ብዛት = 2

ይህኛው መልመጃ ቃላት በስነ-ልሳናዊ አፃፃፍ እንዲፃፉ ብሎም የተናባቢና አናባቢዎች ብዛት እንዲገለፁ ይጠይቃል፡፡ መልመጃው ቀደም ሲል ከቀረበው መሰል መልመጃ ላይ ‹‹ድምፀ-ልሳን›› በሚል የቀረበውን ስነ-ልሳናዊ ስያሜ ምንነት የሚያስገነዝብ አቀራረብን ጨምሮ የያዘ ነው፡፡ ይኸውም ቀደም ባለው መልመጃ ውስጥ ‹‹መሬት›› በስነ-ልሳናዊ አፃፃፍ ከተፃፈ በኋላ የ ምፀ-ልሳናቱ ብዛት አምስት መሆናቸውን ተመልክተናል፡፡ ይህንኑ ቃል በዚህኛው መልመጃ ውስጥ ብናመጣው በስነ-ልሳናዊ አፃፃፍ እንገልፀውና የተናባቢ ብዛት በሚለው ስር ሶስትን እናስቀምጣለን፡፡ የአናባቢ ብዛት በሚለው ስር ደግሞ ሁለትን እናስቀምጣለን፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥም ቀደም ባለው መልመጃ ‹ድምፀ-ልሳናት› የተባሉት በቃል ውስጥ የሚገኙና በስነ-ልሳናዊ አፃፃፍ ወቅት የሚገለፁት አናባቢና ተናባቢ ድምፆች ማለት መሆኑን ተማሪዎቹ ሊገነዘቡት ይችላሉ፡፡ ለዚህም ነው ይህኛው መልመጃ ቀደም ካለው መሰል መልመጃ ጋር ሲነፃፀር ሰፋና ጠለቅ ብሎ የቀረበ ነው የተባለው፡፡

በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የተካተቱ የስነ-ምዕላድ ይዘቶችን ስንፈትሽም ተደጋግመው ሲቀርቡ ጥልቀት እጨመሩ የሚሄዱ መልመጃዎችን እናገኛለን፡፡ ለአስረጂነትም ቀጣዮችን እንመልከት፡፡ በመማሪያ መፅሐፉ ገፅ፣61 ላይ ‹‹በሚከተሉት ቃላት ውስጥ የሚገኙትን ምዕላዶች ለይታችሁ አሳዩ፡፡›› የሚል መልመጃ ቀርቧል፡፡ አቀራረቡም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን ምዕላዶች ለይታችሁ አሳዩ፡፡

ምሳሌ፡- 1. ተሰበረች = ተ- ሰበር -ኧች

2. ልጆቹን = ልጅ -ኦች-ኡ-ን

3. ብልሃተኛነት = ብልህ -ኣት-ኧኛ-ነት

1. ድመቲቱ
2. ስላመማት
3. ሰብሮበታል

ገፅ፣61

በዚህ መልመጃ ውስጥ የተጠየቀው በቃላት ውስጥ የሚገኙትን ምዕላዶች ለይቶ መግለፅ ነው፡፡ ከዚህ መልመጃ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሌላ መልመጃ በገፅ፣ 70 ላይ ቀርቧል፡፡ አቀራረቡም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

በሚከተሉት ቃላት ውስጥ የሚገኙትን ቅጥያ ምዕላዶች ለይታችሁ ፍቻቸውን ግለፁ።

ምሳሌ፡- 1. ፍየሎች = ቅጥያ = /-ኦች/

ፍቺ = አብዢ(የብዙ ቁጥር አመልካች)

2. ልጅሽ = ቅጥያ = /-ሽ/

ፍቺ = ባለንብረትነትን አመልካች

(የሁለተኛ መደብ፣አንስታ ፆታ፣ነጠላ ቁጥር)

3. ወሰደ = ቅጥያ = /-ኧ/

ፍቺ = የአረፍተ-ነገሩን ባለቤት አመልካች

(የ3ኛ መደብ፣ነጠላ ቁጥር፣ተባዕት ፆታ)

4. አስጠረገች = ቅጥያ = /አስ-/ እና /-ኧች/

ፍቺ = /አስ-/ ግሱን አስደራጊ

/-ኧች/ የአ.ነገሩን ባለቤት አመልካች

(የ3ኛ መደብ፣ነጠላ ቁጥር፣ተባዕት ፆታ)

1. አልጋዎች
2. ጫማዋ
3. ነገረችህ

ገፅ፣70

በዚህኛው መልመጃ ተማሪዎቹ በቀረቡላቸው ምሳሌዎች መሰረት ቅጥያ ሆኑ ምዕላዶችን ከየቃሉ ውስጥ ከለዩ በኋላ ፍቻቸውን ይገልፃሉ። መልመጃው ቅጥያዎችን እንዲለዩ ከማድረግ በተጨማሪ የቅጥያዎቹንም ፍቺ እንዲገልፁና ተጨማሪ እውቀትን እንዲያዳብሩ በማድረጉ ቀደም ሲል ከተመለከትነው የዚህ መሰል መልመጃ ሰፋና ጠለቅ ያለ ሆኗል።

የመማሪያ መፅሐፉ የስነ-አገባብ መልመጃዎች ሲደጋገሙ ጥልቀት እዬጨመሩ የሚሄዱ መሆናቸውን ለማሳዬት ቀጣዮቹን አስረጂዎች እንመልከት።

በሚከተሉት አረፍተ-ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ሀረጎች ምን ዓይነት ሀረጎች እንደሆኑ(የሀረግ ዓይነታቸውን) ግለፁ።

መልመጃውን ይሰራሉ ማለት ነው። በመሆኑም መልመጃው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀትን የተከተለ ነው።

ሌላው በመማሪያ መፅሀፉ ገፅ፣61 ቁጥር፣1 ላይ የቀረበው መልመጃ ሲሆን፣ ይኸውም ‹‹በሚከ ሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን ምዕላዶች ለይታችሁ አሳዩ።›› የሚል ነው። መልመጃው ሶስት ምሳሌዎችን ያቀረበ ሲሆን፣ ምሳሌዎቹም ‹‹ምሳሌ፡-1. ተሰበረች=ተ-ሰበር-ኧች፣2. ልጆቹን=ልጅ-ኦች-ኡ-ን፣3. ብልሃተኛነት=ብልሀ-ኣት-ኧኛ-ነት›› የሚሉ ናቸው። ምሳሌዎችን ተከትሎ አስር ጥያቄዎች ቀርበዋል። የመማሪያ መፅሐፉ ምዕላድን አስመልክቶ ማስታዎሻ አላቀረበም። ተማሪዎቹ መልመጃውን የሚሰሩትም ምሳሌዎቹን በመመርኮዝ ነው። ይህም የመልመጃው አደረጃጀት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ መሆኑን ያመለክታል።

በሶስተኛ አስረጂነት የምንመለከተው በገፅ፣70 ቁጥር፣3 ላይ የቀረበውን መልመጃ ነው። መልመጃው ‹‹ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ በምሳሌዎቹ መሰረት አምዶቹን ብቻ ለይታችሁ አውጡ።›› ይላል። መልመጃው ሶስት ምሳሌዎችን ያቀረበ ሲሆን፣ እነሱም ‹‹ምሳሌ፡-1. ኮቱ=ኮት-ኡ አምድ=ኮት ፣2. ብልጠት=ብልጥ-ኧት አምድ=ብልጥ፣ 3.ፈለገ=ፈለግ-ኧ አምድ=ፈለግ›› የሚሉ ናቸው። ተማሪዎቹም የቀረቡላቸውን ምሳሌዎች ከተመለከቱ በኋላ የቀረቡላቸውን አስር ጥያቄዎች ይሰራሉ ማለት ነው። እነዚህ መልመጃዎች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀትን ተከትለው የቀረቡ ሲሆን ከነዚህ መልመጃዎች በተጨማሪ በገፅ፣15 ቁጥር-2፣ በገፅ፣16 ቁጥር-3፣ በገፅ፣19 ቁጥር-1 እና ገፅ፣79 ቁጥር-2 ላይ የሚገኙት ሰዋስዋዊ መልመጃዎች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ አደረጃጀት ተዘጋጅተው የቀረቡ ናቸው። ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸው መምህራን የሰጡት ምላሽ ቀጥሎ ቀርቧል።

ቃለ-መጠይቁ ከቀረበላቸው አራት መምህራን መካከል አንደኛው መምህር ‹‹እኔ እንዳስተዋልኩት፣ የመማሪያ መፅሐፉ ሰዋሰዋዊ ይዘቶች በሁለቱም መንገዶች የተደራጁ መሆናቸውን ነው›› በማለት የመለሱ ሲሆን ሁለተኛው መምህርም ‹‹ይዘቶቹ በሁለቱም ነገር ግን አብዛኞቹ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የተደራጁ መሆናቸውን›› አስረድተዋል። ቀሪዎቹ ሁለት መምህራንም ሁለቱንም አደረጃጀቶች የተከተሉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች

በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ተካተው የሚገኙ መሆናቸውን ገልፀዋል። አጥኚው ሰዋሰዋዊ ይዘቶችን በፈተሸበት ወቅት ሁለቱም አደረጃጀቶች ጥቅም ላይ መዋላቸውን ተመልክቷል። ሁለቱም አደረጃጀቶች የየራሳቸው ጠቀሜታ እንዳላቸው በክለሳ ድርሳን ላይ ተመልክተናል። መማሪያ መፅሐፉ ሁለቱንም አደረጃጀቶች የተከተሉ ሰዋሰዋዊ ይዘቶችን ማካተቱ በጥሩ ጎኑ የሚገለፅ ነው።

### 4.3.4 ከሂደት-ተኮርና ውጤት-ተኮር አደረጃጀት አንፃር

ውጤት ተኮር አደረጃጀት በታላሚው ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ቅርፅ ላይ ያነጣጠረ ነው። ሂደት ተኮር አደረጃጀት ደግሞ የቋንቋውን ቅርፅ ከመተንተን በተጨማሪ እስከ ተግባቦት ድረስ የሚሄድ ነው። መማሪያ መፃሕፍት እነዚህን ጉዳዮች አገናዝበው የሰዋስው መልመጃዎችን ማካተታቸው የሰዋስው ትምህርትን አላማ ለማሳካት ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል። ከዚህ አንፃር ተተኳሪውን መማሪያ መፅሐፍ ለመፈተሽ ተሞክሯል።

በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የተካተቱ ሰዋሰዋዊ ይዘቶች በቋንቋው ቅርፅ ላይ ያነጣጠሩ ሆነው ተገኝተዋል። ይዘቶቹ የቋንቋውን ቅርፅ ከመተንተን ባለፈ እምብዛም ለተግባቦት ያዋሉ አይደሉም። በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ከተካተቱት ሃምሳ ያህል መልመጃዎች ውስጥ በጣም የተወሰኑት የመዋቅሮችን ፍቺ የሚያስተምሩ ቢሆኑም ተግባቦት ላይ የደረሰ አቀራረብ የሌላቸው ናቸው። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው።

በመማሪያ መፅሀፉ ገፅ፣ 70 ላይ ‹‹በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን ቅጥያ ምዕላዶች ለይታችሁ ፍቻቸውን ግለፁ።›› የሚል መልመጃ ይገኛል። መልመጃው አራት ምሳሌዎችን አቅርቧል። ከምሳሌዎቹ መካከል አንዱን ብንመለከት፣‹‹ምሳሌ፦ 1. ፍየሎች ቅጥያ = /-ኦች/፣ ፍቺ = አብዢ /ብዙ ቁጥር አመልካች/›› ይላል። በገጽ፣ 164 ላይ ‹‹በሚከተሉት ግሶች ውስጥ ያሉትን የባለቤትና ተሳቢ ተውላጠ-ስም ወኪል ቅጥያዎችን ለይታችሁ አውጡ።›› የሚል መልመጃ ቀርቧል። በመቀጠል በገፅ፣ 81 ላይ አስር ስም መስራች ቅጥያዎች የቀረቡ ሲሆን፣ መልመጃውም በተሰጡት ስም መስራች ቅጥያዎች ስሞችን እንዲመሰርቱ የሚጠይቅ ነው። በዚሁ ገፅ፣ 81 ላይ አምስት ቅፅል መስራች ቅጥያዎች የቀረበበት መልመጃ የምናገኝ ሲሆን ይኸው መልመጃም በቅፅል መስራች

ቅጥያዎች ቅዕሎችን እንዲመሰርቱ የሚጠይቅ ነው። ከዚህ በተጨማሪም ‹‹በሚከተሉት አታች አረፍተ-ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ተዋቃሪዎች በመጠይቃዊ ቃላትና ሀረጋት በመተካት መጠይቃዊ አረፍተ-ነገር መስርቱ።›› የሚል መልመጃ ይገኛል። የመልመጃውን አሰራር ለመመልከት ካቀረባቸው ምሳሌዎች መካከል አንዱን እንመልከት።

ምሳሌ፡-1. አበበ ለአልማዝ <u>የሰዋሰው መፅሐፍ</u> ገዛላት።

አበበ ለአልማዝ ምን ገዛላት?

ገፅ፣ 155

ከላይ የተመለከትናቸው አስረጂ መልመጃዎች የቋንቋውን ቅርፅ መያዛቸውንና አንዱ ብቻ ቅርፅን ከአጠቃቀምና ፍቺ ጋር አቀናጅቶ ማቅረቡን በ‹ተገቢነት› ስር ተመልክተናል። ይኸው ‹‹በሚከተሉት አታች አረፍተ-ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ተዋቃሪዎች በመጠይቃዊ ቃላትና ሀረጋት በመተካት መጠይቃዊ አረፍተ-ነገር መስርቱ።›› የሚለው ብቸኛ መልመጃ ለሂደት ተኮር አቀራረብ ምሳሌ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም የቋንቋውን የስነ-አገባብ ቅርፅ እስከ ተግባቦት ድረስ የሚያደርስ በመሆኑ ነው። ከዚህ መልመጃ ውጪ ሂደት-ተኮር አቀራረብን የያዘ ይዘት በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ባለመካተቱ፣ የመማሪያ መፅሐፉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ውጤት ተኮር ናቸው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም ቀደም ባሉት ክፍሎች የተመለከትናቸውም ሆኑ ሌሎች መልመጃዎች የቋንቋውን ስነ-ድምፃዊ፣ስነ-ምዕላዳዊና ስነ-አገባባዊ ቅርፆች የሚተነትኑና ቅርፁን ለተግባቦትና በክሂሎች መሰረት አገልግሎት ላይ የማያውሉ በመሆናቸው ነው። ይህን አስመልክቶ ቃለ-መጠይቅ የቀረበላቸው መምህራን የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

ቃለ-መጠይቁ ከቀረበላቸው መምህራን መካከል አንደኛው የመማሪያ መፅሐፉን ሰዋስዋዊ ይዘቶች ‹‹ውጤት-ተኮሮች ብቻ እንጂ ሂደት-ተኮር የሆነ ይዘትን አላካተቱም።›› የሚል ምላሽ ሲሰጡ ሁለተኛው መምህርም ‹‹የሰዋስው ይዘቶች በሙሉ ቋንቋው ቅርፅ ላይ ብቻ ያነጣጠሩ ናቸው። ሂደት ተኮር የሆነ መልመጃ ተካቷል ማለት አልችልም›› ብለዋል። ሶስተኛዋ መምህርት እንደገለፁትም ‹‹የመማሪያ መፅሐፉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች የቃላሚወን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ቅርፅ ከፍቺና አጠቃቀም ጋር አቀናጅተው ያላቀረቡ በመሆናቸው ውጤት ተኮሮች ናቸው›› ብለዋል። ቀሪው አንድ መምህርም ይዘቶቹን ‹‹ውጤት ተኮር ብቻ ናቸው›› ብለዋቸዋል።

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና አስተያየት

### 5.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ይዞት የተነሳው ዋነኛ አላማ በ 1998 ዓ.ም ተሻሽሎ በታተመው የ 12ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ከስነ-ትምህርታዊ መርሆች አንፃር ምን አይነት ገፅታ እንዳላቸው መፈተሽ ሲሆን ከዚህ ዋና አላማ ስርም የሚከተሉትን ዝርዝር ጥቄዎች ለመመለስ ሞክሯል።

1. ተተኳሪ በሆነው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትና አቀራረብ ምን ያህል ስነ-ትምህርታዊ ነው?
2. የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የቋንቋውን ቅርጽ ከፍቺና አጠቃቀም ጋር አቀናጅቶ ከማቅረብ አንጻር ምን ጠንካራና ገጽታ አላቸው?
3. የመማሪያ መጽሐፉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከደረጃው መርሃ-ትምህርት ጋር ምን ያህል ተጣጥመው ተካተዋል?

ከመጻሕፍትና መረጃ መረቦች የተሰባሰቡ ንድፈ-ሐሳባዊ መረጃዎች ጥናቱን እዳር ለማድረስ ጥቅም ላይ ውለዋል። የጥናቱ ግብዓት የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ሰስት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ማለትም ሰነድ ምርመራ፣ ቃለ-መጠይቅና የጽሑፍ መጠይቅ አገልግሎት ላይ ውለዋል። በሂደቱም በተተኳሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች ተሰቅመዋል። አንድ የመማሪያ መጽሐፉ ዝግጅት ባለሙያና አራት መምህራን ቃለ-መጠይቅ ተደርጎላቸዋል። አንድ መቶ አስር የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ሞልተዋል። በሰነድ ፍተሻው የተገኙት መረጃዎች በክለሳ ድርሳን ላይ የሰፈሩ ንድፈ-ሐሳባዊ ጥቆማዎችን መሰረት በማድረግ ተተንትነዋል። ከመምህራን በቃለ-መጠይቅ የተገኙ ምላሾች ደግሞ አይነታዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በገላጭ የምርምር ስልት ተተንትነዋል። ከተማሪዎች በፅሑፍ-መጠይቅ የተሰበሰቡ ምላሾችም ወደ መቶኛ ከተለወጡ በኋላ በገላጭ የምርምር ስልት ተተንትነዋል።

የጥናቱ ተተኳሪ በሆነው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከተመሰረቱበት መርሃ-ትምህርት ጋር ያላቸው ተዛማጅነት ተፈትሿል። በዚህም የመማሪያ መፅሐፉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከመርሃ-ትምህርቱ ጋር ዝምድና የሌላቸው ሆነው ተገኝተዋል። ይኸውም በመርሃ-ትምህርቱ ውስጥ የአናባቢና ተናባቢ ድምፆ ን መካነ-ፍጥረትና ባህርየ-ፍጥረት የተመለከቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ብቻ ተካተው የተገኙ ሲሆን፣ መማሪያ መፅሐፉ ግን ከዚህ ጋር በማይዛመድ ሁኔታ ስለ ድምፀ-ልሳናት፣ ስለ ድምፀ ልሳናዊ ሂደት፣ ስለ ቃል ክፍሎች፣ ስለ ቅጥያዎች፣ ስለቅፅሎች ምስረታ፣ ስለ ስሞች ምስረታ፣ ስለ ሀረግ ዓይነቶች፣ ስለ ነጠላና ውስብስብ አረፍተ ነገር ወዘተ… የሚያወሱ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን አካቶ ይዟል። ይህ የሆነውም ያለ አሳማኝ ስነ ትምህርታዊ ግብ መሆኑን ከመማሪያ መፅሐፉ አሻሻይ ባላሙያ ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል። ይህም የመማሪያ መፅሐፉን ተሻሽሎ መዘጋጀት ከፍተኛ ጥያቄ ውስጥ የሚጥል ችግር ሆኖ ተገኝቷል።

የመማሪያ መፅሐፉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች እንዴት እንደቀረቡ ፍተሻ የተደረገባቸው ሲሆን፣ የተገኘው ውጤትም የሰዋስው ይዘት ማስታዎሻዎችና ትዕዛዞች ከጥቂት ችግሮች በስተቀር የግልፅነት ችግር የሌለባቸው ሆነው ተገኝተዋል። ከትክክለኛነት አንፃር የተደረገው ፍተሻም ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ የታላሚውን ቋንቋ ትክክለኛ ሰዋስዋዊ ቅርፅ በማሳየት በኩል በጣም ጥሩ የሆነ ገፅታ እንዳላቸው የሚያሳይ ውጤት አስገኝቷል።

የቋንቋውን ልዩ ልዩ ሰዋስዋዊ ክፍሎች አመጣጥና ከማቅረብ አንፃር መማሪያ መፅሐፉ አበረታች የሆነ ገፅታ እንዳለው የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። መማሪያ መፅሐፉ የስነ ድምፅ፣ የስነ ምዕላድ፣ የስነ አገባብና የስነ ፍቺ ልዩ ልዩ ክፍሎችን አካቶ ያቀረበ ሲሆን፣ ከሌሎች ሰዋስዋዊ ክፍሎች መካከል ስነ አገባብ አነስ ያለ ትኩረት ተሰጥቶታል። ሌሎች ሰዋስዋዊ ክፍሎች ግን ጥሩ በሆነ ምጣኔ ቀርበዋል።

የመማሪያ መፅሐፉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች የቋንቋውን ቅርፅ፣ ፍቺና አጠቃቀም ማካተታቸውንና ምጣኔያቸው ምን እንደሚመስል ለመገምገም የተደረገው ፍተሻ የይዘቶቹን ደካማ ገፅታ ጠቁሟል። ከጥቂቶች በስተቀር ይዘቶቹ የቋንቋው ቅርፅ ላይ ብቻ

ያተኮሩ ሆነው ተገኝተዋል። ለፍቺና አጠቃቀም የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል።

ከይዘቶቹ ተገቢነት አንፃር የተደረገው ፍተሻ ውጤት የሚያሳየው ደግሞ ሰዋሰዋዊ ይዘቶቹ ከደረጃው ተማሪዎች የመስራት አቅም አንጻር ተገቢ መሆናቸውን ነው። ከዚህ በተጨማሪ በአንድ ተግባር አንድን ሰዋሰዋዊ ቅርፅ ብቻ የሚያስተምሩ ሆነው ተገኝተዋል። ቅርፅን ከፍቺ ጋር አቀናጅተው የሚያቀርቡ መልመጃዎችን ከማቅረብ አንፃር ደግሞ ጉልህ ችግር ተስተውሎባቸዋል። በዚህም የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ መዋቅር በጥሬው የሚያቀርቡ ሆነው ተገኝተዋል።

በሰዋሰዋዊ ይዘቶች አደረጃጀት ላይ የተደረገው ፍተሻም የሚከተሉትን ውጤቶች አስገኝቷል። ሰዋሰዋዊ ይዘቶቹ የታላሚውን ቋንቋ የስነ ድምፅ፣ ስነ ምዕላድ፣ ስነ አገባብና ስነ ፍቻዊ ክፍሎችን የያዙ መልመጃዎችን በተለያዩ ክፍሎች በተደጋጋሚ ከማቅረብ አንፃር ጥሩ ገፅታ ያላቸው ናቸው። እየተደጋገሙ የሚቀርቡ ሰዋሰዋዊ ይዘቶችም ስፋትና ጥልቀት እየጨመሩ የሚሄዱ ሆነው ተገኝተዋል።

ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀቶች አንፃር ምን ገፅታ እንዳላቸው ተፈትሸዋል። በዚህም ይዘቶቹ በሁለቱም መንገዶች የተደራጁ ይዘቶችን አካተው ቀርበዋል። አብዛኞቹ መልመጃዎችም ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀትን ተከትለው የቀረቡ ናቸው።

ሰዋስውን ሂደት ተኮርና ውጤት ተኮር በሆኑ መንገዶች ከማቅረብ አንፃር የተደረገው ፍተሻ ውጤት ደግሞ ሰዋሰዋዊ ይዘቶቹ ውጤት ተኮር አካሄድን የተከተሉ መሆናቸውን አሳይቷል። መልመጃዎቹ የቋንቋውን ቅርፅ ብቻ የሚተነትኑ እንጅን ቅርጹን በአጠቃቀም ያላዋሉ ሆነው ተገኝተዋል።

የተማሪዎችን ትምህርታዊ ዳራ ከማገናዘብ አንፃር ይዘቶቹ ጥሩ ገፅታ ያላቸው መሆናቸውን የመምህራኑና የተማሪዎች ምላሽ አስረድቷል። ሌላው ፍተሻ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ደረጃውን ተማሪዎች ዝንባሌ ከመሳብ አንፃር የተደረገ ሲሆን በዚህም

የደረጃውን ተማሪዎች ዝንባሌ ከመሳብ አንፃር የተደረገ ሲሆን በዚህም ተማሪዎቹ ሰዋስውን ለመማር ዝንባሌ እንደሌላቸው የተማሪዎችና መምህራን ምላሽ ጠቁሟል።

## 5.2 አስተያየት

ከላይ የቀረቡ የጥናቱ ውጤቶችን መሰረት በማድረግ አጥኚው የሚከተሉትን የመፍትሄ ሐሳቦች ሰንዝሯል፤

የቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት የታለመላቸውን ግብ መምታት ይችሉ ዘንድ የተዘጋጀላቸውን መርሃ-ትምህርት አገናዝበው መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ከዚህ አኳያ የዚህ ጥናት ተተኳሪ በሆነው መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከደረጃው መርሃ-ትምህርት ጋር ዝምድና የሌላቸው ናቸው። ወደፊት የሚዘጋጁና ተሻሽለው የሚቀርቡ የቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት የሚመሰረቱበትን መርሃ-ትምህርት መሰረት ያደረጉ ቢሆኑ፤

የታላሚውን ቋንቋ ትክክለኛ ሰዋስዋዊ ቅርፅ ማወቅና ትክክለኛውን ቅርፅ ጠብቆ ተግባቦት መፈፀም የሚሉትን የወቅቱን ሰዋስው ትምህርት ዓላማዎች ከማሳካት አንፃር የመማሪያ መፅሐፉ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የቋንቋውን ቅርፅ ከማስተማር አንፃር እንጂ ትምህርቱን ተግባቦት ላይ ለማዋል ደካማ ሆነው ተገኝተዋል። ዋደፊት የሚዘጋጁና የሚሻሻሉ መማሪያ መፃሕፍት ለዚህ ጉዳይ ትኩረት ቢሰጡ፤

የመማሪያ መፅሐፉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ውጤት ተኮር መሆናቸውም ሰዋስውን ተግባቦት ላይ እንዳይውል አድርገውታል። ይህም በወደፊቶቹ መማሪያ መፃሕፍት ላይ ትኩረት ቢደረግበት፤

መማሪያ መፅሐፉ ከአቀራረብ አንፃር ጥሩ ገፅታ ያለው ሆኖ ተገኝቷል። በዚህም ከግልፅነት፣ ከትክክለኛነትና ከተገቢነት አንፃር ያላቸው ጥሩ ገፅታ ወደፊት በሚዘጋጁ መማሪያ መፃሕፍት ላይም ይበልጥ ተሻሽሎ ቢታይ፤

መማሪያ መጽሐፉ ያካተታቸው አብዛኞቹ ሰዋስዋዊ ይዘቶች የደረጃው ተማሪዎች ቀደም ባሉት ክፍሎች የተዋወቋቸውና የሚመጥኑ መሆናቸውን ናሙና ተማሪዎችና መምህራን ከሰጡት ምላሽ መገንዘብ የተቻለ ሲሆን፣ ይህ የተገቢነት ጥሩ ገፅታ ወደፊት በሚዘጋጁ መማሪያ መፃሕፍት ላይ ቢታይ፤

መማሪያ መፅሐፉ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀትን የተከተሉ ሰዋስዋዊ መልመጃዎችን ይዞ መገኘቱ ጥሩ ገፅታ በመሆኑ ወደፊት በሚዘጋጁና በሚሻሻሉት ላይም ቢደገም፤

መማሪያ መፅሐፉ አንድን መልመጃ በተለያዩ ክፍሎች ያቀረበና ተደጋግመው የቀረቡትም ስፋትና ጥልቀት እየጨመሩ የሚሄዱ በመሆናቸው ከተከታታይነት አንፃር ጥሩ ገፅታ ይዞ ይገኛል። ይህ ጉዳይም በቀጣይ መማሪያ መፃሕፍት ዝግጅት ቢታይ፤

መማሪያ መፅሀፉ የታላሚውን ቋንቋ ልዩ ልዩ ሰዋስዋዊ ክፍሎች ተመጣጣኝነት ባለው ሁኔታ ማቅረቡም የጥሩ አደረጃጀት ገፅታ በመሆኑ በቀጣይ የሚዘጋጁ መማሪያ መፃህፍት ላይ ይህ ሁኔታ ቢደገም፤

ለቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት አዘጋጆችና አሻሻዮች የስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው ንድፈ-ሐሳባዊ እንድምታዎች በመማሪያ መፃሕፍት ላይ እንዴት እንደሚተረጎሙ ያላቸውን ግንዛቤ የሚያሳድጉላቸውን ስልጠናዎች እንዲያገኙ የሚመለከታቸው አካላት ቢያስቡበት፤

መማሪያ መፃሕፍት በሚዘጋጁበት ወቅት የደረጃውን መርሃ-ትምህርት ያገናዘቡ እንዲሆኑ ጠንካራ የክትትልና ቁጥጥር ስራ ቢሰራ፤

የሰዋስውን ትምህርት ዓላማና የስነ-ትምህርታዊ ሰዋስውን ንድፈ-ሐሳባዊ እንድምታዎች በሚመለከት መምህራን የሚኖራቸው ግንዛቤ ወሳኝ ሚና ያለው በመሆኑ መምህራን ተከታታይ ስልጠናዎች ቢሰጧቸው፤

## ዋቢ ጽሑፎች


ትምህርት ሚኒስቴር (1998)። *የ 12ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ*። አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ቤት።

የቋንቋዎች ት/ሥ/ሥ/ዝ/ቡድን/ሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/ ኢንስቲትዩት (1997)። *የ 12ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርሃ ትምህርት*፣ (ያልታተመ)።

ጌታሁን አማረ (1997)። *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ*። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ሁሉባንተ አደመ (1994)። *<<በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በተዘጋጁ የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት የሰዋስው ትምህርት ይዘትና አደረጃጀት ግምገማ።>>* በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)።

ተስፋየ በቀለ (1993)። <<በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት አማርኛ ኢ-አፈ-ፈት ተማሪዎች በተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብ>>። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት ለአማርኛ ማስተማር (TeAm) ኤም ኤ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)።

ንብዩ ሰለሞን (1996)።‹‹በኦሮሚያ ክልል በአማርኛ አፈ-ፈት ለሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ተማሪዎች በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ዉስጥ የሰዋስዉ አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ››፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ያልታተመ፣ለአማርኛ ማስተማር(TeAm) ኤምኤ ዲግሪ ከፊል መሟያነት የቀረበ ጥናት፣ (ያልታተመ)።

ተስፋዬ ሸዋዬ (1981)።‹‹ስነ-ልሳንና ቋንቋን ማስተማር››፣አዲስ አበባ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሑፍ ክፍል፣(ያልታተመ)።

ጌታቸው ተፈራ (1995):: <<ለሁለተኛ ደረጃው እርከንና ለመሰናዶው እርከን በተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሥነ-ልሳን ትምህርት አቀራረብና ደረጃ ግምገማ>>:: በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት ለአማርኛ ማስተማር (TEAM) ኤም ኤ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)::

Allwright, R. L. (1981) <<*What* Do We Want Teaching Materials For?>> *ELT Journal.* Vol. 36, No. 1, 5 — 18.

Batstone, R. (1994) *Grammar.* Oxford: Oxford University Press.

Behar, S. Linda (1994) *The Knowledge Base of Curriculum: An Imoerial Analysis.* Lanham: Lanham University Press of America.

Brown, D. (1994). *Principles of Language and Teaching Practice and Theory.* Cambridge: Cambridge University Press.

Bygate, M. and et.al. (1994) *Grammar and the Language Teacher.* .(eds.) *London.* Prentice Hall International: UK ltd.

Crow, D. L. and Crow, A. (1960) *Introduction to Education Fundamental Principles and Modern Practices,*(new edition) New york: American Book Company.

Cunningsworth,A. (1984) *Evaluating and Selecting EFL Teaching Materials.Oxford: Heinman..* (eds.), The Edinburgh Course in Applied Linguistics, vol. 2, 1-15, OUP, Oxford.

--------------- (1995) *Evaluating and Selecting EFL Teaching Materials.* (fifth print). Oxford: Heinman.

Dawson, C. (1984) *Teaching English as a Foreign Language.* Edinburgh: Nelson Harp.

Dubin,F.AND Olshtain,E. (1986) *Course Design.* Cambridge: Cambridge University Press.

Edge, J. (1993) *Essentials of English Language Teaching.* London: Longman.

Good, C. V. (1973) (3rd ed) *Dictionary of Education.*New York:MacGraw-Hill.

Grant, N. (1987) *Making the Most of Your Text Books.* London: Longman.

Harmer, J. (1987). *Teaching and Learning Grammar.* London: Longman.

Greenbaum, S. (1987) *'Reference Grammars and Pedagogical Grammars',* World Englishes, vol. 6, no. 3, 191-7.

Hutchison, T. and Torres, E. (1994) *<<The Text Book as Agent of Change.>> ELT Journal,* Vol. 48, no. 4, pp. 315-328.

James C. and Grett P. (1991) *Language Awareness in the Class-room.London:* Longman

KleanthesGrohmann(2004)UniversityofCyprus,http://www.linguistlist.org/askling/archive-most-recent/.html) (20/5/2010)

Larsen-Freeman, D. (2003) *Teaching Language: From Grammar to Grammaring.* Boston: Thomson, Heinle.

Dawson, C. (1984) *Teaching English as a Foreign Language.* Edinburgh: Nelson Harp.

Dubin,F.AND Olshtain,E. (1986) *Course Design.* Cambridge: Cambridge University Press.

Edge, J. (1993) *Essentials of English Language Teaching.* London: Longman.

Good, C. V. (1973) (3rd ed) *Dictionary of Education.*New York:MacGraw-Hill.

Grant, N. (1987) *Making the Most of Your Text Books.* London: Longman.

Harmer, J. (1987). *Teaching and Learning Grammar.* London: Longman.

Greenbaum, S. (1987) *'Reference Grammars and Pedagogical Grammars',* World Englishes, vol. 6, no. 3, 191-7.

Hutchison, T. and Torres, E. (1994) *<<The Text Book as Agent of Change.>> ELT Journal,* Vol. 48, no. 4, pp. 315-328.

James C. and Grett P. (1991) *Language Awareness in the Class-room.London:* Longman

KleanthesGrohmann(2004)UniversityofCyprus,http://www.linguistlist.org/askling/archive-most-recent/.html) (20/5/2010)

Larsen-Freeman, D. (2003) *Teaching Language: From Grammar to Grammaring.* Boston: Thomson, Heinle.

Rowntree, D. (1991) *A Dictionary of Education.* London: Harper and Row Publishers.

Sheldon, L. E. (1988) <<*Evaluating ELT Text Book and Materials.*>> ELTJournal. Vol. 42, No. 4, pp. 237 – 246.

Stern, H.H. (1992) *Issues and Options in Language teaching.* Oxford: Oxford University Press.

Stevick, E. W. (1986) *Images and Options in the Language Class Room.* Cambridge: Cambridje University Press.

Swan, M. (1994) <<Design Criteria for Pedagogic Language Rules.>> In Bygate, M. 'etal' (eds.) , *Grammar and the Language Teacher.* New York: Prentice Hall. pp. 45-55.

Taba,H. (1962) *Currriculum Development Theory and Practice.*New York:Hascourt Brace Jouanorich.

Titone, R. (1968) *Teaching Foreign Languages.* Washington D. C.: Georgetown University Press.

Tyler, R. (1949) *Basic Principles of Curriculum and Instruction.*Chicago:Chicago University Press.

Tonkyn, A. (1994) <<*Introduction: Grammar and the Language Teacher.*>> . In Bygate, M. 'etal' (eds.) , *Grammar and the Language Teacher.* New York: Prentice Hall. pp. 1-14.

Ur,P. (1994) *Grammar Practice Activities, a Practical Guide for Language Teachers.*London: Cambridje University Press.

---------- ------(1996) *A Course in Language Teaching.* Cambridge: CUP.

Rowntree, D. (1991) *A Dictionary of Education.* London: Harper and Row Publishers.

Sheldon, L. E. (1988) <<*Evaluating ELT Text Book and Materials.*>> ELTJournal. Vol. 42, No. 4, pp. 237 – 246.

Stern, H.H. (1992) *Issues and Options in Language teaching.* Oxford: Oxford University Press.

Stevick, E. W. (1986) *Images and Options in the Language Class Room.* Cambridge: Cambridje University Press.

Swan, M. (1994) <<Design Criteria for Pedagogic Language Rules.>> In Bygate, M. 'etal' (eds.) , *Grammar and the Language Teacher.* New York: Prentice Hall. pp. 45-55.

Taba,H. (1962) *Currriculum Development Theory and Practice.*New York:Hascourt Brace Jouanorich.

Titone, R. (1968) *Teaching Foreign Languages.* Washington D. C.: Georgetown University Press.

Tyler, R. (1949) *Basic Principles of Curriculum and Instruction.*Chicago:Chicago University Press.

Tonkyn, A. (1994) <<*Introduction: Grammar and the Language Teacher.*>> . In Bygate, M. 'etal' (eds.) , *Grammar and the Language Teacher.* New York: Prentice Hall. pp. 1-14.

Ur,P. (1994) *Grammar Practice Activities, a Practical Guide for Language Teachers.*London: Cambridje University Press.

----------------(1996) *A Course in Language Teaching.* Cambridge: CUP.

Westney, P. (1994) <<*English Grammar and the Views of English Teachers*>>. In Bygate, M., Tonkyn, A. and Williams, E. (eds.) Grammar and the Language Teachers. Cabridge: Cambridge University Press. Pp. 105-118.

Wilkins, D. A. (1972) *Linguistics in Language Teaching*. New York: Edward Arnold.(puplishers) Ltd.

<<*Writing Language Teaching Materials*>> (2003). Internet Site: wwwwebofenglish.co.uk/ltmat.htm. (25/5/2010)

መምህር 2፡-

1. የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ስም፡- ዳሞት የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ትምህርት ቤት
2. ፆታ፡- ሴት
3. የትምህርት ደረጃ፡- 12+4
4. የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ፡- አማርኛ መምህርነት
5. የአገልግሎት ዘመን፡- 6

ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ቀን፡- 5/08/2003

መምህር 3፡-

1. የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ስም፡- ጂጋ የከፍተኛ ት/ት መሰናዶ ት/ቤት
2. ፆታ፡- ወንድ
3. የትምህርት ደረጃ፡- 12+4
4. የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ፡- አማርኛ መምህርነት
5. የአገልግሎት ዘመን፡- 4

ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ቀን፡- 6/08/2003

መምህር 4፡-

6. የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ስም፡- ሽኩዳድ የከፍተኛ ት/ት መሰናዶ ት/ቤት
7. ፆታ፡- ወንድ
8. የትምህርት ደረጃ፡- 12+4
9. የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ፡- አማርኛ መምህርነት
10. አገልግሎት ዘመን፡- 7

ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ቀን፡- 7/08/2003

ጥያቄ 1፡-በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የተካተቱ ሰዋስዋዊ ገለፃዎች(ማስታዎሻዎች) ለተማሪዎች ምን ያህል ግልፅ ሆነው ቀርበዋል ይላሉ?

መልስ፡-

መምህር 1፡- …ከዚህ አንፃር ችግር አላገኘሁባቸውም፡፡ ግልፅ ሆነው የቀረቡ ናቸው፡፡

መምህር 2፡- ማስታዎሻዎች ተማሪዎች ተማሪዎች ሊረዷቸው በሚችሏቸው ሁኔታ ግልፅ ሆነው የቀረቡ ናቸው፡፡ …ውስብስብነትም የለባቸውም፡፡

መምህር 3፡- በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የሚገኙት የሰዋስው ገለፃዎችን ተማሪዎች ሊረዷቸው የሚችሏቸውና ግልፅ ሆነው የቀረቡ ናቸው፡፡ …በዚህ በኩል ችግር አላገኘሁባቸውም፡፡

መምህር 4፡- …ማስታዎሻዎቹ ግልፅ ሆነው የቀረቡ ናቸው፡፡ በማስታዎሻዎቹ ውስጥ የጎላ የግልፅነት ችግር አይታይም፡፡ …አንዳንድ ችግሮች ቢኖሩም በትምህርት ሂደቱ ውስጥ ችግር ሳይፈጥሩ የሚስተካከሉ ናቸው፡፡

ጥያቄ 2፡- በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የሚገኙ የሰዋስው መልመጃ ትዕዛዞች ለተማሪዎች ምን ያህል ግልፅ ናቸው ይላሉ?

መልስ፡-

መምህር 1፡- …የሰዋስው መልመጃ ትዕዛዞች በበቂ ሁኔታና ግልፅ ሆነው የቀረቡ ናቸው፡፡

መምህር 2፡- ሁሉም ሰዋስዋዊ መልመጃዎች ትዕዛዞች ያሏቸው ሲሆኑ ትዕዛዞችም ግልፅ ናቸው፡፡

መምህር 3፡- …ትዕዛዞቹ ላይ ምንም ችግር የለም ማለት ይቻላል፡፡ …ግልፅ ናቸው፡፡

መምህር 4፡- …ሁሉም የሰዋስው መልመጃ ትዕዛዞች በግልፅ ሁኔታ የቀረቡ ናቸው፡፡

ጥያቄ 3፡- የመማሪያ መፅሐፉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች የቋንቋውን ልዩ ልዩ ሰዋስዋዊ ክፍሎች በተመጣጠነ ሁኔታ ከማካተት አንፃር ምን ገፅታ አላቸው ይላሉ?

መልስ፡-

መምህር 1፡- …ሰዋስዋዊ ይዘቶች ውስጥ የተወሰነ የሚዛናዊነት ችግር ይስተዋላል፡፡ በአብዛኛው ግን ደህና ናቸው፡፡

መምህር 2፡- ከተመጣጣኝነት አንፃር ትሩ ናቸው፡፡ …ይዘቶቹ ተመጣጣኝ…ተቀራራቢ በሆነ ቁጥር የተሰራጩ ናቸው፡፡

መምህር 3፡- የመማሪያ መፅሐፉ የሰዋስው ክፍሎች ልዩ ልዩ ክፍሎችን ለማካተት የሞከሩ ናቸው፡፡ …ከስርጭት አንፃርም ሚዛናዊ የሚባሉ ናቸው፡፡ …ሙሉ በሙሉ እኩል የሆነ ባይሆንም በአጠቃላይ ሲታይ ግን አበረታች የሚባል ነው፡፡

መምህር 4፡- …እኔ ሰዋስው ይዘቶችን ከሚዛናዊነት አንፃር ጥሩ ናቸው ነው የምለው፡፡

ጥያቄ 4፡- የመማሪያ መፅሀፉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች በቋንቋው ቅርፅ በተጨማሪ የሰዋስዋዊ መዋቅሮቹን ፍቺና አጠቃቀምን ለማስተማር የሰጡትን ትኩረት እንዴት ይገልፁታል?

መልስ፡-

መምህር 1፡- …በዚህ በኩል እንኳን ይዘቶቹ በሙሉ የቋንቋውን ቅርፅ ብቻ ሚያስተምሩ ናቸው፡፡ …የይዘቶቹ ትኩረትም ይህ ብቻ ነው፡፡

መምህር 2፡- ከዚህ አንፃር ትልቅ ችግር አለባቸው፡፡ ይዘቶቹ የመዋቅር ትንተና ላይ ብቻ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡

መምህር 3፡- መልመጃዎቹ ሰዋስውን በደረቁ ያቀረቡ ናቸው፡፡ ለፍቺና አጠቃቀም ምንም ትኩረት አልሰጡም፡፡

መምህር 4፡- መልመጃዎቹ የቋንቋውን ሰዋስው ብቻ የሚያስተምሩ እንጂ ለፍቺና አጠቃቀም ግን ትኩረት የሚሰጡ አይደሉም፡፡

ጥያቄ 5፡- በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ሰዋስውን ለማስተማር የተካተቱት ይዘቶች ከደረጃው ተማሪዎች ከመስራት አቅምና ተገቢውን እውቀት ከማስጨበጥ አንፃር እንዴት □ገልጿቸዋል?

መልስ፡-

መምህር 1፡- ….ይዘቶቹ ለተማሪዎቹ እውቀት ማያስጨብጡ ናቸው፡፡ ይህንንም ለማስተዋል ችያለሁ፡፡ አንድ ሰዋስው መልመጃ አንድን ሰዋስዋዊ ክፍል ብቻ ለማስተማር ታስቦ እንደተዘጋጀ ከይዘቶቹ ተረድቻለሁ፡፡ …እናም ጥሩ ናቸው ነው የምለው፡፡

መምህር 2፡- …በርግጥ በደረጃው ተማሪዎች መካከል ልዩነት ሊኖር ይችላል፡፡ ነገር ግን ይዘቶቹን ከአብዛኛው የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች አንፃር ካናቸው ተገቢነት አላቸው የሚል አስተያየት ነው ያለኝ፡፡

መምህር 3፡- የተካተቱት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ተገቢ ናቸው የሚል አስተያየት ነው የምሰጠው፡፡

ጥያቄ 6፡- ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ የቋንቋውን ቅርፅ፣ ፍቺና አጠቃቀም አቀናጅተው የሚያስተምሩ መልመጃዎችን ምን ያህል አካተዋል?

መልስ፡-

መምህር 1፡- …ቀደም ሲል እንዳልኩህ ይዘቶቹ ለቅርፅ ብቻ ትኩረት የሚሰጡ በመሆናቸው ከቅርፅና ፍቺ ጋር ተቀናጁ ይዘቶችን አላካተቱም፡፡

መምህር 2፡- በቀደመው ጥያቄ እንደመለስኩልህ በመልመጃዎች ውስጥ የቋንቋው ቅርፅ እን

ጂ ...ቅርፁ ከፍቺና አጠቃቀም ጋር ተቀናጅቶ አልቀረበም።

መምህር 3፡- ሰዋስው ብቻውን.... ከፍቺና አጠቃቀም ጋር ሳይቀናጅ ነው የቀረቡት።

መምህር 4፡- ...ከዚህ አንፃር ሙሉ ለሙሉ ድክመት ይታያል። ችሬ የሰዋስው መልመጃ ነው በመልመጃዎቹ ውስጥ የሚገኘው።

ጥያቄ 7፡- ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ ከተከታታይነት አንፃር ማለትም አንድን ሰዋስዋዊ መልመጃ በተለያዩ ክፍሎች ደጋግሞ ከማቅረብ አንፃር ምን አይነት ገፅታ ያላቸው ናቸው?

መልስ፡-

መምህር 1፡- አዎ! አንድ መልመጃ በተለያዩ ክፍሎች እየተደጋገመ ነው የቀረበው። ...ሁሉም መልመጃዎች በእኩል መጠን ተደጋግመዋል ማለት ግን አይደለም። ...ባጠቃላይ ግን ከተከታታይነት አንፃር ጥሩ ናቸው።

መምህር 2፡- መልመጃዎች በተለያዩ ክፍሎች ተደጋግመው ቀርበዋል።...ሁሉም በእኩል መጠን ባይደጋገሙም ጥሩ ናቸው የሚል አስተያየት ነው ያለኝ።

መምህር 3፡-...ሁሉም በእኩል መጠን ባይደጋገሙም አብዛኞቹ ይዘቶችን ግን ተደጋግመው እናገኛቸዋለን።

መምህር 4፡- አብዛኞቹ ተደጋመዋል። ...በዚህ በኩል መፅሐፉ ጥሩ ነው የሚል አስተያየት ነው ያለኝ።

ጥያቄ 8፡- በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ተደጋግመው የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች ሰፋና ጥልቀት እየጨመሩ የሚሄዱ ናቸው፤ ወይስ ለውጥ አይታይባቸውም?

መልስ፡-

መምህር 1፡- አንድ መልመጃ ሌላ ቦታ ላይ ተደግሞ ሲቀርብ ከበፊቱ ጠንከር እንደሚል ነው ያስተዋልኩት።

መምህር 2፡- መልመጃዎቹ ሲደጋገሙ እየከበዱ እየከበዱ ነው የሚሄዱት።

መምህር 3፡- ከአንዳንድ መልመጃዎች በስተቀር መልመጃዎቹ እየከበዱ የሚመጡ ናቸው።

መምህር 4፡- በተለያዩ ክፍሎች የሚደጋገሙ ይዘቶች በሂደት ሰፋ ሰፋ እያሉ ሚሄዱ ናቸው።

ጥያቄ 9፡- በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው መልመጃዎች የተደራጁት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ነው፤ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ነው? የትኛው አደረጃጀት በስፋት ይገኛል?

መልስ፡-

መምህር 1፡-...እኔ ያስተዋልኩት ሁለቱ አደረጃጀቶች በተለያየ ቦታ በመፅሐፉ ውስጥ እንደቀረቡ ነው።

መምህር 2፡- ይዘቶቹ በሁሉቱም አደረጃጀቶች... አብዛኞቹ ግን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ነው የተደራጁት፡፡

መምህር 3፡- አብዛኞቹ ከአጠቃላይ ወደ ዝር ዝር ነው፤ ...መጀመሪያ ገለፃ ወይም ማስታዎሻ ከቀረበ በኋላ ነው አብዛኞቹ መልመጃዎች የቀረቡት፡፡ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የተደራጁ መልመጃዎችም አሉ፡፡

መምህር 4፡- በሁለቱም መንገድ እንደቀረቡ ነው ያለኝ አስተያየት፡፡ ...እኔ እንዳስተዋልኩት፡፡

ጥያቄ 10፡- ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ ውጤት ተኮር ማለትም በቋንቋው ቅርፅ ላይ ብቻ የሚያተኩሩ ወይስ ሂደት ተኮር ማለትም ከቋንቋው ቅርፅ ተነስተው ቅርፁን ለተግባቦት ወይም አገልግሎት ላይ የሚያውሉ ናቸው? በዚህ ላይ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ላይ ምን ገፅታ አስተውለዋል?

መልስ፡-

መምህር 1፡- ሂደት ተኮር አይደሉም፡፡ በሙሉ ውጤት ተኮር ናቸው፡፡

መምህር 2፡- በሙሉ በቋንቋው ቅርፅ ላይ ብቻ እንደሚያተኩሩ ቀደም ሲል ነግሬሃለሁ፡፡ ይህ ይዘቶቹ ውጤት ተኮር ብቻ መሆናቸውን ያሳየናል፡፡

መምህር 3፡- ቀደም ሲል ተነጋግረነዋል፡፡ ...በዚህም ውጤት ተኮር መሆናቸውን እንረዳለን፡፡

መምህር 4፡-...የቋንቋው ቅርፅ አጠቃቀም ላይ ሲውል ያስተዋልኩበትን መልመጃ አላስታውስም፡፡ በመፅሐፉ ውስጥ ያሉት የሰዋስው መልመጃዎች ውጤት ተኮር ናቸው፡፡

ጥያቄ 11፡- በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የሚገኙት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ደረጃው ተማሪዎች ቀደም ባሉት የክፍል ደረጃዎች ላይ የተዋወቋቸው ወይም ተማሯቸው ናቸው?

መልስ፡-

መምህር 1፡-ሁሉም ይዘቶችን ማለት ይቻላል አስራ አንደኛና ከዛ በታች በነበሩበት ወቅት የተማሯቸው ናቸው፡፡

መምህር 2፡-ከመካኑ ፍትረትና ባህርየ ፍጥረት መልመጃዎች በስተቀር ሌሎች መልመጃዎች ከበድ ብለው ቢቀርቡም ታች ክፍል ላይ የተማሯቸው ናቸው፡፡

መምህር 3፡- ከስነ-ድምፅ በስተቀር ሌሎች ይዘቶችን የተማሯቸው ናቸው፡፡ ልላ አዲስ መልመጃም አላየሁም፡፡

መምህር 4፡- መልመጃዎች ወይም የትምህርቱ ስፋትና ይዘት ከበድ ብሎቀርቦ ሲሆን ይችላል፡፡ ግን አብዛኞቹን ከዚህ በፊት የተማሯቸው ናቸው፡፡

ጥያቄ 12፡- የደረጃውን(የ 12ኛ ክፍል) ተማሪዎችን በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ለሚገኙት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ያላቸውን ዝንባሌ እንዴት ይገልፁታል፡፡

መልስ፡-

መምህር 1፡- ተማሪዎቹ ለሰዋስው ትምህርት ዝንባሌ የሌላቸው ናቸው ብል፤ የተሳሳትኩ አይመስለኝም። ...በሰዋስው ክፍለ-ጊዜ ቀዝቃዛ ተሳትፎ ነው የሚያደርጉት።

መምህር 2፡- የስነ-ፅሑፍና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ክፍል ውስጥ ሲሰሩ በደስታና በፍላጎት ነው።

መምህር 3፡- ...ለምሳሌ፡- ከሰዋስው ክፍሎች ውስጥ ስነ-ፍቹን ብናይ ተማሪዎች ለነዚህ ዝንባሌ ይታይባቸዋል።

መምህር 4፡- ተማሪዎቹ ሰዋስውን እንደከባድ ስለሚያዩት ይመስለኛል፤ ፍልጎት የላቸውም።

ጥያቄ 13፡- በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች የታላሚውን ቋንቋ ትክክለኛ ሰዋስዋዊ ስርዓት/መዋቅር ከማሳየት አንጻር ምን ገጽታ እንዳላቸው ቢገልጹልኝ?

መልስ፡-

መምህር 1፡- ከዚህ አንጻር እንኳን ... እኔ ምንም ነገር አላስተዋልኩም። ማለቴ... ምንም ችግር አላገኘሁባቸውም።

መምህር 2፡- እስካሁን ባስተማርኩባቸው ጊዜያት ስህተት ነው የምለው ... ከትክክለኛውን የአማርኛ ሰዋስው ስርአት ጋር የሚጋጩ ነገሮችን መጽሐፉ ላይ አላገኘሁም ።

መምህር 3፡ ምናልባት ከግድፈት አንጻር የሚታዩ ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ እንጂ ሰዋስዋዊ ስህተት እንኳን አላየሁም።

መምህር 4፡- የቋንቋው ሰዋስዋዊ ስርዓትማ በጣም በትክለኛ መንገድ ነው ቀርቦ የሚገኘው።

አባሪ ሁለት

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም
## በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል
## የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሀ ግብር

### የመማሪያ መጽሐፉ አሻሻይ ባለሙያዎች ቃለ-መጠይቅ

የዚህ ቃለ-መጠይቅ ዓላማ በ 1998 ዓ.ም ተሻሽሎ አገልግሎት ላይ በዋለው የ 12ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ከስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው አንፃር መፈተሽ ነው:: እርስዎም በመማሪያ መፅሐፉ የማሻሻል ስራ ላይ ከተሳተፉ ባለሙያዎች መካከል በመሆንዎ ለዚህ መጠይቅ ተመርጠዋል:: ለቃለ መጠይቁም ፍቃደኛ በመሆነዎ በቅድሚያ ላቅ ያለ ምስጋናን አቀርባለሁ::

ጥያቄ 1:- የመማሪያ መጽሐፉ የማሻሻል ስራ ሂደት እንዴት እንደነበር አጠር ያለ ማብራሪያ ቢሰጡ?

ጥያቄ 2:- በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚካተቱ የትምህርት ልምዶች ከመሪሃ-ትምህርቱ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው መሆናቸው ምን ያህል ጠቃሚ ነው ይላሉ?

ጥያቄ 3:- በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከተመሰረቱበት መርሃ-ትምህርት ጋር ምንም ዝምድና እንደሌላቸው፣ የሰነድ ግምገማው ውጤት አሳይቷል:: እርስዎም የመማሪያ መጽሐፉ ገምጋሚ ባለሙያና የመርሃ-ትምህርቱ አዘጋጅ ባለሙያ በመሆንዎ ይህ እንዴት ሊሆን እንደቻለ ቢገልጹልኝ?

ጥያቄ 4፡- በጥያቄ ቁጥር 3 ላይ የተጠቀሰው ማለትም መርሃ-ትምህርቱ ላይ የሌሉ ይዘቶች መመሪያ መጽሐፉ ውስጥ መካተታቸው ለምን ዓላማ ሲባል ወይም ምን ጥቅምና ጉዳት አለው ይላሉ?

አባሪ ሶስት

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም
## በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል
## የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሀ ግብር

## የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ

የዚህ መጠይቅ አብይ አላማ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ተግባራዊ ስነ-ልሳን አማርኛን በማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ ለማዘጋጀት መረጃ ለመሰብሰብ ነው። የጥናቱ ርዕስ ‹‹ለአስራ ሁለተኛ ክፍል እያገለገለ በሚገኘው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ከስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው አንፃር መገምገም የሚል ነው። ስለዚህ ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በትዕዛዙ መሠረት የራሳችሁን ምላሽ ስጡ። ከጓደኛ ሀሳብ መጠየቅ ወይም በጋራ መስራት የጥናቱን መረጃ ስለሚያዛባ ጥያቄዎቹን በግላችሁ እንድትሞሉ በአክብሮት እጠይቃለሁ። ላደረጋችሁት ትብብር ሁሉ አጥኚው ከፍ ያለ ምስጋናን ያቀርባል።

ከዚህ በ□ች ለቀረቡት መጠይቆች መልስ ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮች ከዝርዝር መጠይቆቹ ትይዩ ቀርበዋል። አማራጮቹም በቁጥር የተወከሉ ሲሆን እናንተ በምትስማሙበት የመመዘኛ ነጥብ ስር የ«✓» ምልክት አስቀምጡ።

| | |
|---|---|
| በጣም እእስማማለሁ፡ | 1 |
| እእስማማለሁ፡ | 2 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል ፡ | 3 |
| አልስማማም ፡ | 4 |
| በጣም አልስማማም | 5 |

| ተ.ቁ | ዝርዝር መጠይቆች | የመመዘኛ ነጥቦች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 1 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ገለጻዎች(ማስታዎሻዎች) ግልጽ ናቸው:: | | | | | |
| 2 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው መልመጃ ትዕዛዞች ግልጽ ናቸው:: | | | | | |
| 3 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው መልመጃዎች ከእናንተ(ከ 12ኛ ክፍል ተማሪዎች) የመስራት አቅም ጋር ተመጣጣኝ ናቸው:: | | | | | |
| 4 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው መልመጃዎች በተለያዩ ምዕራፎች ተደጋግመው ቀርበዋል:: | | | | | |
| 5 | የሰዋስው መልመጃዎች በመማሪያ መጽሐፉ የተለያዩ ክፍሎች ተደጋግመው ሲቀርቡ ከበድና ሰፋ እያሉ የሚሄዱ ናቸው:: | | | | | |
| 6 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው መልመጃዎች ከእናንተ(የ 12ኛ ክፍል ተማሪዎች) ካላችሁበት የክፍል ደረጃ በፊት የተማራችኋቸው ናቸው:: | | | | | |
| 7 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙትን የሰዋስው መልመጃዎች ለመማር ዝንባሌ አለህ/ አለሽ:: | | | | | |